# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት
# Journal of Ethiopian Church Studies

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
## የማኅበረ ቅዱሳን ጥናትና ምርምር ማእከል

The Ethiopian Orthodox Tewahido Church
Mahibere Kidusan Research Centre


**ቍጥር 6** | አዲስ አበባ | ነሐሴ ፳፻፲ ዓ.ም

**No. 6** | **Addis Ababa** | **August 2018 G.C**

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት
# Journal of Ethiopian Church Studies

**ቍጥር 6** **ነሐሴ ፳፻፳ ዓ.ም**
**No. 6** **August 2018 G.C**

**ነሐሴ ፳፻፲ ዓ.ም ታተመ**
**Published: August 2018**

## አማካሪ ቦርድ

| | |
|---|---|
| ብፁዕ አቡነ ሉቃስ | የሰቲት ሁመራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ |
| ክብርት አምባሳደር ዐለምፀሐይ መሠረት | በኡጋንዳ የኢትዮጵያ አምበሳደር |
| ፕ/ር ባዬ ይማም | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |
| ፕ/ር ሽፈራው በቀለ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |
| ፕ/ር ጥላሁን ተሾመ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |
| ዶ/ር ውዱ ጣፈጠ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |
| ዶ/ር የራስ ወርቅ አድማሴ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |
| ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ | ማኅበረ ቅዱሳን |
| ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |

## አርትኦት ኮሚቴ

መስፍን መሰለ
ዶ/ር ዳንኤል ጥሩነህ
ዶ/ር አለልኝ አስቻለ
ዶ/ር ዘላለም መሰረት
ወ/ሮ መሠረት ከበደ
ወ/ሮ ኤልሳቤት ደምሴ
መ/ር ቸርነት አበበ
አማረ ፀሐይ
ዶ/ር ደርብ አዶ
ዶ/ር ፍሬሕይወት ባዩ
ዶ/ር ኃይለእየሱስ ሙሉቀን
ዶ/ር አበራ ጥበቡ

## ዋና አርታኢ፡-

ዶ/ር ዳንኤል ጥሩነህ

**የመሸጫ ዋጋ**

| | |
|---|---|
| በኢትዮጵያ | ብር 60 |
| በውጭ ሀገር | 10$ የአሜሪካ ዶላር |

## Advisory Board

| | |
|---|---|
| His Grace Abune Lukas | Archbishop of Setit Humera Diocese |
| H.E. Ambassador Alemtsehay Meseret | The Ethiopian Ambassador to Uganda |
| Prof. Baye Yimam | Addis Ababa University |
| Prof. Shiferaw Bekele | Addis Ababa University |
| Prof. Tilahun Teshome | Addis Ababa University |
| Dr. Wudu Tafete | Addis Ababa University |
| Dr. Yeraswork Admassie | Addis Ababa University |
| Dn. Birhanu Admas | Mahibere Kidusan |
| Dn. Yaregal Abegaz | Addis Ababa University |

## Editorial Committee:

Mesfin Messele
Dr. Daniel Tiruneh
Dr. Alelign Aschale
Dr. Zelalem Meseret
W/ro Meseret Kebede
Mhr. Chernet Abebe
Amare Tsehay
W/ro Elisabet Demissie
Dr. Derib Ado
Dr. Firehiwot Bayu
Dr. Haileyesus Muluken
Dr. Abera Tibebu

## Editor-in- chief:

Dr. Daniel Tiruneh



**Selling Price**

| | |
|---|---|
| **Ethiopia** | **Eth. Birr 60** |
| **Overseas** | **Us$10** |

# Transcription

## 1) Consonant

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| h ሀ | r ረ | t ተ | ʾአ | ž ዠ | ṭ ጠ | f ፈ |
| l ለ | s ሰ | č ቸ | k ከ | y የ | č̣ ጨ | p ፐ |
| ḥ | š ሸ | ḫ | w ወ | d ደ | p̣ ጰ | q ʷ |
| m መ | q ቀ | n ነ | ʿ ዐ | ǧ ጀ | ṣ | ḫʷ |
| ś | b በ | ñ ኘ | z ዘ | g ገ | ṣ́ | k ʷ |
| | | | | | | g ʷ |

## 2) Vowels

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| ä | u | i | a | e | ə or no vowel | o |
| bä=በ | ቡ | Bi =ቢ | b= ባ | be=ቤ | b ə, b=ብ | bo=ቦ |

# ማውጫ/Contents

ገጽ/Pages

**መቅድም** ....................................................................................v

Preface.......................................................................................... vi

መጽሐፈ ሄኖክ በግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ያለው ቦታ:
በማብራሪያ የታገዘ ትርጉምና ትንተና ......................................................1

**ኃይለ ኢየሱስ አለባቸው ሞላው** ..........................................

የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊ ፎክሎር.........................................................33

**በ ፍሬሕይወት ባዩ** ...............................................................

ቅኔ ዘዝክረ አድዋ ወዘመነ ፋሽስት: ፍቺና ሐተታ ...............................................54

**ኃይለ ኢየሱስ አለባቸው ሞላው**

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ለዘመን አቆጣጠር፣ ለከዋክብት እና
ለአየር ትንበያ ጥናት መጽሐፈ ሄኖክ መነሻ...................................................74

**በዮሐንስ ደምስ በለጠ** ...........................................................

Wallie Iyesus: An Aksumite Church in a Zagwe Landscape?...............................104

**Yeras Work Admassie and Tekeste Negash**.......................................

Education of the Ethiopian Orthodox Church: Personal Reflection on
Nibab Bet and Zema Bet............................................................................112

**Woube Kassaye**.....................................................................

# መቅድም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሕገ-ልቡና፣ በሕገ-ኦሪትና በሕገ-ወንጌል ዘመናት ያካበተችውን ታሪክ፣ ጥበብ፣ ክህሎት፣ ሐሳብ፣ ፍልስፍና፣ እውነት፣ ወዘተ በመጠቀም ለሀገሪቱ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጋለች። እነዚህም የቤተ ክርስቲያኗ ሀብታት የሆኑት ጥንታዊ ታሪክ፣ አኩሪ ባህል፣ ጥልቅ ዕውቀትና ጥበብ በቀደሙ አባቶቻችን ተጽፈው ተስፋፍተውና ተሰንደው ይገኛሉ። በዚህም እንደ ትምህርት ሥነ ከዋክብት ፍልስፍና ሥነ ጥበብ (ሥነ ጽሑፍ፣ ሥነ ዜማ፣ ሥነ ሥዕል፣ ሥነ ምሕንድስና ወዘተ) ለመሳሰሉ ዘመናዊ የጥናት መስኮች መነሻ በመሆን አገልግላለች።

የጥንታዊ ታሪክና አያሌ ቅርስ ባለቤት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በነበራት ሀገራዊ አበርክቶት ላይ የሚጠበቀውን ያህል ጥናትና ምርምር አልተደረገበትም። በመሆኑም የቀደምት አበውና እመው ሥራዎችና አበርክቶዎች ለትውልድ ለማስተዋወቅ በሥራዎቹም ላይ ለመመራመርና የዕውቀት ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል።

ቤተ ክርስቲያኗ ካላት የረጅም ዓመታት ታሪክና በርካታ ሀብታት አንጻር ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የጥናትና ምርምር ተቋማት ሊኖሯት ይገባ ነበር። ይህንንም ክፍተት በመረዳት ማኅበረ ቅዱሳን የጥናትና ምርምር ማእከል በ 2001 ዓ.ም ሊያቋቁም ችሏል። ማእከሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የተደረጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማሰባሰብ አምስት የጥናት መጽሔቶችን አሳትሟል። ይህ ስድስተኛው የጥናት መጽሔትም የዚሁ ሥራ አካል ነው።

የቤተ ክርስቲያኗ መጠነ ሰፊ ሀብታት ብዙ ጥናትና ምርምር የሚጠይቁ ቢሆንም አሁን በማኅበረ ቅዱሳን የተጀመረው ጥናትና ምርምርን አሰባስቦ የማሳተም ሥራ ጋንን በጠጠር የመደገፍ ያህል ነው። ስለሆነም በውጭ ሀገርም ሆነ በሀገር ውስጥ ያሉ የዘርፉ ባለሙያዎች በቤተ ክርስቲያኗ ባሉ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናትና ምርምር በማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ከወዲሁ አደራ እያልን የጥናትና ምርምር ማእከሉን አድራሻ በመጠቀም የምርምር ሥራዎቻችሁን እንድትልኩልን በእግዚአብሔር ስም እንጠይቃለን።

# Preface

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church has made significant contributions to the country's religious, social, economic, cultural and political interactions through its history, wisdom, skills, ideas, philosophy, truth, etc that it developed from the Law of Consciense, the Old testament and the New Testament. The church's rich history, culture, knowledge, and wisdom were written and expanded by our forefathers. As a result, it became the basis for modern studies, such as astronomy, philosophy, art (literature, melody, art, engineering, etc.).

The church, which is the owner of rich history and numerous heritage, has not been as well researched as expected given the significant contribution it has to the country. Therefore, we need to do more to promote the works and contributions of our forefathers and grandparents thereby doing research on their work and enabling knowledge transfer.

In view of its long history and rich resources, the church should have had world-class and standardized research institutes. Recognizing this gap, Mahiber Kidusan established Research Center in 2009. Since its establishment, the center has published five research journals on a variety of topics related with church issues. This sixth research journal is also part of this endeavor. Although the church's vast resources require much research, the work commenced by Mahiber Kidusan is very little. Therefore, we kindly request scholars both at home and abroad to do research on topics related with church matters and carry out their Christian duties. We also humbly urge you to send us your research work using the address of the Research Center.

# መጽሐፈ ሄኖክ በግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ያለው ቦታ፡ በማብራሪያ የታገዘ ትርጉምና ትንተና

# (Reception of Ethiopic Enoch in Gə‘əz Literature: Annotated Translation and Textual Analysis)

ኃይለ ኢየሱስ አለባቸው ሞላው[1]

## ABSTRACT

The book of Enoch is one of the ancient compositions, which exists centuries before the birth of Christ and preserved only in Gə‘əz language while it has been lost, for over 2,000 years in the world. Currently, Scholars of philology, ancient history, and Second Temple Judaism, and the Origins of Christianity are interested in studying the Ethiopic Book of Enoch. However, their primary objective is not to investigate the position of Enoch in Ethiopic literatures rather to enhance their knowledge of Jewish folklore and to seek information upon the religious ideas of Judaism, especially concerning the Messiah. Above all, the Enochic scholars in the west judged the Book of Enoch as ‘book of idolatry and magical practice’.

The general objective of this study, therefore, is focused at exploring the role of 1Enoch in the production of medieval Gə‘əz texts and investigating the themes of Enochic readings by analyzing words, lines, stanzas, and paragraphs of Enochic writings which might indicate the Ethiopian socio-religious context in which the book has been transmitted and used. Hence, both prose and poetic manuscripts are consulted.

[1] ይህ ጽሑፍ ለ3ኛ ዲግሪ ማሟያ ከቀረበ የምርምር ሥራ ተቀንጭቦ የተወሰደ ነው፡፡ Haileyesus Alebachew Molaw (PhD), Samara University, Addis Ababa, Ethiopia haileeoc@gmail.com

Then, the quotations from Ethiopic Enoch explained in the light of the Book of Enoch accompanied by other liturgical and historical writings and annotated translations.

The result showed that the Book of Enoch was frequently referred and used as a source of Gəʿəz literatures like in Mäṣəḥäfä Məśṭir, Mäṣḥäfä Bahərəy, Mäṣḥäfä Bərhan, Mäṣḥäfä ṣäḥäy, Mäṣḥäfä Säʿatat, Dərsanä ʼUra ʼel, Mäṣḥäfä Sənkəsar, ʼÄrke, Mälkkəʼä Gubae and Qəne collections. The study, in general, showed that the fact that the presence of Ethiopic Book of Enoch in the Gəʿəz literature and the Book of Enoch itself doesn't have to do with idolatry and magical practice. Rather, in the post- Enochic literature we find the manifestation of refined theological points of view about Trinity, Christology and Mariology.

*Keywords: Reception, Ethiopic Enoch, Gəʿəz Literature,*

# ፩. መግቢያ

መጽሐፈ ሄኖክ፦ ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዓለም ካበረከተቻቸው ቅርሶችና በመላው የዓለም ፈላስፎችና ምሁራን ዘንድ ከምትታወቅባቸው መገለጫዎቿ አንዱ ነው፡፡ ይኽ ታላቅና ብርቅየ መጽሐፍ በመላው ዓለም ከኹለት ሺሕ ዓመታት በላይ ዱካው በጠፋበት ዘመን በሀገራችን ግን በግዕዝ ቋንቋ ተተርጉሞ ሊቃውንቶቻችን ሲያነቡት፣ሲያጠኑት፣ሲማሩበት፣ ሲያስተምሩበትና ሲመራመሩበት ኑረዋል፡፡ ምዕራቡ ዓለም ግን ለብዙ ምዕት ዓመታት መጽሐፉን ማግኘትና ማጥናት አቅቶት ኖሮአል፡፡ በግሪክ ወይም በዕርዕ ቋንቋ ከተላለፈው የመጽሐፈ ሄኖክ ክፍል (20 በመቶ የኽል) በስተቀር[2]፣ ከመጽሐፈ ሄኖክ የተወሰዱ አጫጭር ጥቅሶችን ከማንበብ ውጭ ምዕራባውያን መጽሐፈ ሄኖክን የማንበብም ኾነ የማጥናት እድል በምልአት አላገኙም ነበር፡፡ ምንም እንኳ ያገኙት መረጃ ትክክለኛ ባይሆንም የመጽሐፈ ሄኖክን በኢትዮጵያ መኖር ለመጀመሪያ ጊዜ ፍንጭ ያገኙት በ17ኛው መቶ ክ.ዘ የመጀመሪያው አጋማሽ አካባቢ ነበር፡፡ ይኽውም በግብፅ ይኖር የነበረ ጊለስ ዲ ሎቼስ (Gilles de Loches) የተባለ የካፑቹን (Capuchin) ካቶሊካዊ መነኩሴ የሄኖክን ብራና (የግዕዙን ቅጂ) እንዳገኘው የሚገልጽ ድብዳቤ ጽፎ በ1633 እ.ኤ.አ ኒኮላስ-ክላውዴ ፋብሪ ዲ ፔሪስክ (Nicolas-Claude Fabri de Peiresc) ለታባለ ፈረንሳዊ ምሁር በመላኩ ነበር፡፡ ምሁሩም በጣም ከመደሰቱ የተነሳ በከፍተኛ ዋጋ ገዝቶ በ1636 እ.ኤ.አ በእጁ ካስገባ በኋላ ለመተርጎም ቢያስብም ከሽጠለት መነኩሴ ይኹንታን ባለማኘቱ ትክክለኛውን መጽሐፈ ሄኖክ እንዳገኘ በማሰብ እውነታውን ሳይረዳ ሞት ቀደመው፡፡ ከዚያም በ1681 እ.ኤ.አ ሂዮብ ሉዶልፍ (Hiob Ludolf) የተባለ ምሁር የተገኘው ብራና ራሱ መጽሐፈ ሄኖክ ሳይኾን ከመጽሐፈ ሄኖክ ጥቅስን የያዘ መጽሐፈ ምሥጢረ ሰማይ ወምድር የሚባል መኾኑን አረጋገጠላቸው፡፡[3] ምዕራባውያን ትክክለኛወንና ሙሉውን መጽሐፈ ሄኖክ አግኝተው ማጥናት የሚችሉበት አጋጣሚ የተፈጠረላቸው በ18ኛው ምዕተ ዓመት መዝጊያ ገደማ ግድም ላይ ነው፡፡

ይኽውም በ1773 እ.ኤ.አ ጄምስ ብሩስ የተባለው የስኮትላንድ ተወላጅ 3 የመጽሐፈ ሄኖክ ብራናዎችን ወደ አውሮጳ በማስገባቱ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለብዙ ምዕት ዓመታት በኢትዮጵያ ብቻ ሲነበብና ሲጠና የቆየው መጽሐፍ በምዕራባውያንም ዘንድ ከፍተኛ ትኩረትን በመሳብ የመጠናት እድል አጋጠመው፡፡ ይኽንንም እውን ለማድረግ

[2] Abba Daniel Assefa, (2006) "Enochic Studies in our Time", Paper Presented at Addis Ababa University, Addis Ababa

[3] Ted M. Erho and Loren T. Stuckenbruck, "A Manuscript History of Ethiopic Enoch" *Journal for the study of thePseudepigrapha*, 2013,Vol 23, no.2

ምዕራባውያን መጽሐፉን ከግዕዝ ወደ እንግሊዘኛ፣ወደ ጀርመንኛና ወደ ፈረንሳይኛ፣ወደ ዕብራይስጥም ተረጉሙት። በአኹኑ ሰዓት በብዙየአውሮጳ ቋንቋዎች ተተርጕሞ ይገኛል።[4]

መጽሐፈ ሄኖክ ወደ አውሮጳ ከገባ በኋላ ለዘመናዊ ጥናት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው ጀርመናዊው ኦገስት ዲልማን (August *Dillmann*) ነበር። ዲልማን አምስት የግዕዝ ብራናዎችን ከማነጻጸሩም[5] በላይ እጅግ የሚጠቅም ትርጕምም አሳትሞአል። ከዲልማን በኋላ የመጡ ሊቃውንትም የጥንት ጽሑፎችን ሲያጠኑ በመጽሐፈ ሄኖክ ላይም ምርምራቸውን ቀጥለው ነበር።

# ፪. በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ የተደረጉ ምርምሮችና ውጤቶች አጭር ቅኝት

ከላይ እንደተጠቀሰው መጽሐፈ ሄኖክ ከግዕዝ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ከመተርጎሙ ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ በአሜሪካ፣ በአውሮፓና በእስራኤል የሚገኙ ታላላቅ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክን ዘርፈ ብዙ በኾነ መንገድ ያጠኑታል፤ ጉባኤም ዘርግተው ይወያዩበታል። የሚሰጡት ትኩረት ከምን ጊዜውም በላይ ከመጨመሩ የተነሣ ከ60 የማያንሡ ሊቃውንት በሄኖክ ስም በየኹለት ዓመቱ እየተሰበሰቡ በአውሮጳ ሲወያዩ፣ እንዲኹም ቁጥራቸው በርካታ የኾነ የድኅረ ምረቃ ተማሪዎችም በመጽሐፈ ሄኖክ

[4] መጽሐፈ ሄኖክ ከግዕዝ ወደ እንግሊዘኛ በተለያዩ ግለሰቦች ተተርጕሟል። ከነዚኽ ሥራዎች ውስጥ በ15ኛ ክፍለ ዘመን ብራና ላይ የተመሠረተውና በፕሮፌሰር ኤፍርም ይስሐቅ የተዘጋጀውን ትርጕም መጥቀስ እንችላለን፣ E. Isaac, « 1 (Ethiopic Apocalypse of) Enoch. A New Translation and Introduction », The Old Tesament Pseudepigrapha Vol. 1 (J. H. Charlesworth ed.), DoubleDay, 1983. በ20ያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ መጽሐፈ ሄኖክ በአማርኛም ታትሞአል። መጽሐፉም እንደ ግዕዙ በ108 ምዕራፎች ሳይኾን በ42 ምዕራፎች ተከፍሎአል። እርግጥ የአንድምታው ትርጕም መጽሐፈ ሄኖክ በ19ኛው ክፍለ ዘመንም ኾነ ከዚያም በፊት ወደ አማርኛ እንደተመለሰ ያመለክታል (Daniel Assefa 2006)።

[5] ይኽ በጥንታውያን ጽሑፎች የጥናት ዘርፍ ውስጥ *critical edition* ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ከዓላማውም አንዳንዶቹን ብንጠቅስ፣ በብራናዎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች መመርመር፣ ብራናዎችን ማዋገን፣ ታሪካቸውን ማጥናት፣ እንዲሁም የንባብ ቅደም ተከተልን በማውጣት የልዩነቶችን መንሥኤ ለማወቅ መሞከር ይገኙበታል (Daniel Assefa 2006)። ከዲልማን በኋላ ቻርልስ (እንግሊዛዊ) ብራናዎችን በማነጻጸር በተሻለ መልኩ ሒሳዊ ዕትም (*critical edition*) አዘጋጅቷል። Charles, R. H., *The Ethiopic Version of the Book of Enoch : Edited from Twenty-Three Mss. Together with the Fragmentary Greek and Latin Vesions*, Anecdota Oxoniensia, Semitic Series 11 ; Oxford, Clarendon, 1906. )። ኒብ ድግሞ ጥንታዊ ባልኾነ በአንድ ብራና ላይ የተመሠረተ ዕትም ማዘጋጀቱ ይታወሳል፣( M. A. Knibb, *The Ethiopic Book of Enoch : A New Edition in the Light of the AramaicDead Sea Fragments* (2 vols.), Oxford, Clarendon, 1978)። በአኹኑ ሰዓት የሚገኙት የመጽሐፈ ሄኖክ ብራናዎች ቍጥራቸው እጅግ ስለጨመረ ሊቃውንት አዲስ ሒሳዊ እትም እንደ ሚያስፈልግ ይጠቁማሉ (ዝኒ ከማሁ)።

ጥናት ዙሪያ በየኹለት ዓመቱ በአሜሪካ እንደሚሰበሰቡና መጽሐፉ በምልዓት ተጠብቆ የሚገኘውና የተላለፈው በግዕዝ ቋንቋ በመኾኑ ለጥናታቸው ጥራት ሲሉም ብዙ የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች የግዕዝ ቋንቋን እንደሚያጠኑ አባ ዳንኤል አሰፋ (2006) ያስረዳሉ፡፡

በአይሁድ ሃይማኖት ላይ ማለትም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ (ቅ.ል.ክ) ከ3ኛው ክፍለ ዘመን አንሥቶ እስከ ክርስትና ሃይማኖት መነሻ ድረስ የነበረውን የአይሁድ እምነት፣ ባህልና ታሪክ የሚያጠኑ ሊቃውንት ለመጽሐፈ ሄኖክ ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ፡፡እንዲኹም አያሌ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማለትም በሐዋርያትና ድኅረ ሐዋርያት በተነሡ አበው ክታቦች ውስጥ እንዴት እንደ ተጠቀሰ፣በሌሎች ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ መዛግብት ውስጥ ያለውን ቦታ እና የጥንት ቋንቋዎችን፣ጥንታዊ የሥነ ፈለክ ወይም ሥነ ከዋክብት (አስትሮኖሚን) እና የመሳሰሉትን ፍሬ ነገሮች ለማጥናት ያለውን ፋይዳ የሚጠቁሙ ምርምሮችን ማካኼድና በሄኖክ ስም በሚጠራ መጽሔት ማሳተም ከጀመሩም ውለው ማደራቸውን ዳንኤል አሰፋ (2006) አብራርተዋል፡፡

ሐዋርያው ይሁዳ "ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የኾነ ሄኖክ እነሆ ጌታ በኹሉ ላይ ሊፈርድ ይመጣል... ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚኽ ደግሞ ትንቢት ተናገረ" (1፣14) በማለት የገለጸው መጽሐፈ ሄኖክ በዘመነ ሐዋርያት የነበረውን የከበሬታ ቦታ በግልጽ ያመለክታል፡፡

እንዲኹም ብዙ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን አስመልክቶ "ወልደ እጓለእመሕያው/ የሰው ልጅ" በሚለው አገላለጽ ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ጥናታዊ ግምታቸውን አስቀምጠዋል[6]፡፡ በጥንት ቤተ ክርስቲያን አበው ዘንድም ትልቅ ስፍራ እንደነበረው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ በኒክልስበርግ (Nickelsburg 2001) እንደተገለጸው ቀሌምንጦስ ዘሮም፣ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ፣ ጠርጡሊስ (Tertullian)፣ አርጌንስ (Origen) እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡[7]

## ፫. ማን ጻፈው?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የሐዋርያውን የይሁዳን ምስክርነትና የሐዋርያውያን አበውን ትምህርትና ጽሑፎች መሠረት አድርገው መጽሐፉ የተጻፈው የአዳም ሰባተኛ ትውልድ በኾነው በነቢዩ ሄኖክ መኾኑን አምነው ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ አንዱ ቆጥረው ተቀብለውታል፡፡ ምዕራባውያን ያላቸው ምልከታ

---

[6] G. Boccaccini (ed.), Enoch and the Messiah Son of Man, Revisiting the Book of Parables, Grand Rapids, Eerdmans,2007. G. W. E, Nickelsburg, A Commentary on the Book of 1 Enoch, chapters 1–36 ; 81–108, Minneapolis, Fortress Press, 2001, 83-86. (በአባ ዳንኤል 2006 እንደተጠቀሰው)፡፡

[7] መጽሐፈ ሄኖክን በጽሑፎቻቸው ውስጥ የሚጠቅሱ የጥንት አባቶችንና ምሁራንን ስም በዝርዝር ለማወቅ በ Nickelsburg2001, 87-100 የተብራራውን መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

ግን ከዚኽ የተለየ ነው። የእነርሱ መላምት (Hypothesis) መጽሐፉ በተለያየ ዘመን የተጻፉ አምስት መጻሕፍቶችን አንድ ላይ የያዘ ሲኾን ጊዜውም ቅ.ል.ክ 300 ዓመት ጀምሮ እስከ 165 ቅ.ል.ክ እንደኾነ ያስባሉ[8]። ማን ጻፈው? ለሚለውም ያስቀመጡት መላምት የተለያየ ነው። የተወሰነውን ክፍል በሙት ባሕር አካባቢ ኩምራን(Qumran) በሚባል ቦታ ይኖሩ የነበሩ የኩምራን ማኅበረ-ሰብ (Qumran community) ኢሴኔ ወይንም ሀሲዲያን (Essene or Hasideans)[9] የሚባሉ ማኅበረ-ሰብ (community) ወይንም ደግሞ የእነርሱ ቅድመ አያቶች ሊኾኑ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ (Nickelsburg 2001፡65)። አንዳንዶቹ አጥኚዎች መጽሐፈ ሄኖክ በከፊል ጥንታዊ እንዳልኾነና ክርስቲያኖችም እንደጻፉት የተረዱና ለማስረዳትም የሞከሩ ነበሩ (J. T, Milik 1976)[10]። ይኹን እንጂ ይኽ አቋም በአኹኑ ወቅት ተቀባይነትን አጥቶአል። ምክንያቱም የዛሬ 71 ዓመት አካባቢ በኩምራን ዋሻዎች የተገኙ የብራና ጥቅሎች (Qumran Scrolls) ከ2000 ዓመታት በላይ እድሜን ያስቆጠሩ በመኾናቸውና የመጽሐፈ ሄኖክን ጥቅሶች ይዘው በመገኘታቸው መጽሐፉ በሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት አለመጻፉን አረጋግጠዋል። የጥቅሎቹም መገኘት የመጽሐፈ ሄኖክን ጥንታዊነት ከማረጋገጥ ባሻገር በዕብራይስጥና በአራማይክ የተጻፉ አያሌ መጻሕፍትንም ለዓለም በማስተዋወቅ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ኾኖም፣ በዚኽ ግኝት ሊቃውንቱ እጅጉን ቢደሰቱም በኩምራን የተገኘው የመጽሐፈ ሄኖክ ብራና በፈለጉት መጠን ሊያሠራቸው አልቻለም (አባ ዳንኤል 2006)። የተገኘው የመጽሐፈ ሄኖክ ብራና ከግዕዙ ብራና ዘር (ንባብ) ጋር ሲነጻጸር ከጽሑፉ 5 በመቶ ብቻ ነበር ይዞ የተገኘው[11]።

---

8 መጻሕፍቶቹንም ፡-ስለ ረዓይት የሚናገረውን ክፍል the Book of the Watchers (1 Enoch 1–36)፣ በምሳሌ የሚናገረውን ክፍል the Book of Parables of Enoch (1 Enoch 37–71)፣ ስለ ሚጠተ ብርሃናት የሚናገረውን the Astronomical Book or Book of Luminaries (1Enoch 72–82)፣ የራዕዩን ክፍል the Book of Dreams (1Enoch 83–90), እና የመልእክቱን ክፍል the Epistle of Enoch (1Enoch 91–108) በማለት ፈርጀውታል (Nickelsburg 2001)። በዚኽ ጥናት ውስጥ ከመጽሐፈ ሄሔኖክየተጠቀሱት ምዕራፍና ቁጥሮች መሠረት ያደረጉት የግዕዙን መጽሐፈ ሄኖክ አከፋፈል ነው። ግዕዙ በ108 ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲኾን አማርኛውና አንድምታ ትርጓሜው 42 ምዕራፎች አሉት።

9 እነዚኽ ሰዎች በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ከሚሰጠው መመርያ በማፈንገጥ በይሁዳ መቃቢስ (Judas Maccabeus) መሪነት የራሳቸውን መንገድ የመረጡ የአይሁድ እምነት ተከታዮች አንደኾኑ ይገመታል።

10 ይህንን አቋም በአንክሮ ያቀረበው የፖላንድ አገር ተወላጅ የነበረው ሚሊክ ነው (J. T, Milik, *The Books of Enoch : AramaicFragments of Qumrân Cave 4*, Oxford, Clarendon, 1976)። እርሱም በዚኽ መላምቱና፣ለግዕዙ ዘርዕ/ ንባብ ይሰጥ
በነበረው ዝቅተኛ ግምቱ ከሊቃውንት ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ደርሶበታል (አባ ዳንኤል 2006)።

11 ይኽንን የመቶኛ ንጽጽር(Proportion) ያሰሉት ኡሌንዶርፍ እና ኒብ (Ullendorff and Knibb 1977:601) ሲኾኑ መነሻቸውም ሚልክ (Milik) የተባለው አጥኚ በዋሻዎቹ ውስጥ የተገኙትን አረማይክ ብራናዎች ከግዕዙ ቅጅ እና ከዚኽም ከዛም ከሰባበሰበው ከግሪኩ ቅጅ ጋር በማነጻጸር ያገኘውን ውጤት እንደገና በ "በሳል ቅኝት" (critical review) ማየት ነበር። የእርሱ ሥራ ከግዕዙ ይልቅ ለግሪኩ ቋንቋ ያደላ ስለነበር ግኝቱን የደመደመው "for the first book ofEnoch, the Book of Watchers, we can calculate that exactly 50 per cent of the text is covered by the Aramaicfragments; for the third, the Astronomical Book, 30 per cent; for the fourth, the Book of Dreams, 26 per cent; for the fifth, the Epistle of Enoch, 18 per cent" (Milik

# ፬. መጽሐፈ ሄኖክ "ከቅዱሳት መጻሕፍት ዓለም" ለምን ተገፉ?

መጽሐፈ ሄኖክ ምንም እንኳ በጥንታውያን አይሁዶችም ኾነ በጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዘንድ ታላቅ ከበሬታና በሰፊው የመነበብ እድል የነበረው ቢኾንም አኹን ግን በአይሁዶች ቤተ እምነትም ይኹን በምዕራብና ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተገፍቶ የመውጣትና ከቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር ውጭ የመኾን እድል ገጥሞታል፡፡ ይኽም በዘርፉ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን ትኩረት መሳቡና ለምን የሚለውን ጥያቄ ማስነሣቱ አልቀረም፡፡በጥናታቸውም ያመለከቱት በተለያዩ ምክንያቶችና በኺደት (gradual) እንጂ ቅጽበታዊና አሐዳዊ በኾነ ምክንያት አልነበረም፡፡ ብሩክ አየለ[12] (2015፡134) በዚኽ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችን በማሰባሰብ የሚከተሉትን ምክንያቶች አስቀምጧል፡፡ ለምሳሌ ከዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና (from canon of the Hebrew Bible) እንዲወጣና እንደ ባእድ እንዲቈጠር ካደረጉት ምክንያቶች ዋና ምክንያት ተብሎ የሚታሰበው በምኩራቡ አካባቢ ያሉ ረበናት (rabbis) በተባሉ የካህናት ወገን (Priestly groups) እና ኢሴኔ ወይንም ሀሲዲክ (Essene, or Hasidic) በተባሉት ቡድኖች መካከል የተፈጠረው መለያየትና አለመግባባትን ተከትሎ የመጣ ሲኾን ይኽውም መጽሐፈ ሄኖክ በሀሲዲዎች ዘንድ ተቀባይነት ስላለውና እንዲኹም የተጻፈው በእነርሱ እንደኾነ ረበናት(rabbis) ስለሚያምኑ ከሙሴና ከነቢያት መጻሕፍት ጋር እንዳይቈጠርና ቦታ እንዳይኖረው ወስነዋል[13]፡፡ እንደ ኹለተኛ ምክንያት የሚወሰደውም መጽሐፈ ሄኖክ የተጻፈው አምስቱ መጻሕፍተ ሙሴን (Torah) በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ እንደ ምስክር (reference) በመጥቀስ ሳይኾን በራሱ እውነት (self-assertion) ላይ ተመሥርቶ በመኾኑ ይኽም የሙሴን ሕግ እንዳለመቀበል ወይንም እንደመካድ ስለተቈጠረበት ነው ("...Enochism was condemned because of its lack of belief in Moses' torah''[14]:: ሦስተኛም በመጽሐፈ ሄኖክ ውስጥ ስለ ወደቁት መላእክት (Fallen angels) የተጠቀሰው በዘፍጥረት 6፥2-4 ላይ እንደተገለጸው "የእግዚአብሔር ልጆች" (Sons of God) መባል ሲኖርበት መላእክት ስለሚል ነገረ ሃይማኖትን (Theology) እንደሚያፋልስ በማሰብ አይሁድ መጽሐፈ ሄኖክን

---

1976:5) በማለት ነበር፡፡ (Milik, Jozéf T. 1976, The Books of Enoch: Aramaic Fragments of Qumran Cave 4, Oxford: Clarendon).

12 Bruk Ayele. "*1 Enoch* in *Jude* and in the EOTC "Canon": Developing an Adequate Insight in Second Temple Literature (STL) in the Various Ethiopian Churches for a Better Understanding of Each Other and for the Promotion of Ecumenism and Mutual Cooperation"(PhD Thesis: University of Kwazulu-Natal,2015).

13 ይኽም የኾነው ድ/ል/ክ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት አካባቢ ላይ ነው፤ በጊዜውም የአይሁድን እምነት ማእከል ይዘው ይመሩና ይወስኑ የነበሩት ረበናት ስለነበሩ መጽሐፈ ሄኖክን (ተቃዋሚዎቻቸው የሚቀበሉትን) ከእነርሱ የቀኖና መጻሕፍት ለማስወጣት መወሰን አይከብዳቸውም፡፡

14 ይኽ አይነት አስተሳሰብ የተፈጠረባቸው መጽሐፉን የጻፈው ነቢዩ ሄኖክ መኾኑን ስለማያምኑና ስለማይቀበሉ ነው፡፡

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር ውጭ አድርገውታል፡፡[15]

ከምዕራብና ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት (Western and Eastern Churches) በኩልም በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ ሒሶች፣ጥያቄዎች እና ነቀፌታዎች መነሣት የጀመሩት በ3ኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ነው፡፡ ከመጽሐፈ ሄኖክ ፊታቸውን ለማዞር በቀዳሚነት የሚጠቀሱትም ጠርጡለስ[16] እና አርጌንስ (Tertullian and Origen) ሲኾኑ ከእነርሱ በኋላም ከፍተኛ ትቺትና ተጽዕኖ በማሳደር የሚታወቀው አው ግስቲኖስ (Augustine of Hippo) ነው፡፡ የሒሳቸው ዋና ማጠንጠኛም መላእክት በሥጋዊ ፍትወት የወደቁ ኾነው በመጽሐፉ መገለጡ ነው፡፡ ከዚኽ በተጨማሪም መጽሐፉን ከጥንቆላና ከነገረ አጋንንት ጋር አያይዘው ስለሚፈርጁት ነው፡፡ የመጽሐፈ ሄኖክ ጥናት ውጤቶች ከሚጠቁሟቸው ነጥቦች መካከል ሌላው ጉዳይ ይኽ መጽሐፍ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት መጣ? እንዴት ሊስፋፋና የክብር ቦታን ሊያገኝ ቻለ? የሚለው ነው፡፡፡ ይኽን በተመለከተ ምንም እንኳ እርግጠኛ እና ግልጽ የኾነ ማስረጃ ማግኘት ባይችልም ኒከልስበርግ (Nickelsburg 2001) የሚከተሉትን መላምቶች አስቀምጧል፡፡ አንደኛ በ4ኛው መ.ክ.ዘ መጽሐፈ ሄኖክ በግብፅ በከፍተኛ ደረጃ የሚታወቅና የተስፋፋ የነበረ መኾኑን በመጥቀስ በዘመኑ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሹመው ከግብፅ የሚላኩ ጳጳሳት ይዘውት ሊመጡ እንደቻሉ ይገምታል (...the close ties between the Ethiopian Church and the patriarchate in Alexandria and the book's widespread and long-standing use in Egypt would have been a factor in the book's importation into Ethiopia)፡፡[17] ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላም መጽሐፉ እንዴት ተቀባይነትን እንዳገኘና ሊስፋፋ የቻለበትን ምክንያት ኒከልስበርግ ሊያስረዳ የሞከረው የመጽሐፈ ሄኖክን ይዘት ከኢትዮጵያ መልክአ ምድራዊና ሥርዓተ አምልኮ ጋር በማያያዝ ነው፡ እንደእርሱ መላምት መጽሐፈ ሄኖክ ስለ ልዩ ልዩ ተራሮች፣ ኮረብቶችና ሸለቆዎች ስለሚናገር ኢትዮጵያ ደግሞ የእነዚኽ መልክአ ምድሮች ባለቤት ስለኾነች መጽሐፉ በቀላሉ ተቀባይነትን አግኝቶ ሊስፋፋ መቻሉን ይጠቁማል፡፡ ይኸውም መጽሐፉን የሚያነቡት (ኢትዮጵያውያን) ከሚያውቁት ከሀገራቸው መልክአ ምድር ጋር ተዛምዶ ስላገኙት በቀላሉ

15 ምክንያት ለማብዛት እንጂ የመጽሐፉን አስፈላጊነት ቢያምኑበት የኢ/ኦ/ተ/ዋ/ቤተ ክርስቲያን በአንድምታ እንደምታትተው የወደቁት መላእክት(Fallen angels) የሚ.ለውን ደቂቀ ሴት ብሎ መተርጎምና መጽሐፉን መቀበል ይቀልነበር፡፡

16 ጠርጡለስ ምንም እንኳ በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ ጥያቄ ቢያነሣም ልክ እንደ ሐዋርያው ይሁዳ ሄኖክን ከነቢያት እንደ አንዱ የሚቀበልና መጽሐፈ ሄኖክም በነቢዩ ሄኖክ እንደ ተጻፈ የሚቀበል መኾኑን ኒከልስ በርግ ጽፏል (Nickelsburg (2001:89) ፡፡

17 እዚኽ ላይ አንባቢ ሊያነሣው የሚገባ ጥያቄ በ4ኛው መ.ክ.ዘ. መጽሐፈ ሄኖክ በግብፅ በከፍተኛ ደራጃ የተስፋፋና የሚታወቅ ከነበረ የመጽሐፉ ቅጅ (Copy) ወይንም ደግሞ አሻራው በዘመናዊቷ ግብጽ እንዴት ሊገኝ አልቻለም? ኒከልስበርግ ራሱ እንደሰጠን መረጃ ከኾነ በኮፕት ቤተ ክርስቲያን የአንድ መነኩሴ መካነ መቃብር (ከ8ኛው-12ኛው መ.ክ.ዘ እንደ ነበረ የሚገመት መቃብር) ውስጥ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ የጴጥሮስ ወንጌል (Gospel of Peter) ከተባለ ከአንድ ቁንጽል (ጎደሎ) የብራና ጥቅል ጋር ከተገኘው የመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ ወይንም ጥቅስ እና ከቀደምት አሌክሳንደራውያን (Alexandrian) ሊቃውንት ጽሑፎች ላይ ከተገኙት አንዳንድ ጥቅሶች በቀር ወጥና ምሉዕ የኾነ መጽሐፈ ሄኖክ አልተገኘም፡፡

ተረዱትና ወደዱት ማለቱ ይመስላል፡፡ በተጨማሪም እንደ ኒከልስበርግ አረዳድ መጽሐፈ ሄኖክ ስለ ልዩ ልዩ ዕፅዋትና እንስሳት ስለሚገልጽ ኢትዮጵያ ደግሞ የተለያዩ ብርቅየ እንስሳትና የዕፅዋት ዓይነቶች የሚገኙባት ሀገር በመኾኗ መጽሐፉ ተቀባይነት እንዲያገኝ ምቹ ኹኔታን እንደፈጠረ ይገምታል፡፡ በተጨማሪም በኒክልስበርግ (እንዲኹም በሌሎች) ዘንድ መጽሐፈ ሄኖክ እንደ መጽሐፈ ጥንቆላ (Magical Book) እና አምልኮተ አጋንንትን (demonolatry) የሚያስተምር ተደርጎ ስለሚቈጠር በእነርሱ አመለካከት ኢትዮጵያ እስከ 5/6ኛው መ.ክ.ዘ.[18] በአምልኮ ጣዖትና በክፉዎች መናፍስት (evil spirits) ቁጥጥር ውስጥ እንደነበረች ስለሚያምኑ ለመጽሐፈ ሄኖክ በኢትዮጵያ የክብር ቦታ አግኝቶና ተጠብቆ ለመኖሩ እንደ ምክንያት ተወስዷል፡፡በመጨረሻም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መጽሐፈ ሄኖክን ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደ አንዱ አድርጋ የተቀበለችው እንደ አውሮፓውያን ሊቃውንት መጻሕፍትን መርምሮ ሃይማኖታዊ የኾኑትንና ያልኾኑትን ለይቶ ማወቅ የሚያስችል የትምህርተ ሃይማኖት ብቃት ስላልነበራት ነው በማለት ኒከልስበርግ ይደመድማል[19]፡፡

---

[18] አብዛኛዎቹ ምዕራባውያን አጥኝዎችና የእነርሱ ተጽዕኖ ያደረባቸው አንዳንድ የሀገር ውስጥ ጸሓፊዎች ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በ4ኛው መ.ክ.ዘ እንደኾነና ከዚያ ቀድሞ በነበረው ዘመን ግን ጣዖት ስታመልክ የኖረች አድርገው የሚጽፉ ሲኾን ኒከልስበርግ ደግሞ ይኽም አልበቃው ብሎ ክርስትና ከተቀበለች በኋላም እስከ 6ኛው መ.ክ.ዘ በመናፍስትና ጣዖት አምልኮ ውስጥ እንደ ነበረች ለመግለጽ ሞክሯል፡፡ ይኹን እንጂ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ምሁራን የሚያስረዱት ሀገሪቱ ቀድሞ በሕገ ልቡና ከዚያም በሕገ ኦሪት ስትመራ የኖረችና በኋላም በ34 ዓመተ ምሕረት የክርስትና ሃይማኖትን ተቀብላ በሐዲስ ኪዳን የምትመራ መኾኗን ሲኾን 4ኛው መ.ክ.ዘ ክርስትና የተጠናከረበትና መንግሥታዊ ሃይማኖት (State religion) ለመኾን የደረሰበት ዘመን እንደኾነ ያስረዳለሁ፡፡(Lule Melaku, Histroy of Ethiopian Orthodox Church (2008: 63).

[19] *the book's acceptance was affected by elements and conditions indigenous to Ethiopia and Ethiopian Christianity.... The story of the watchers' breeding a world of demons, which still prey on humanity, resonated in an environment where demons and spirits were part of one's understanding of everyday life. The book's developed angelology, with its plethora of heavenly intercessors and guardian spirits, was also compatible with such a worldview.*

*... The book's portrayal of angels binding evil spirits (10:4–5, 11) and the inclusion of a text like 69:4–5 were compatible with magical practice, and magic spells were in fact identified with Enochic revelation. 1 Enoch's focus on the created world, its sacred cosmology and geography and its flora and fauna, may have contributed to the book's popularity and helped it to exude a sense of familiarity. In a country of deep ravines and high mountain peaks—some of them sacred—the story of the watchers' descent onto Hermon (chap. 6) and the accounts of Enoch's journeys to the great mountain ranges of the west and east and the valleys of punishment would have led the reader's imagination through familiar terrain. Enoch's journeys through the spice orchards to the great tree of paradise would have resonated in a world where groves of trees were sacred. Many of the wild animals that preyed on the Israelite sheep that populate Enoch's second dream vision were part of the everyday experience of many Ethiopians....In short, 1 Enoch took root in Ethiopia because: (a) it was brought there by missionaries who came from an environment that had long cherished the book; (b) its worldview spoke to the Ethiopians' worldview, and the environment it imaginatively portrayed resonated with their environment; and (c) Ethiopian Christianity lacked the theological and intellectual counterforces that led to the book's rejection in Mediterranean Christianity.*

ኒከልስበርግ ምንም እንኳ መጽሐፈ ሄኖክን ለ50 ዓመታት ያክል በማጥናት(እርሱ እንደ ነገረን) ብዙ ትሩፋቶች ቢለግሰንም ከላይ ላስቀመጣቸው የተሳሳቱ መላምቶች ግን ሊተች ይገባዋል፡፡ የኒከልስበርግ መላምቶች አሳማኝነት የሚጎላቸውና ከጥያቄ ሊያመልጡ የማይችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ እርሱ እንዳለው መጽሐፈ ሄኖክ ባንድ መልኩ ከጥንቆላና እኩያን መናፍስት ጋር የሚያያዝ ከኾነ በሌላ መልኩ ደግሞ መጽሐፉን ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት የግብፅ ጳጳሳት ከኾኑ ጳጳሳቱ ሲያስተምሩና ሲያስፋፉ የኖሩት ጥንቆላንና ትምህርተ አጋንንትን ወይስ ትምህርተ ክርስቶስን? በተጨማሪም ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺሕ ዓመት ጀምሮ በሕገ ኦሪት ስትመራ አግዚአብሔርን ስታመልክ የኖረች ሀገር መኾኗን የሚያስረዱ ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ እሴቶች ለምሳሌ፡- ግዝረት፣ሥርዓተ-ምግብ፣ ታቦት፣ መሥዋዕተ ኦሪት የተሰዋባቸው ቦታዎችና ቅዱሳት ንዋያት ወዘተ አማናዊ ምስክር ኾነው የሚገኙባትን ሀገር ከክርስቶስ ልደት በኋላም እስከ 6ኛው መ.ክ.ዘ ጣዖትን ስታመልክ የነበረች አድርጎ ማቅረብ ምን ያህል ተአማኒነት አለው?[20]ከኹሉምበላይ አንድ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊትና አስተምህሮ ጠንቅቆ የማያውቅ ጸሓፊ መጽሐፈ ሄኖክ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካተቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ በቂ የሃይማኖት ዕውቀት ስለሚያንሳት ወይንም ስለሌላት ነው ብሎ መገመትና መጻፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የተደረገ 'ምሁራዊ ትንኮሳ' (Intellectual harassment) ከመኾነ የዘለለ ትርጉም አይሰጥም፡፡ ምክንያቱም ፍረጃው መጽሐፉን ለዘመናት ሲያነቡት ሲተረጉሙት ሲማሩትና ለሌሎች ሲያስተምሩት የኖሩትን የቀደሙትንም ኾነ ያኹኑን ዘመን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ስለሚያካትት ነው፡፡ በመኾኑም የዚኽ ጥናት ዋና ዓላማ፡- መጽሐፈ ሄኖክ በመካከለኛው ዘመን የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያለውን ቦታ ማሳየትና በይዘቱም እንደማጣቀሻ (Refference) እና ምንጭ (Source) ኾኖ ማገልገሉን በአብነት ማሳየት ነው፡፡

- በተጨማሪም ከመጽሐፈ ሄኖክ በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ በሌሎች የብራና

---

[20] በታሪክ እንደሚታወቀው በንግሥተ-ሳባ እና በንጉሥ ሰሎሞን ልጅ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት ታቦተ ጽዮንን ጨምሮ 318 ሌዋውያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፤ መጻሐፍትንም ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል (Tewodros Abraha and Seyfe Sillase Yohanns, as cited by Mersha Alehegn, *The Ethiopian Commentary on the Book of Genesis: Critical Edition and Translation.* Germany: Memminger MediemCentrum AG. (2011:2). እንዲኹም በአራቱ ማዕዘናተ ዓለም ያሉት አይሁዶች በዓልን ለማክበር በኢየሩሳሌም ይሰባበሱ እንደ ነበረ ኹሉ ኢትዮጵያውያንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ሺህ ዓመት ተመሳሳይ ሃይማኖታዊ ጉዞ ያደርጉ የነበረ ለመኾኑ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 27 ላይ የተዘገበው የኢትዮጵያው ጃንደረባ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ በመሆኑም ከዚኽ ታሪካዊ ዳራ በመነሣት መጽሐ ሔኖክ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ወይንም ደግሞ ከዚያበኋላ ባለው አንድ ሺሕ ዘመን ውስጥ ያለማቋረጥ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ በነበሩ ሃይማኖታዊ ተጓዦች ሊኾን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡

ጽሑፎች ውስጥ የተጠቀሱ ቃላትን፣ ሐረጋትን፣ ዐረፍተ ነገሮችን አንቀጾችን (paragraphs) ከተጠቀሱበት ዐውድ በመናሣት መጽሐፈ ሄኖክ በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሊቃውንት እንዴት ተነበበ? ወይንም ተተረጎመ? የሚለውን ማየትና መረዳት ነው፡፡

- እንዲኹም የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የቅኔ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክን ለቅኔ ምሥጢር ማፍለቂያነት እንዴት እንደተጠቀሙበትና በመጽሐፈ ሄኖክ የተገለጠን ሐሳብ በቅኔያቸው እንዴት እንዳንጸባረቁት ማሳየት ነው፡፡

- በመጨረሻም በሄኖካዊ የግዕዝ ጽሑፎች (Enochic Gəʽəz Literature s)[21] ውስጥ ያሉትን ምሥጢራዊ ትምህርቶች ፈልቅቆ ማውጣትና ከተለያዩ አይታዎች አንጻር ትንታኔ መስጠት ይኾናል፡፡

ከላይ የተገለጸውን የዚኽን ጥናት ዐቢይና ንዑስ ዓላማዎች ግብ ለማድረስና የጥናቱን ተግባር በተገቢው መንገድ ለማስኬድ ይቻል ዘንድ ገላጪ የጥናትና ምርምር ዘዴ ተመርጧል፡፡ ይኽ ዘዴ የተመረጠበት ዋና ምክንያት በልዩ ልዩ የጽሑፍ መዛግብት ላይ ተመርኩዞ ለሚካኼድ ጥናታዊ ሥራ ተስማሚ በመኾኑ ነው፡፡ ለዚኽ ጥናት ግብዓት የሚኾን መረጃ የተሰበሰበበት መንገድም ልዩ ልዩ ጥንታዊ የብራና ጽሑፎችን እና የትርጓሜ መጻሕፍትን በቀዳሚ የመረጃ ምንጭነት በመጠቀም ነው፡፡ በመኾኑም የዚኽ ጥናት ርእሰ ጉዳይ ከኾነው ከመጽሐፈ ሄኖክ ጋር በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ምንባባት በመውሰድ ከዋናው ምንጭ (መጽሐፈ ሄኖክ)ከየትኛው ምዕራፍና ቁጥር እንደተወሰዱና ለምን ዓላማ (ምን ለመግለጽ) እንዳገለገሉ ሰፊ ትንታኔ ቀርቧል፡፡

# ፫. የመጽሐፈ ሄኖክ አስተዋጽኦ (Role) በመካከለኛው ዘመን የግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ

የመካከለኛው ዘመን የግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ እንደገና በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋበትና አያሌ መጻሕፍት የተጻፉበት ዘመን በመኾኑ "ወርቃማው የሥነ ጽሑፍ ዘመን" ይባላል፡፡ በዚኽ ዘመን የነበሩ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክን ያነቡት፣ ያጠኑት፣ ይመረምሩትና ለድርሰቶቻቸው እንደ ምንጭ (Source) ይጠቀሙበት እንደ ነበር ለማወቅ የዘመኑን ድርሳናት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በመኾኑም መጽሐፈ ሄኖክ በልዩ ልዩ ብራናዎች ለምሳሌ በመጽሐፈ ብርሃን፣ መጽሐፈ ምሥጢር፣መጽሐፈ ባሕርይ፣መጽሐፈ ስንክሳር፣ መጽሐፈ ፀሐይ፣መጽሐፈ ሰዓታት፣ድርሳነ ዑራኤል፣አርኬ፣ መልክአ ጉባኤ፣ ነግሥ እና

[21] ከመጽሐፈ ሄኖክ ጥቅሶችን በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ ያካተቱ ጽሑፎች ሄኖካዊ ጽሑፎች ይባላሉ፡፡

በተለያዩ ቅኔዎች መጽሐፈ ሄኖክ በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ ተጠቅሶ እንደሚገኝ በዚኽ ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚኽ አጭር ጽሑፍ ኹሉንም ማቅረብ ባይቻልም ለምሳሌ ያኽል ከብራናዎቹ የተወሰዱትን የሚከተሉትን ምንባባት እንመልከት።

## ፫.፩. ሄኖክ በመጽሐፈ ብርሃን (EMML 7001)

መጽሐፈ ብርሃን በ15ኛው መ.ክ.ዘ በዓፄ ዘርዓያዕቆብ የተደረሰ ሲኾን ስያሜው እንደሚያመለክተው ብርሃን የተባለ ክርስቶስን ማእከል ያደረገና ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚያደርስ መኾኑን ጸሓፊው ይገልጻል::[22] ደራሲው ስለ መጽሐፈ ሔኖክ አስፈላጊነት በመግለጽ መጽሐፉን የሚነቅፉትን እንደሚከተለው ይሞግታል።

*ወለመጽሐፈ ሄኖክሰ ንትዌከፎ በእንተ ዘዓቀምዎ ስምዓ ሐዋርያት እንዘ ይብሉ ዘከመ ተነበየ ሄኖክ ዘውእቱ ሳብእ እመነ አዳም...ጳውሎስኒ ይቤ፡- በተአምኖ አፍለሶ ለሄኖክ ከመ ኢይርአዮ ለሞት ወኢተክበ እምድኅረ አፍለሶ እግዚአብሔር፤ እምቅድመ ፍልሰቱ ሰማዕተ ኮኖ ከመ አሥመሮ ሄኖክ ለእግዚአብሄር። ወእግዚአብሔርኒ ኮነ ስምዓ በእንቲአሁ በመጽሐፈ ኩፋሌ እንዘ ይብል ለሙሴ... ወውእቱ ቀዳሚ ጸሐፈ ስምዓ ለደቂቀ እስራኤል ውስተ ትዝምደ ሰብአ ምድር፤ ወሱባኤሆሙ ለኢዮቤልዩ ውእቱ ነገረ፤ ወመዋዕለ ዓመታት አይድዓ፤ ወዐውራኃተ ሥርዓ ወሰንበታተ ዓመታት። ወካዕበ እንዘ ያጸድቅ ነገሮ ለሄኖክ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በመጽሐፈ ኩፋሌ ወአንተኒ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ይዕቀቡ ዓመታተ በዝ ኍልቈ ፫፻ወ፷፬ (ሠለስቱ ምዕት ወስሳ ወረቡዓ) መዋዕለ*

[22] "...ሰመይናሁ ለዝንቱ ድርሳን መጽሐፈ ብርሃን ዘይምህር አምልኮቶ ለእግዚአብሔር ብርሃን...ዝንቱ ድርሳን ዘይሰመይ መጽሐፈ ብርሃን ዘበትርጓሜሁ መጽሐፈ ክርስቶስ ብርሃን እስመ ይመርሖሙ ለክርስቲያን ኀበ ርቱዓ አሚን ወያበጽሖሙ ለክርስቲያን ኃበ ክርስቶስ ብርሃን በከመ ለሊሁ በእንተ ርእሱ ይቤ አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ዘተለወኒ ኢየሐውር ውስተ ጽልመት.../ ይኽንን ድርሳን መጽሐፈ ብርሃን ብለን ሰየምነው፤ ብርሃን የተባለ እግዚአብሔርን ማምለክን ያስተምራልና። ይኽ መጽሐፈ ብርሃን የተባለ ድርሳን ትርጓሜው የብርሃን ክርስቶስ መጽሐፍ ነው፤ ክርስቲያኖችን ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት ይመራቸዋል፤ ወደ ብርሃን ክርሰቶስ ያደርሳቸዋል። እርሱ /ክርስቶስ ስለራሱ እንዲኽ እንዳለ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ፣የሚከተለኝ በጨለማ ውስጥ አይሄድም... "::

ትርጉም፡- የሄኖክን መጽሐፍ የምንቀበለው ሐዋርያት ምስክርነት ስላቆሙለት ነው። እንዲህ እያሉ። ከአዳም ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ እንደተናገረው ....። ጳውሎስም ተናግሯል። ሄኖክ ሞትን እንዳያየው በእምነት ሰወረው/አሳረገው። እግዚአብሔር ከሰወረው በኋላም አልተገኘም። ሄኖክ እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘው ከመወሰዱ በፊት ምስክር ሆነው። እግዚአብሔርም ስለ እሱ ምስክር ሆነ። በመጽሐፈ ኩፋሌለሙሴ እንዲህ አለው.... በምድር ላይ በሰው ልጅ ዝምድና ለእሥራኤል ልጆች ምስክርነት አስቀድሞ የፃፈ እሱ ነው። የኢዮቤልዩ ሱባኤያቸውን የተናገረ እሱ ነው። የዓመታትን ጊዜ የተናገረ እሱ ነው። ወሮችን፣ የዓመታትን ሰንበቶች የሠራ እሱ ነው። ዳግመኛም የሄኖክን ነገር እውነት ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር በመጽሐፈ ኩፋሌ ሙሴን አለው። አንተም የእሥራኤልን ልጆች አዘዛቸው በዚህ በ፫፻፷፬ (364) ቁጥር ዓመታትን ይጠብቁ

*ወይከውን ፍጹመ ዓመተ (cf En 74፡9-13)።*

*ርኢኬ ዘይብል ኢይትዌከፎ ለመጽሐፈ ሄኖክ ሶበ ታቀውም ሊተ ስምዓ ለዘዓቀምዎ ሐዋርያት ስምዓ በመጽሐፈ መልእክቱ ለይሁዳ እኍሁ ለያዕቆብ። ወእግዚአብሔርኒ ኮኖ ስምዓ ለመጽሐፈ ሄኖክ ወነገሮ ለሙሴ ኊልቈ መዋዕለ ዓመት። እፎኑ ይትከሀለከ ታእምር ዑደተ ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብት፤ ምልዓተ ብርሃን ወሑፃጼሁ፤ ወሥርዓተ ዓመታት ዘእንበለ ሄኖክ ። ወሐዋርያትኒ ይቤሉ በእንተ ክብረ ሄኖክ... ወእምሰ አክበርዎ ወአስተዓረይዎ ሐዋርያት በዲድስቅልያሆሙ ለመጽሐፈ ሄኖክ ምስለ መጽሐፈ ሙሴ ወኢሳይያስ ወዳዊት ወመጻሕፍተ ካልዓን አበው ቀደምት እስመ እሙንቱ ነቢያቲሁ ለእግዚአብሔር፤ በከመ ይቤሉ ሐዋርያት በዲድስቅልያሆሙ እስመ አበው ቀደምት ጥዩቀ እምንቱ አፉሁ ለእግዚአብሔር፤ ወሄኖክኒ ነቢይ እምአበው ቀደምት ውእቱኒ አፉሁ ለእግዚአብሔር። ወበእንተዝ ናፈቅሮ ወንትዌከፎ ለመጽሐፈ ሄኖክ አእሚረነ ከመ ተወክፍዎ ሐዋርያት ለስምዕ...(ff 81-83)።*

*ትርጉም፡- ተመልከት! የሄኖክን መጽሐፍ አልቀበልም የሚለውን "ሶበ ታቀውም ሊተ ስምዓ" ሐዋርያት በያዕቆብ ወንድም በይሁዳ መጽሐፈ መልእክት ምስክርነትን ላቈሙለት እግዚአብሔርም ለሄኖክ መጽሐፍ ምስክር ሆኗል። ለሙሴም የዓመታትን የጊዜ ቊጥር ነግሮታል። የፀሐይን፣ የጨረቃን እና የከዋክብትን ዙረት (ዑደት)፣ የብርሃንን መሙላት እና መጉደል፤ የዓመታትን ሥርዓት ያለ ሄኖክ ታውቅ ዘንድ እንዴት ይቻልሀል?ሐዋርያት ስለ ሄኖክ ክብር ይናገራሉ።.... ሐዋርያት በዲድስቅሊያቸው የሄኖክን መጽሐፍ ከሙሴ መጽሐፍ፣ ከዳዊት መጽሐፍ፣ ከኢሳይያስ መጽሐፍ እና የእግዚአብሔር ነብያት ተብለው ከሚጠሩ ሌሎች ቀደምት አባቶች መጽሐፍ ጋር ከአስተ ካከሉት እና ከአከበሩት፤ ሐዋርያትም በዲድስቅሊያቸው እንዳሉት የቀደሙ አባቶች የእግዚአብሔር አፍ (አንደበት) እንደሆኑ የታወቀ የተረዳ ነው። ሄኖክም እንደቀደሙት አባቶች ነብይ ነው። እሱም የእግዚአብሔር አፍ (አንደበት) ነው። ስለዚህ ሐዋርያት የሄኖክን መጽሐፍ ለምስክርነት እንደተቀበሉት አውቀን እንወደዋለን እንቀበለዋለን።*

ዘርዓ ያዕቆብ መጽሐፈ ሄኖክን መቀበል እንደሚገባ በአመክንዮ ያስረዳል። ሐዋርያት በትምህርታቸው ለምስክርነት (ለማስረጃነት) የጠቀሱት መኾኑን ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ (ቁጥር 14-15) "ዘከመ ተነበየ ሄኖክ ዘውእቱ ሳብእ እም አዳም..." ያለውን በዋቢነት ጽፏል። የነቢዩ ሄኖክንም የሃይማኖቱን ጽናት የምግባሩን ቅናት ለማስረዳት ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት (ዕብ. 11፡5) በመጥቀስ ዘርዓ ያዕቆብ ያትታል። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሄኖክ የገለጠውን ስለ ቀናት፣ ወራት፣ ዓመታት ሰንበታት (ሱባኤያት) እና ኢዮቤልዩ አቆጣጠር በኋላም ለሙሴ በድጋሚ በመጽሐፈ ኩፋሌ እንዲጽፈው ማዘዙ

የመጽሐፈ ሄኖክን አስፈላጊነት የሚመሰክር መኾኑን ዘርዓ ያዕቆብ ጽፏል፡፡ ሐዋርያት በመልእክታቸውና ዲድስቅልያ በተባለው መጽሐፋቸው ስለ መጽሐፈ ሄኖክ የሰጡትን ምስክርነት የማይቀበልን ሰው "እፎኑ ይትከሀለከ ታእምር ዑደተ ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብት፤ ምልዓተ ብርሃን ወሑፃጼሁ፤ ወሥርዓተ ዓመታት ዘእንበለ ሄኖክ.../ የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብትን ዑደት (መመላለስ) እንዴት ልታውቅ ትችላለህ? የብርሃንን መሙላትና መጉደል፣ የዓመታትን ሥርዓት (አቆጣጠር) ያለ መጽሐፈ ሄኖክ እንዴት ማወቅ ትችላለህ?..." በማለት ደራሲው ይሞግታል፡፡ በመጨረሻም ሐዋርያት መጽሐፈ ሄኖክን ከሙሴ፣ ከኢሳይያስ፣ ከዳዊት ከሌሎቹም የቀደሙ አባቶች መጻሕፍት ጋር እኩል አድርገው ከቆጠሩት፣እኛም እንወደዋለን፤ እንቀበለዋለን፤ በማለት ይደመድማል፡፡

## ፳.፪. ሄኖክ በመጽሐፈ ሙላድ (Call No. 6838)

ዘርዓ ያዕቆብ ስለ ክርስቶስ ልደት በሚያትተው በመጽሐፈ ሙላድ ድርሰቱ መጽሐፈ ሄኖክን ማጣቀሻ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ የትኛውንም ሃይማኖት የሚከተል ሰው ክርስቲያንም ይኹን አይሁዳዊ መጽሐፈ ሄኖክን ማቃለል እንደማይችል ከታች ያለው አንቀጽ ያስረዳል፡፡

> *ስማዕ ኦ ብእሲ እመኒ ኮንከ ክርስቲያናዊ ወእመኒ ኮንከ አይሁዳዊ ወኢይትከሀለከ ትትከሐዶ ለሄኖክ እስመ ውእቱ ቀደመ ተነብዮ ወእምኵሉ እለ እምዓለም ነቢያት፡፡ ወእምኵሎሙ እለ ተነበዩ ልደቶ ለክርስቶስ እማርያም ድንግል በክልኤ፡፡ ወዓዲ ጥምቀቶ...፡፡ እስመ ሄኖክ ርእየ ሙፃኣ ፀሐይ ወምዕራብ ፀሐይ ዘከመ ይሠርቅ ወየዐርብ ለለወርኁ ወለለ ዕለቱ በመሳክወ ሰማይ፡፡ በከመ ይቤ ለሊሁ፡- ወሕጸራ ለዕለት ወለሌሊት ወኑኃ ለዕለት ወለሌሊት በምሕዋረ ፀሐይ ውእቱ ይትሌለይ፡፡*

> ትርጉም፡- ሰው ሆይ ስማ! ክርስቲያን ብትሆንም አይሁድ ብትሆንም ሄኖክን ትክደው ዘንድ አይቻልህም፡፡ እሱ በዓለም ውስጥ ከነበሩ ነብያት ሁሉ፤ በኹለት ወገን ድንግል ከሆነች ከማርያም የክርስቶስን መወለድ ከተናገሩት ነብያትም ሁሉ በፊት አስቀድሞ ትንቢትን ተናግሯል፡፡ ጥምቀቱንም እንዲሁ....፡፡ ሄኖክ የፀሐይን መውጫና መግቢያ፤ ፀሐይ በየወሩ እና በየእለቱ ሲወጣና ሲገባ በሰማይ መስኮት ተመልክቷል (አይቷል) እና፡፡ እሱም እንዳለው፡- የቀኑ እና የሌሊቱ ማጠር፤ የቀኑ እና የሌሊቱ መርዘም የሚለየው (የሚታወቀው) በፀሐይ መንገድ ነው፡፡

> *ወበእንቲአሁ ይነውሕ ምሕዋሪሁ ዕለት እምዕለት ወሌሊት እምሌሊት (cf. 1En.72: 33-35)፡፡ እስመ ለፀሐይ ብዙኀ ውእቱ ኀቡአቲሁ፡፡ ወለውሉደ ምድርኒ ሄኖክ*

*ነገረ ወምሥጢራቲሃ ወሕፀፂሃ (ለወርኅ)... ወካዕበ ይቤ ሄኖክ በእንቲአሃ:- "ወበ-ኖኅት ቀዳማዊ በመዋዕል ምዕት ወሰብዓ ወሰብዓቱ ወዘመነ ዚአሁ ሙፃኡ ሠለስተ ወርኃ ያስተርኢ በበሰላሳ። ወሠለስተ ወርኃ ያስተርኢ በበዕሥራ ወተሱዐ መዋዕል:: በሌሊት ያስተርኢ በበዕሥራ ከመ ብእሲ ወመዐልተ ከመ ሰማይ እስመ ካልዕ ምንትኒ ኣልባቲ ዘእንበለ ብርሃነ ዚኣሃ" (cf. 1En. 78:15-17)። ወካዕበ አርአየ (ርእየ) ሄኖክ ሥርአታቲሆሙ ለከዋክብት እለ የዐርቡ መካናቲሆሙ ወአዝማኒሆሙ ወበዓላቲሆሙ ወበአውራኃቲሆሙ:: ወለከዋክብተ ጽባሕሂ ወለከዋክብተ ምሴት አእመረ ኅቡረ ምስሌሆሙ (cf. 1En. 82:9-11) ። ኦ ብእሲ መስተካሕድ እሎንተ ሶበ ትፈክር ትሰመይኬ ጠቢበ ወማእምረ። ስማዕ ኦ ብእሲ ዘትትከሓዶ (ዘትክሕዶ) ለሄኖክ እምአይኑ ታመጽእ ዕለታተ ሠለስተ ምእተ ወስሳ ወአርባዕተ ዕለታተ። ወዓዲ አውራኃ ዐሠርተ ወክልኤተ። ወዓዲ ካዕበ ሰብዓ ምእተ ዓመታተ ዘውእቱ ሰባቱ ስሕ ዓመታቲሁ ለእግዚአብሔር። በከመ ነገረ ሄኖክ እንዘ ይብል ከመዝ:- "ወእምድኅረ ዝንቱ በሰንበት ዐሥርት ሳብዒት ዕዳ ባቲ ኵነኔ እንተ ለዓለም ዓቢይ ዘይትቤቀል እማእከሎሙ መላእክተ ወሰማይ ቀዳማዊ ይወጽእ ወየሐልፍ። ወሰማይ ሐዲስ ይትረአይ። ወኵሎሙ ኃይለ ሰማያት ያበርሁ ለዓለም ሰብዓተ ምክዕቢተ። ወእምድኅረዝ ሰንበታት ብዙኃት እለ አልቦን ኊልቈ በዓለም በኂሩት ወበጽድቅ ይከውኑ..."(cf. 1En. 91:15-17)። ወአንተሰ አይሁዳዊ ትብልአ ከመዝ ወእምድኅረ ሰብዓቱ ሲህ ዓመታት ሀሎ ዓመታት ብዙኀ። ዘንተ ዘትትናገር ሶበ ተኃጥአ እድሜሁ ወውሳኔሁ ለትፍሥሕትከ ወሐሤትከ እስመ መዝበረ ወኃመደ ኮንከ...። (ff 4s-47) ስማዕ ኦ ብእሲ ክርስቲያናዊ ጠቢብ፣ በስመ ሥላሴ ዕቱብ፣ ልደትከኒ ክዑብ፣ አእምሮ ሃይማኖትከ ዕድው እምአብዳነ ልብ። እመሂ መጽአ ብእሲ እምሥራቅ ወእምእራብ፣ እምሰሜን ወእምደቡብ፣ወእምኵሉ ትርብዕተ ዓለም ርኂብ፣ እመሂ ጾሙ ወእመሂ ፋሲካሁ ወእመሂ በዓላቲሁ፣እመሂ በጸሐይ ወእመሂ በወርኅ ወእመሂ በኮከብ፣ዘእንበለ ሄኖክ ኢይትከሃል ኵሉ ሐሳብ። ( f 165)*

*ትርጉም፡- በእሱም የእለት ከእለት የሌሊትም ከሌሊት ጉዳናው ይረዝማል (cf.1En.72: 33-35)። የፀሐይ መሠወሪያው ብዙ ነው እና። ሄኖክ ለምድር ልጆች የጨረቃን ምስጢሮቿን፣ ጉደለቶቿን ተናገረ። ዳግመኛ ሄኖክ ስለእሷ እንዲህ አለ በመጀመሪያው ደጃፍ (በር) በ፻፹፪ ዘመን በራሱ ዘመን መውጫው ለሦስት ወሮች በ፴ በ፴ ይታያል። ለሦስት ወሮችም በ፳፱ በ፳፱ ይታያል። ሌሊት በ፳ በ፳ እንደ ሰው ይታያል። ቀን ደግሞ ሰማይ መስሎ ይታያል። ከእራሷ ብርሃን ሌላ ምንም ብርሃን የላትም እና። (cf. 1En. 78:15-17) ። ዳግመኛም ሄኖክ የከዋክብትን የሚገቡበትን ቦታ፣ የዘመናቸውን፣ የበዓላቶቻቸውን እና የወሮቻቸውን ሥርዓት አየ። የንጋት ኮኮቦችን፣ የምሽት ኮኮቦችን በአንድነት ከእነሱ ጋር አወቀ (     )። የምትክድ አንተ ሰው ሆይ! እነዚህን በተረጎምህ ጊዜ አዋቂ እና ጥበበኛ ትባላለህ። ሄኖክን የምትክደው አንተ ሰው ሆይ ስማ! ፫፻፷፬*

*(364) እለታትን ከየት ታመጣለህ? ዳግመኛም ፲፪ (12) ወሮችን፣ ሰብአ መቶ (፸፻) ዓመታትን እነሱም የእግዚአብሔር ሰባት ሺሕ ዓመታትን ከየት ታመጣለህ? ሄኖክ እንዲህ ብሎ እንደተናገረ ከዚህ በኋላ በሰባት ሺህኛውን ሰንበት እዳ አለባት መላእክትን ከመካከላቸው ለዘለዓለም የሚበቀል ታላቅ ኩነኔ አለባት። የመጀመሪያው ሰማይ ይወጣል ያልፋልም። አዲስ ሰማይ ይታያል ሁሉም የሰማያት ኃይሎች እጥፍ ይበራሉ። ከዚህ በኋላ ቍጥር የሌላቸው ብዙ ሰንበቶች በቸርነት እና በእውነት በዓለም ይሆናሉ። አንተ አይሁዳዊ እንዲህ ትላለህን? ከሰባቱ ሺህ ዓመቶች በኋላ ብዙ ዓመት አለ። ይህን ስትናገር የተድላ ደስታህን እድሜውን እና ውሳኔውን ባጣኸው ጊዜ አመድ እና ትቢያ ትሆናለህ እና (ff 4s-47)። በሥላሴ ሥም የተባረክህ፣ ሁለት ልደት ያለህ የሃይማኖት ማስተዋልህ ከሰነፎች ልብ ያለፈ አንተ ጥበበኛ ክርስቲያን ሰው ሆይ ስማ! ሰው ከምሥራቅም ኾነ ከምእራብ፣ ከሰሜንም ኾነ ከደቡብ ሰፈ ከሆነችው ዓለም ከአራቱም አቅጣጫ ቢመጣ፣ ጾሙም፣ ፋሲካውም፣ በዓላቶቹም ቢኾን፣ በፀሐይም፣ በጨረቃም፣ በከዋክብትም ቢኾን ኹሉም ሐሳብ ያለ ሄኖክ አይቻልም (f165)።*

በዚኽ አንቀጽ ዘርዓ ያዕቆብ የክርስቶስን ልደት፣ ጥምቀት… አስቀድመው ከተናሩ ነቢያት ቀዳሚው ሄኖክ መኾኑን ይጠቅሳል። የፀሐይን መውጫና መግቢያ፣በየዕለቱና በየወሩ ፀሐይ የሚወጣበትንና የሚገባበትን መስኮቶች፤የያንዳንዱ ቀንና ሌሊት መርዘምና ማጠር የሚለየው በፀሐይ መኾኑን እንዲኹም የፀሐይ መግቢያና መውጫው ብዙ መኾኑን (12 መስኮቶች እንዳሉት)፤የጨረቃንም ምሥጢር (እንዴት እንደሚወጣና እንደሚገባ፣ እንደሚጎልና እንደሚሞላ፣ብርሃኑን ከፀሐይ እንዴት እንደሚቀበል፣በቀንና በሌሊት ለሰው ልጆች እንዴት እንደሚታይ …)፤ የከዋክብትንም ሥርዓት የሚታዩበትን ወራት፣በዓላትና ዘመናት… ስለሚያስረዳ መጽሐፈ ሄኖክን ማንኛውም ሰው ከምሥራቅም ይኹን ከምዕራብ ከደቡብም ይምጣ ከሰሜን ሊቀበለው እንደሚገባ ዘርዓ ያዕቆብ ይሞግታል። የትኛውንም ሃይማኖት የሚከተል ስው፣ በፀሐይ በጨረቃም ይኹን በከዋክብት ዘመናትን ቢቆጥር፣ ጾሙና ፋሲካው በዓላቱ የሚውሉበትን ቀናት ለይቶ ለማወቅ መጽሐፈ ሄኖክ አስፈላጊ መኾኑን ደራሲው ያስረዳል።

## ፩.፫.ሄኖክ በመጽሐፈ ባሕርይ (Call No. EMML1480)

አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዚኽኛው ድርሰቱ መጽሐፈ ሄኖክን በስፋት የጠቀሰው ሲኾን ለምሳሌ ከዚኽ በታች በቀረበው አንቀጽ ጠንቋዮችንና ጥንቆላቸውን ሲቃወምበት እናነባለን።

*… ወአንትሙሰ ክርስቲያን ኢትስምዕዎ ለጠንቋሊ…እሉ እሙንቱ ጠንቋልያን ዘይቤልዎሙ ሐዋርያት በሲኖዶሶሙ አይሑድ ወመጣዐውያን ደቂቀ ትምህርቶሙ*

*ለመላእክተ ጽልመት እኩያን እለ ኀደጉ ሰማየ ልዑለ ወምቅዋመ ቅዱሰ (cf. En12:4, 15:3)፤ ወአብደሩ ከመ ያማስኑ በኵሉ ርኵሰ ዚአሆን(ሙ) ለአንስት። ወመሀሩ ለውሉደ ሰብእ ሩጸተ ፀሐይ ወወርኀ ወከዋክብተ ወኵሎ ምራያተ፤ ወኵሎ ምግባራተ ምኑናተ(cf. En8:1-4)። ያድኅነነ እግዚአብሔር እመክፈልቶሙ ለእሉ ለነ ለሕዝቡ ለአባግዐ መሬቱ፤ ወይረስየነ ናምልኮ በጽድቅ ወበርትዕ ሎቱ ለባሕቲቱ ለዓለመ ዓለም አሜን (f 57)...።*

ትርጉም፡- እናንተ ክርስቲያኖች ጠንቋይ አትስሙ።... እነዚህን ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ጠንቋይ አይሁድ፣ ምትሐተኞች፣ የተቀደሰውን መቋሚያ ሰማይ ልዑልን የተው ክፉ የኾኑ የመላእክተ ጽልመት የትምህርት ልጆች ይሏቸዋል። በሴቶቻቸው ርኩሰት ሁሉ ለማጥፋት ይቀዳደማሉ። ለሰው ልጆች የፀሐይን፣ የጨረቃን፣ የከዋክብትን ሩጫ፣ ምትሐትን ኹሉ፣ የተናቁ ምግባራትን ኹሉ ያስተምራሉ። እግዚአብሔር እኛንም መንጋውንም ከእነሱ እጣ ፈንታ ያድነን። በእውነት እና በቅንነት እንድናመልከው ያድርገን ለእሱ ለብቻው ለዓለም ዓለም አሜን።

*....ወአንተኒ ኦ ብእሲ ዘተሰመይከ ክርስቲያናዌ፤ ወእምነ ክርስቲያን ዘተሠየምከ መዘምረ፤ ... ወእምነ ጳጳስ ዘተሠየምከ ሊቀ ጳጳሳተ፤ አልቦኬ ዘየዓቢ እምዝ መዐርገ ክህነት... ወአንተሰ እምድኅረ በጻሕከ ውስተ ዝንቱ መዐርግ ክቡር አንሐልከ ኵሎ መዐርገ ክህነት፤ ወኮንከ ዕሩቀ እምጥምቀተ ክርስትናከ። ወረሰይከ ርእሰከ አይሁዳዌ ወመጠዐዌ በኀርየትከ ዕለተ እምዕለት፣ ወሰዐተ እምሰዐት፤ ወበነጽሮትከ ፀሐየ ወወርኀ ወከዋክብተ በትእምርተ እከይ በትምህርቶሙ ለመላእክተ ጽልመት እለ ወድቁ እምሰማይ ዲበ ምድር፤ ወመሀሩ ርእየተ ከዋክብት ወኵሎ ትእምርታተ እከይ። እሉ እሙንቱ በረቅያል ወኮከብኤል ወጣምኤል ወአስድረኤል አበወ ረአይት እለ ኮኑ ለከኒ አበው። በከመ ይቤ ሄኖክ ሳብዕ እምአዳም በረቅኤል መሀረ ረአይያነ ኮከብ፤ ወኮከብኤል ትእምርታተ፤ ወጠምኤል መሀረ ራእየ ኮክብ፤ ወአስድረኤል መሀረ ሩጸተ ወርኀ ለአኀጕሎተ ሰብእ....(ff. 57-58) , (cf. En8:1-4)*

*ትርጉም፡- አንተም ጥበበኛ ክርስቲያን ሰው ሆይ! ከክርስቲያንም ዘማሪ የተባልክ፣ ... ከጳጳሳትም ሊቀ ጳጳስ ተብለህ የምትጠራ ከዚህ የሚበልጥ የክህነት ማዕረግ የለም። አንተ ግን ከዚህ የከበረ የክህነት ማዕረግ ከደረስክ በኋላ ኹሉንም የክህነት ማዕረግ አፈረስክ። ከክርስትና ጥምቀትህም የተራቆትህ ኾንህ። ከሰዓት ወደ ሰዓት፣ ከእለት ወደ እለት በእራስህ ምርጫ እራስህን መጣዊ እና አይሁዳዊ አደረግህ፣ ፀሐይን፣ ጨረቃን እና ከዋክብትን የምታየው ከሰማይ ወደ ምድር በወደቁ የጨለማ መልእክተኞች ትምህርት በክፉ ምልክት ነው። ኮከብ ማይትን እና ኹሉንም የክፋት ምልክቶችን አስተማረ። እነሱም ብርቅያል፣ ኮከብኤል፣ ወጣምኤል፣ አስድረኤል የረአይት አባቶች ናቸው። ለአንተም አባቶችህ ኾኑ ከአዳም ሰባተኛ የኾነው ሄኖክ እንዳለው ብርቅኤል ኮከብ ማየትን አስተማረ፣*

*ኮከብኤልም ምልክቶችን፣ ወጣምኤል ኮከብ መቁጠርን አስተማረ፤ አስረድኤልም ሰውን ለማጥፋት የጨረቃን ሩጫ አስተማረ።*

ከገጸ ምንባቡ እንደምንረዳው ዘርዓ ያዕቆብ ክርስቲያኖች ኹሉ ጠንቋዮችን እንዳይከተሉ ያሳስባል። እነዚኽም ጠንቋዮች የተቀደሰውንና ከፍ ያለውን መኖሪያቸውን የተዉ የክፉዎችና የጨለማ መላእክትን ትምህርት የሚከተሉ ናቸው። በሄኖክ እንደተገለጸው መላእክተ ጽልመት የተባሉትም ልዩ ልዩ ርኲሰትን፣ በፀሐይ በጨረቃ፣ በከዋክብት ማምለክንና ማሟረትን ያሰተማሩ ናቸው። በመኾኑም ማንኛውም ክርስቲያን በልዩ ልዩ ማዕርግ የሚገኙ (መዘምር፣ አናጉንስጢስ፣ንፍቅ-ዲያቆን፣ሥረይ ዲያቆን፣ቄስ፣ኤጲስቆጶስ፣ጳጳስ፣ሊቀ ጳጳስ)[23] ጠንቋዮችን በመተባበር፣ ትምህርታቸውን በመስማትና ግብራቸውን በመከተል ከክርስቲያናዊ ሕይወት እንዳይራቆት ደራሲው ያስጠነቅቃል። ይኽም የሚያሰረዳው በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ከጨለማው መላእክት የመነጨው ልዩ ልዩ የጥንቆላ ትምህርትና ሥራ ምን ያኽል ተስፋፍቶ እንደ ነበርና በከፍተኛ ማዕርገ ክህነት ያሉትንም እንዳጠቃ "...ወአንተሰ እምድኅረ በጳሕከ ውስተ ዝንቱ መዐርግ ክቡር አንሐልከ ኵሎ መዐርገ ክህነት..." የሚለው ኀይለ ቃል በግልጽ ያሳያል። በመጨረሻው አንቀጽ የጨለማው መላእክት ስማቸው ከነ ግብራቸው መጠቀሱ ደራሲው ስለመጽሐፈ ሄኖክ ያለውን ጥልቅ ግንዛቤ ያስረዳል።

# ፳.፬.ሄኖክ በመጽሐፈ ምሥጢር (EMML 6456)

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መጽሐፈ ሄኖክን በድርሰቱ የተለያዩ ሐሳቦችን ለመግለጽ በተደጋጋሚ በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ የጠቀሰው ሲኾን ለምሳሌ ገነት በምሥራቅ በኩል በምድር ላይ ከፍ ብላ የምትገኝ መኾኗን ለማስረዳት መጽሐፈ ሄኖክን አስረጅ በማድረግ እንደሚከተለው ጽፏል።

*...ወቦ እለ ይቤሉ ከመ ገነትኒ ኤዶም ውስተ ሰማይ ይእቲ ወአኮ ውስተ ምድር። ወእመሰ በሰማያት ይእቲ ለምንትኬ ትቤ ቅድስት ኦሪት ወፈለግ ይወፅእ እምነ ቅድሜሃ ከመ ይስቅያ ለገነት ወእምህየ ይትፈለጥ ለአርባዕቱ መዓዝነ ዓለም...ወሶበሰ በሰማያት ይእቲ እምይቤ ይረድ ከመ ዘእምላዕሉ ወኢይቤ ይወፅእ እምገነት...። ወምድርሰ ዘነበረ አዳም ውስቴታ ጥቃ ገነት ይእቲ ዘአንጻረ ጽባሕ...። ወእምአዳም እስከ ኖኅ ነበሩ ደቂቀ አዳም ውስተ ጥቃ ገነት። ወሶበ አማሰኑ ውሉደ ሰብእ ፍኖቶሙ በዐሊወ ትእዛዛቲሁ ለእግዚአብሔር አመ ርደቶሙ ለትጉኃነ ሰማይ እለ ተደመሩ ምስለ አዋልደ ሰብእ ወመሀሩ መቲረ ዐሥራው ወገቢረ ሥራይ ወርእየተ ኮከብ ወመልአት ምድር ዐመፃ ወትዕቢተ*

[23] እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የአገልግሎት ደረጃዎች ናቸው።

*ወትእግልተ ፍግዓ ወዝሙተ ወቀትለ ወክዕወተ ደም (cf. En7:1-5)። ወነስሐ እግዚአብሔር በእንተ ዘገብሮ ለእጓለ እመሕያው ወይቤሎ ለኖኅ ግበር ለከ መስቀረ በዘትድኅን አንተ...። ወገነትሰ ይእቲ ዘተካላ እግዚአብሔር ወይእቲ ትነብር ድሉተ ለርስተ ቅዱሳን ጽጌሃ ኢይትነገፍ ወፍሬሃ ኢየዐብር ወቈጽላ ኢይጸመሂ (cf. En24:4) እስመ እግዚአብሔር ተከላ...(ገጽ 84-89)።*

*ትርጉም፦ .... ገነት በምድር ሳይኾን በሰማይ ናት የሚሉ አሉ። ገነት በሰማይ ከኾነች ቅድስት ኦሪት ሰለሞን እንደዚኽ አለች፤ ወንዝ ከፊቷ ይወጣል ገነትንም ያጣታል። በዚኽም ዐራቱ የዓለም አቅጣጫዎች ይለዩበታል። ገነት በሰማይ ብትኾን ኖሮ ከላዩ ይወርዳል ባለ ነበር፤ ከገነትም ይወጣል አይልም ነበር።... አዳም በውስጧ የነበረባት ምድር በስተምስራቅ በኩል ከገነት አጠገብ ነበረች ከአዳም እስከ ኖኅ የነበሩ የአዳም ልጆች በገነት አጠገብ ኑረዋል የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን ሕግ በመጣስ መንገዳቸውን ባጠፉ ጊዜ፣ የሰማይ ትጉሀን ወርደው ከሰው ልጆች ጋር በተቀላቀሉ ጊዜ፣ ሥር መበጠስን፣ ኮከብ መቁጠርን፣ ሥራይ ማድረግን አስተማሩ። ምድርም አመፃን፣ትእቢትን፣ መዳራትን፣ ዝሙትን፣ ግድያንና ደም መፋሰስን ተሞላች። እግዚአብሔርም ሰውን በመፍጠሩ ተፀፀተ። ኖኅንም የምትድንበትን ታቦት ሥራ አለው። እግዚአብሔር የተከላት ገነትስ ይህች ናት። እሷም ለቅዱሳን እርስት ተዘጋጅታ ትኖራለች። አበባዎቿ አይረግፉም፤ ፍሬዎቿም አይጨማተሩም፣ ቅጠሎቿም አይጠወልጉም እግዚአብሔር ተክሏታልእና...*

አባ ጊዮርጊስ ገነት በምድር ላይ እንደምትገኝ ለመግለጽ ከአዳም እስከ ኖኅ ያሉት አባቶች በገነት አቅራቢያ መኖራቸውን ይገልጻል[24]። ይኹን እንጂ ትጉኃን የተባሉ ደቂቀ ሴት ከሰማይ (ከደብር ቅዱስ) በወረዱና ውሉደ ሰብእ (የሰው ልጆች) ተብለው ከተገለጹት ከደቂቀ ቃየል ጋር በተገናኙ ጊዜ ሥር መበጠስ፣ ኮከብ መቁጠርና ሥራይ ማድረግን በማስተማራቸው የሰው ልጆች በመንገዳቸው ኹሉ እግዚአብሔርን በደሉ። ምድር በዐመፃ፣ በቅሚያ፣በዝሙት፣በመገዳደልና ደም በማፍሰስ ተሞላች። ይኽም ፈጣሪን ስላስቀየመው በጉን የጠበቀ ኖኅንና ቤተሰቦቹን በመርከብ ሰውሮ ምድርንና በምድር ያሉትን በጥፋት ውኃ ቀጣቸው። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለቅዱሳን ርስት ትኾን ዘንድ ያዘጋጃት ገነት የምድር ክፍል ብትኾንም ማየ አይኅ በምድር ላይ ሲዘንብ ልምላሜዋ ሳይደርቅ፣ቅጠሉዋ ሳይጠወልግ፣ ፍሬዋ ሳይረግፍ ተጠብቃ መኖሯን ሄኖክን ዋቢ በማድረግ አባ ጊዮርጊስ ያስረዳል።

[24] አዳም ከሞተ በኋላ ነገደ ሴትና ነገደ ቃየል ለኹለት እንደተከፈሉ፣ሴትም ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን በደብር ቅዱስ (አዳም ከገነት ሲባረር ያረፈበት ቦታ) ቃየልም ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን ከደብር ቅዱስ በታች በሚገኝ ቦታ እንዳስቀመጣቸው በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ተጠቅሷል (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ገጽ 25)።

# ፩.፩.ሄኖክ በመጽሐፈ ሰዓታት (Call No. EMML7020)

አባ ጊዮርጊስ ከብሉይና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እየጠቀሰ ክርስቲያኖች የሌሊትና የቀን በማለት በኹለት ከፍለው የሚጸልዩትን የ መጽሐፈ ሰዓታት የጸሎት መጽሐፍ ሲያዘጋጅ መጽሐፈ ሄኖክንም እንደ አንድ ምንጭ ተጠቅሞታል፡፡ ለማስረጃ ያክል የሚከተለውን አንቀጽ ማየት በቂ ነው፡፡

*…በምክረ ጥበብ (cf. En42:1) ተተክለ ሕሊናሆሙ ለከዋክብት ዘምስለ ሠርቅ ወዐረብ በበጊዜሁ ወለለአዝማኑ ወለለ አውራኂሁ (cf. En82:9) ፤ ወዑደታተ ፀሐይኒ ዘምስለ አብሀርቲሁ (cf.*

*… የከዋክብት ሕሊናቸው በየጊዜው፣ በየዘመኑ፣ በየወራቶቹ ከመውጫ እና መግቢያው ጋር የፀሐይም ዙረቶች (ዑደታት) ከብርሃናቱ ጋር በምክር ጥበብ ተተከለ፡፡*

*En72:4-37) ፤ ወሩጸተ ወርኅኒ ለለመዋዕሊሁ ሑጻጼሁኒ እስከ ይተርፍ በከመ ዐውዱ (cf. En78:8)፡፡ ወልደ ብርሃኑኒ እንዘ ይትዌሰክ እምዕለት ዕለት እስከ ይመልእ ጥንቁቀ (cf. En73:8, 78:10)፡፡ ወኵሉ ሥሩዕ ወግቡር በኃይለ ሥላሴ ቅድስት…(f. 3)*

*…ዝ ውእቱ መልአክ ዘይቀጽብ ነፍሳተ ውስተ አኅጉሎቱ፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘይሜህር ሐሰተ እምዚአሁ፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘመሀሮ ለቃየል ይቅትል እኁሁ (cf. En69:6)፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘሜጠ ሕሊናሆሙ ለውሉደ ሰማይ ከመ ይዘምዉ በአዋልደ ሰብእ እስከ አውለዱ ደመ ሥጋ (cf. En6:1, 69:4)፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘረሰዮሙ ለረአይት ከመ ይቅትሉ ሰብአ ወከመ ያብዝኑ ሥራያተ ዲበ ምድር ወ (ሰገላ) በአዕዋፍ (cf. En7:4-5)፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘረሰዮ ለአፍከስድ ከመ ያዕሉ መጻሕፍተ ሥራይ ዘሀሎ ውስተ ኵኵሕ ዘጸሐፉ ረአይት ከመ ኢይደምሰስ በአይኅ… (cf. En69:9) (f. 9)*

ትርጉም፡- የጨረቃ ሩጫም በየዘመኑ፣ ጉድለቱም እንደ አውዱ እስኪተርፍ ድረስ የብርሃኑ መወለድም በጥንቃቄ እስኪሞላ ድረስ ከቀን ወደ ቀን እየተጨመረ፡፡ ሁሉም በቅድስት ሥላሴ ኃይል የተሰራ እና የተፈጠረ ነው፡፡
ነፍሳትን ወደ ጥፋቱ የሚጠቅሰው መልአክ ይህ ነው፡፡ ሐሰትን ከእራሱ የሚያስተምር መልአክ ይህ ነው፡፡ ከሰው ልጆች ጋር ዝሙትን ፈፅመው ደመ ሥጋ እስኪወልዱ ድረስ የሰማይ ልጆችን አእምሮ የለወጠው መልአክ ይህ ነው፡፡ ረአይትን ሰውን እንዲገድሉ፣ በምድር ላይ ሥራይ እንዲያበዙ፣ በወፍ እንዲያሟርቱ ያደርጋቸው መልአከ ይህ ነው፡፡ አፍብድስን ረአይት የጻፉትን

በአላት ውስጥ ያለውን የአስማት መጽሐፍ በጥፋት ውሃ (በማየ አይኅ) እንዳይጠፋ እንዲያሸሽ ያደረገው መልአክ ይህ ነው፡፡

ደራሲው በመጀመሪያው አንቀጽ ስለ ከዋክብት፣ ፀሐይ እና ጨረቃ ይናገራል፡፡ በየቀኑ በየወራቱና ዘመናቱ የሚወጡና የሚገቡ የከዋክብት አኗኗር በጥበበ እግዚአብሔር መዘጋጀቱን አባ ጊዮርጊስ ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም የፀሐይ ምሕዋር፣ የጨረቃ በየጊዜው መመላለስ፣ ብርሃኑም ፈጽሞ እስኪሞላ ወይንም እስኪጎድል ድረስ ከዕለት ወደ ዕለት እንዴት እየጨመረ ወይንም እየቀነሰ እንደሚኼድ፣ በጠቅላላው ኹሉም ነገር በቅድስት ሥላሴ ኀይል እንደሚከናወን ያስረዳል፡፡

በኹለተኛው አንቀጽ አባ ጊዮርጊስ ስለክፉው መልአክና መገለጫዎቹ ያብራራል፡፡ ከራሱ አመንጭቶ ውሸትን ለሌሎች የሚያስተምር፣ቃየል ወንድሙ አቤልን እንዲገድል ያስተማረ፣ የሰማይ ልጆችን (ደቂቀ ሴትን) ልቡናቸውን ወደ ዝሙት በመመለስ ከሰው ልጆች (ደቂቀ ቃየል) ጋር እንዲገናኙ ያደረገና ረአይት የተባሉ ረጃጅም ልጆችን እንዲወልዱ ያደረገ፣ በምድር ላይ ሰዎችን እንዲገድሉ፣ሥራይ ማድረግን በወፍ (በዶሮ) ማሟረትን እንዲለማመዱ ያደረገ ይኽ ክፉው መልአክ መሆኑን ከመጽሐፈ ሄኖክ በመጥቀስ ደራሲው ያብራራል፡፡

## ፩.፮.ሄኖክ በመጽሐፈ ፀሐይ (Call No. EMML 1389)

መጽሐፈ ፀሐይ እንደ ስሙ ስለ ፍጥረታዊቷ ፀሐይ የሚያትት ሳይኾን ስያሜው ምሳሌያዊ (symbolical) ነው፡፡ ይኸውም ፀሐይ በወጣ ጊዜ ጨለማ እንደ ሚገፈፍና እንደሚርቅ በፀሐይ የተመሰለ ቃለ እግዚአብሔርም ወደ ሰዎች አእምሮ በገባ ጊዜ በጨለማ የተመሰለ ድንቁርና ይወገዳል፤ ዕውቀት ጥበብ (ፈሪሐ እግዚአብሔር) ይገለጣል ለማለት መኾኑን ደራሲው ይናገራል፡፡ ደራሲው ከመጽሐፍ ቅዱስ በዋናነት ደግሞ ከትንቢተ ነቢያት ኀይለ ቃልን እየመዘዘ ግዕዝ በግዕዝ ያብራራል፡፡ ትርጓሜውን በምስክር ለማጽናት ሲሻም መጽሐፈ ሄኖክን እና ሌሎች መጻሕፍትን ዋቢ አድርጎ ይጠቅሳል፡፡ ለማሳሌ፡-

*"…ወዓዲ ይቤ ኢሳይያስ ከመ በኵረ ላህም ሥነ ላህምሰ ይተረጎም በአዳም፤ ይቤ ሄኖክ በእንተ አዳም፡- ወጽአ ላህም ፀዓዳ እምድር (cf. En85:3) ወከመሰ ይመስሎ እግዚአብሔር ለአቡነ አዳም*

*ዳግመኛም ኢሳይያስም አለ ውበቱ እንደ በሬ አውራ ነው፡፡ በሬውም በአዳም ይተረጎማል፡፡ ሄኖክ ስለ አዳም አለ፡፡ ነጭ በሬ ከምድር ወጣ እግዚአብሔር አባታችን አዳምን እንደሚመስለው፡፡*

*… ወዓዲ ይቤ ላህምኒ አእመረ ዘአጥረዮ ወአድግኒ ምቅማሆ ወቤተ እግዚአ*

*(ኢሳ.1፡3)፤ አልህምትኒ አበው ቀደምት እሙንቱ እለ አእመርዎ ለእግዚአብሔር በከመ ሰመዮሙ ሄኖክ ወአእዱግሰ አሕዛብ እሙንቱ ወቤተ እግዚአሙኒ ቤተ ክርስቲያን ይእቲ እንተ ይቀምሁ በውስቴታ ትምህርተ ሃይማኖት። ሄኖክኒ ይቤ በእንተ አብርሃም ወእስማኤል፦ ወዝኩ ላህም ፀዓዳ ወለደ አድገ ገዳም፤ ላህምሰ ፀዓዳ አብርሃም ውእቱ ወአድግኒ እስማኤል..." (cf. En89:11)...(ff. 23-25)።*

*...ወዓዲ ይቤ ነቢይ ዕንባቆም፦ ወይትቀጠቀጡ አድባር እምኃይሉ ወይትመሰዉ አውግር ዘእምዓለም ርኢኩ...አድባርሰ ወአውግር እለ ተቀጥቀጡ ነገሥት ዓላውያን እሙንቱ። ወሄኖክኒ ይቤ በእንቲአሆሙ፦ ደብረ ሐፂን ወደብረ ጸሪቅ ደብረ ብሩር ወደብረ ወርቅ ደብረ ነጠብጣብ ወደብረ አረር እሉ ኩሎሙ በቅድሜሁ ለኀሩይ ይከውኑ ከመ መዓረ ግራ ዘቅድመ እሳት፤ ወከመ ማይ ዘይወርድ እምላዕሉ ዲበ እሉ አድባር ወይከውኑ ድኩማነ በታሕተ እገሪሁ (cf. En52:6) ። እሉሴ ነገሥት አድባር እምዓለም እለ ይቀጠቅጦሙ ወልድ በዕለተ ስቅለቱ...*

*ትርጉም፦ ... ዳግመኛም አለ በሬ የገዥውን አህያም የጌታውን ጋጥ አወቀ (ኢሳ 1፥ 3)። ሄኖክ እንደሰየማቸው በሬዎቹ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ የቀደሙ አባቶች ናቸው። አሕያዎችም አህዛብ ናቸው። የጌታቸው ቤትም በውስጧ የሃይማኖት ትምህርትን የሚማሩበት (የሚግጡበት) ቤተ ክርስቲያን ናት። ሄኖክም ስለ አብርሃም እና ስለ እስማኤል ተናገረ። ይህ ነጭ በሬ የሜዳ አህያ ልጅ ነው። ነጩ በሬ አብርሃም ነው። አህያውም እስማኤል ነው ።*

*... ዳግመኛ ነብዩ እንባቆም አለ። ተራራዎች በኃይሉ ሲቀጠቀጡ፣ኮረብታዎችም ሲቀልጡ ለዘለዓለም አየሁ። የተቀጠቀጡ ተራራዎችና ኮረብታዎች ከሀድያን ነገስታት ናቸው። ሄኖክም ስለእነሱ ተናገረ የብረት ተራራ፣ የመዳብ ተራራ፣ የወርቅ ተራራ፣ የጠል ተራራ፣ የሐናር ተራራ እነዚህ ሁሉ በተመረጠው ፊት ከእሳት ፊት እንዳለ እንደ ግራር ማር ይሆናሉ። ከእነዚህ ተራራዎች እንደሚወርድ ውሃ ከእግሩ በታች ደካማ ይሆናሉ። እነዚህ ነገስታት ተራሮች ወልድ በሚሰቀልበት የሚቀጣቸው ናቸው።*

ከላይ እንደተቀመጠው በነቢዩ ኢሳይያስና ዕንባቆም የተጠቀሱትን ኀይለ ቃላት ለማብራራት የመጽሐፈ ፀሐይ ደራሲ ሄኖክን እንደምስክር ይጠራል። ለምሳሌ በኢሳይያስ የተነገረውን "...ላህምኒ አእመረ ዘአጥረዮ ወአድግኒ ምቅማሆ ወቤተ እግዚኡ/ በሬም ገዢውን አህያም ገለባ የሚቅምበትን የጌታውን ቤት አወቀ" የሚለውን ምሳሌያዊ ትምህርት ሲተረጉም አልህምት/በሬዎች የተባሉ እግዚአብሔርን የሚያውቁ/የሚያመልኩ አበው ሲኾኑ አእዱግ/አህዮች የተባሉት ደግሞ እግዚአብሔርን የማያወቁ/የማያመልኩ አሕዛብ መኾናቸውን ያመለክታል። እንዲኹም ገለባ የሚቅሙበት የጌታቸው ቤት የተባለችው ትምህርተ ሃይማኖትን የሚመገቡባት ቤተክርስቲያን መኾኗን መጽሐፈ ሄኖክን አብነት

አድርጎ ያስረዳል፡፡ ነቢዩ ዕንባቆም "ከኀይሉ የተነሳ ተራሮች ይንቀጠቀጣሉ፤የዘላለምም ኮረብቶች እንደ ስም ይቀልጣሉ"[25] ሲል በተራሮች መስሎ ያስተላለፈውን ምሥጢር ከሄኖክ (52፡6) ከተነገረው ምሳሌ ጋር በማዛመድ በተራራና ኮረብታ የተመሰሉ ነገሥታትና መኳንንት መኾናቸውን ደራሲው ያብራራል፡፡ ይኽም ጌታ በስቅለቱ ሔሮድስ፣ ጲላጦስን፣ ሃና ቀያፋን እንዲሁም አጋንንትንና ሠራዊቱን ድል ማድረጉን ያመለክታል፡፡

## ፭.፯.ሄኖክ በመጽሐፈ ስንክሳር (Call No. EMML 4273)

የመጽሐፈ ሄኖክ ጥቅሶች በስፋት ከሚገኙባቸው አንዱ መጽሐፈ ስንክሳር ሲኾን በተለይም ስለ ቅዱሳን መላእክት የሚያዘክረው ክፍል ተጠቃሽ ነው፡፡ ለምሳሌ መስከረም አንድ ቀን ስለ መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል፣ኅዳር ስምንት ስለ መልአኩ ቅዱስ አፍኒን እና አርባዕቱ እንስሳ፣ኅዳር12 ስለ ቅዱስ ሚካኤል፣ጥር 27 ስለ ነቢዩ ሄኖክ የተጻፉትን ማየት ይቻላል፡፡

## ፮. መጽሐፈ ሄኖክ በግጥም ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ

ከግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ አንዱ ዘውግ ግጥም ነው፡፡ አባቶቻችን ካወረሱን የሥነ-ጽሑፍ ቅርሶች መካከል ከማንም ያልተቀዳ የራሱ መሠረትና ቅርጽ ያለው ግጥም አንዱ ነው፡፡ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶችን ጨምሮ የእነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አባ ጽጌ ድንግል፣ አርከ ሥሉስ፣ ዘርዓ ያዕቆብ እና የመሳሰሉት ሊቃውንት ድረሰቶቻቸው በከፊል እንዲሁም በምልአት ግጥሞች ናቸው፡፡ መልክዕ፣ አርኬ፣ ነግሥ ተብለው ከሚታወቁት ባለ አምስት ስንኝ ግጥሞች[26] ባሻገር እንደ መስተብቁዕ፣ሊጦንና እሴብሕ ጸጋኪ የመሳሰሉ ባለ ብዙ ስንኝ ግጥሞችም አሉ፡፡ሊቃውንቱ ለግጥሞቻቸው መነሻ ሐሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከአዋልድ መጻሕፍት በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ የሚወስዱ ሲኾን መጽሐፈ ሄኖክንም እንደ ምንጭ ተጠቅመውበት እናገኛለን፡፡ ጸሓፍያኑ መጽሐፈ ሄኖክን መነሻ አድርገው በደረሷቸው ግጥሞች ትምህርተ ሃይማኖትን (ነገረ ሥላሴ፣ ነገረ ክርስቶስ፣ ነገረ ማርያም፣ነገረ መላእክትን ወዘተ) በስፋትና በጥልቀት አስተላልፈዋል፡፡ኹሉንም ማቅረብ ባይቻልም ለምሳሌ ይኾን ዘንድ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

[25] ዕንባቆም 3፡6

[26] እዚኽ ላይ የግጥምን ባሕርያት (የቃላት ምርጫና ምጠና፣ የቤት መምታትና መድፋት ወዘተ) አሟልተው ስለሚገኙ ግጥም ተባሉ እንጂ መልክእ፣ አርኬ ነግሥ የራሳቸው መለያ ሥነ-ጽሑፋዊ ባሕርይ ያላቸው መኾኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

በከመ ሄኖክ ዜነወነ ነኵርኳረ ነፋስ ዘተጽዕነ
ልሣነ እሳት ሕኑጽ ዘትረፍቅ መካነ
ጰራቅሊጦስ ነድ ቁርባነ ምሥጢር ዘኮነ
ክረምተ ሕግከ ነፍንፍ ዲቤነ
አስካለ ወንጌል ስሂነ ዘያፈሪ ብነ።

ምንጭ:- አርኬ፡ Call No EMML3128,f 7 , date: 16th cent

ትርጉም፡ በነፋስ ሠረጋላ የተጫነ /የተጓዘ ሄኖክ እንደነገረን
በእሳት ልሣን በታነጸ ቤት
የምትኖር ጰራቅሊጦስ ነድ ሆይ፣ የሚስጥር ቁርባን የኾነ
ክረምት ሕግህን በእኛ ላይ አዝንም፤
የወንጌል ዘለላ (ፍሬን) በእኛ ያፈራ ዘንድ፡

ከላይ ያለው ግጥም ዋና ሐሳቡ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስን የሚያመሰግን ሲኾን ገጣሚው ለሐሳቡ መነሻ ያደረገው ነቢዩ ሄኖክ ያየውን ምሥጢር ነው። ይኸውም በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 14፡15-22 የተከተበው ሲኾን የሚከተለው ነው፡-

*...ወናሁ ካልዕ ቤት ዘየዐቢ እምዝንቱ ቤት ወኵሉ ኆኅቱ ርኅው በቅድሜየ ወሕኑጽ በልሳነ እሳት። ወበኵሉ ይፈደፍድ በስብሐት ወበክብር ወበዕበይ እስከ ኢይክል ዜንዎተክሙ በእንተ ስብሐቲሁ ወበእንተ ዕበዩ። ወምድሩሰ እሳት ወመልዕልቴሁ መብረቅ ወምርዋጸ ከዋክብት ወጠፈሩኒ እሳት ዘይነድድ። ወነጸርኩ ወርኢኩ ውስቴቱ መንበረ ልዑለ ወራእዩ ከመ አስሐትያ ወክበቡ ከመ ፀሐይ ዘያበርህ ወቃለ ኪሩቤል። ወእምታሕተ መንበሩ ዐቢይ ይወፅኡ አፍላገ እሳት ዘይነድድ ወኢይክሉ ርእዮቶ። ወዐቢየ ስብሐት ይነብር ላዕሌሁ ወዐጽፉሰ ዘይበርህ እምፀሐይ ወይጸዐዱ እምኵሉ በረድ። ወኢይክል መኑሂ እመላእክት በዊአ ወራእየ ገጹ ለክቡር ወስቡሕ ወኢይክል መኑሂ ዘሥጋ ይርአይ ኪያሁ እሳተ። እሳት ዘይነድድ በዐውዱ ወእሳት ዐቢይ ይቀውም ቅድሜሁ ወአልቦ ዘይቀርብ ኀቤሁ እምእለ ዐውዱ ትእልፊተ ትእልፊት ቅድሜሁ ወውእቱስ ኢይፈቅድ ምክረ ቅድስተ...*

*ትርጉም፡- ... አሁን ከዚህ ቤት የሚበልጥ ሌላ ቤት ሁሉም በሮቹ በፊቴ ተከፈቱ። በእሳት ልሳን የታነፀ ነው። ስለ ምስጋናው እና ግርማው ልነግራችሁ እስከማልችል ድረስ ክብሩ ምሥጋናው፣ ግርማሞገሱ ከሁሉም ይልቃል። ታች እሳት ላዩ መብረቅ ከዋክብት የሚሮጡበት። ጣራውም የሚነድ እሳት ነው። በውስጡ መልኩ እንደ አመዳይ፣ ክበቡ በኪሩቤል ቃል እንደሚያበራ ፀሐይ ያለ ታላቅ ዙፋን (መንበር)*

*አየሁ። ከታላቁ ዙፋን በታች ለማየት የማይችሉ የሚነዱ የእሳት ወንዞች ይወጣሉ። ታላቅ ምስጋና ከላዩ ላይ ተቀምጧል። መጎናፀፊያው ከፀሐይ ይልቅ ይበራል። ከበረድም ሁሉ ይነጣል ከመላእክት ማንም መግባትና የተነሰገነውን፣ የተከበረውን ገፁን ማየት አይችልም። ከሥጋዊውም ማንም እሱን እሳትን ያይ ዘንድ አይችልም። በዙሪያው እሳት ይነዳል። ታላቅ እሳትም በፊቱ ይቆማል በዙሪያው ካሉ የብዙ ብዙ በፊቱ የሚቀርብ የለም። እሱም የተለየች ምክርን አይሻም……*

ከላይ እንደተመለከትነው በእሳት ላንቃ በታነጸው፣ሊነገርና ሊተረጎም በማይችል በክብር ሁሉ ከፍ ያለ ቤት፣ መሠረቱ እሳት፣ ጠፈሩ እሳት፣ በላዩም የከዋክብትና የመባርቅት መፋጠን የሚታይበት ቤት ውስጥ ሌላ ደግሞ እጅግ ከፍ ያለ፣ መልኩ እንደ ዐመዳይ፣ ክበቡ እንደ ፀሐይ የሚያበራ፣ከሥሩም የሚነድ የእሳት ወንዞች የሚፈልቁበት መንበር እንደ አየ ይገልጻል።

በዚኽም መንበር ላይ የክብርና የምስጋና ባለቤት፣መጎናጸፊያው ከፀሐይ ይልቅ የሚያበራ፣ ከበረዶም ኹሉ የሚነጣ፣ ከመላእክትም ወገን ማንም ወደርሱ መቅረብ የሚቻለው የሌለ፣ “ወኢይክል መኑሂ ዘሥጋ ይርአይ ኪያሁ እሳተ ”- ከሥጋውያን ፍጥረታትም ወገን ማንም ሊያየው የማይችል “እሳት” ተብሎ የተጠራ ተቀምጦበታል። ይኽንን ነቢዩ ሄኖክ “እሳት” ብሎ የጠራውን ምሥጢር ደራሲው “ጸራቅሊጦስ ነድ” በማለት በዚያ ግሩምና ድንቅ በኾነው ቤትና በሚያስፈራው መንበር ላይ የተገለጸው መንፈስ ቅዱስ መኾኑን ተርጉሞልናል።

ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት በተለይም በሐዲስ ኪዳን የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ኹለት አንጻርም ሲታይ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል መገለጡ የተለመደ በመኾኑ[27] ደራሲው የሄኖክን ምሥጢር ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ መተርጎሙ የትኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ ሊያስማማ የሚችል ሀቅ ነው። በመኾኑም ሊቁ ደራሲ መጽሐፈ ሄኖክ በነገረ መንፈስ ቅዱስ (Pnuemathology) ላይ ሊኖረን የሚገባንን ዕውቀት እንድናገኝና ልናደርገው የሚገባንን ጥናትና ምርምር ለማሳደግ የሚያግዘን ኹነኛ መጽሐፍ መኾኑን አመላክቶናል።

ወመጽአ ኅቤየ ርእሰ መዋዕል
ሄኖክ ይብል
ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል
ወምስለ ሩፋኤል ወፋኑኤል

[27] ለምሳሌ ማቴ. 3፥11 (*ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው (በአንድምታ)*፣ (1988 ዓ.ም)፣ አዲስ አበባ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።

ምስለ ኵሎሙ፡ አዕላፈ አዕላፋት
እለ አልቦሙ፡ ኍልቍ ሠራዊት
ምንጭ:- ነግሥ/ እግዚአብሔር ነግሠ Call No. 7061, f6, date:15thcent.

ሄኖክ እንዲህ አለ፡- ብሉየ መዋዕል (አብ)
ወደእኔ መጣ፤ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር፤
ከሩፋኤልና ከፋኑኤል ጋር፤
ቁጥር ከሌላቸው የብዙ ብዙ ከሚሆኑ ሠራዊተ
መላእክት ጋር፡፡

የዚኽም አርኬ መሠረተ ሐሳብ "…ወመጽአ ውእቱ ርእሰ መዋዕል ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ሩፋኤል ወፋኑኤል ወአእላፍ ወትእልፊተ አእላፍ እለ አልቦሙ ኍልቍ…" (ሄኖክ.71÷13) ከሚለው በቀጥታ የተወሰደ ነው፡፡ የግጥሙ ዋና መልእክትም ብሉየ መዋዕል ተብሎ የሚጠራ ዘመን የማይቆጠርለት እግዚአብሔር እልፍ አእላፋት በኾኑ መላእክት ታጅቦ እርሱ በወደደው መጠን ለሄኖክ መታየቱን ወይም መገለጡን ያስረዳል፡፡ ምንም እንኳ ሠለስቱ አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብሉየ መዋዕልነት ገንዘባቸው ቢኾንም በመጽሐፈ ሄኖክ አገባብ ግን ብሉየ መዋዕል የሚለው አገላለጽ በአብዛኛው የሚያመልከተውከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር አብን ነው፡፡ ለምሳሌ፡- "ወበህየ ርኢኩ ዘሎቱ ርእሰ መዋዕል፤ ወርእሱ ከመ ፀምር ፀዓዳ፤ ወምስሌሁ ካልዕ ዘገጹ ከመ ርዕየተ ሰብእ… ወተስእልክዎ ለአሐዱ እመላእክት ቅዱሳን ዘየሐውር ምስሌየ ወኵሎ ኅቡአተ ዘአርአየኒ በእንተ ዝኩ ወልደ ሰብእ"[28] (መ.ሄኖክ ትርጓሜ 12÷19) በሚለው ገጸ ምንባብ ውስጥ **ዘሎቱ ርእሰ መዋዕል** የሚለው ሐረግ የሚወክለው ብሉየ መዋዕልነት ገንዘቡ የኾነ እግዚአብሔር አብን ሲኾን ከርሱ ጋር አብሮ ለሄኖክ የተገለጠውና **ዘገጹ ከመ ርዕየተ ሰብእ፣ ወልደ ሰብእ** ተብሎ የተጠራው እግዚአብሔር ወልድ ነው፡፡ ይኸውም ወልደ አብ የተባለ የአካላዊ ቃልን ደኃራዊ ልደቱንና ሰው መኾኑን አስቀድሞ ለሄኖክ በምሥጢር እንደገለጠለት የሚጠቁም ነው፡፡ በመኾኑም ከላይ ያለው ግጥም (ነግሥ) መጽሐፈ ሄኖክ ስለ እግዚአብሔር አብ የሚያስተምር መኾኑን ያስረዳል፡፡

ሰላም እብል ለሄኖክ ጸሐፊሁ
ሙፃዓ ትንቢት እምቅድሜሁ
እምአዳም አቡሁ ወእስከ ክርስቶስ ጌናሁ
ወልደ ሰብእ ይመስል ርኢክዎ ይብል
በመንበረ ስብሐት ግሩም እንዘ ይነብር ኀይል፡፡
ምንጭ:- እግዚአብሔር ነግሠ Call No. 7061, f 50

[28] ሄኖክ 12፡19 (*መጽሐፈ ሄኖክ (አንድምታ)፣* (2003 ዓ.ም)፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡

ከአባቱ ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መወለድ
ትንቢትን ለተናገረ ለጸሓፊው ሔኖክ ሰላምታ አቀርባለሁ።
(እንዲህም) አለ፡- ድንቅ በኾነ የክብር ዙፋን ላይ ተቀምጦ
ኃይልን (ወልድን) አየሁት፤ የሰውን ልጅ ይመስላል።

የዚኽ አርኬ ዋና ዓላማ የወልደ እግዚአብሔር ሰው የመኾን ምሥጢር አስቀድሞ የተገለጠለትና ይኽንን ለጻፈ ለነቢዩ ሄኖክ ሰላምታ/ምስጋና ማቅረብ ሲኾን መነሻ ሐሳቡም፡- በምዕራፍ 46፥47 እና 48 ላይ ሄኖክ ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ እንዲሁም እስከ ዳግም ምጽአተ ክርስቶስ በምሳሌ የተናገረውን መሠረት ያደረገ ሲኾን በተለይም ነገረ ክርስቶስን በሰፊው ያስረዳል። በመኾኑም ደራሲው ይኽንን ነገረ ክርስቶስን (Christology) በጥልቀትና በስፋት ለመማር ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችል መጽሐፍ ለጻፈልን ለሄኖክ የምስጋና ሰላምታ ሲያደርስለት እናያለን። እስካሁን ለአብነት ባቀረብናቸው ድርሳናት ውስጥ እንዳየነው መጽሐፈ ሄኖክ ስለ ነገረ ሥላሴ ጥናት (Trinitarian Theology) ይልቁንም ስለ ነገረ መንፈስ ቅዱስ እና ነገረ ክርስቶስ ሊያስተምረን የሚችለው ብዙ ነገር መኖሩን ተገንዝበናል። በነገረ ማርያም ጥናት (Mariology) ዙሪያም ቢኾን ከመጽሐፈ ሄኖክ ብዙ ነገር መማርና ማጥናት እንደሚቻል የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሊቃውንት ጥልቅና የታመቀ ምሥጢር በላቸው ድርሰቶቻቸው አሳይተውናል። ለምሳሌ የሚከተለውን ማየት በቂ ነው።

ሰላም ለማርያም ቤተ ሄኖክ ነቢይ
በምድር ሐዋዝ ሥነ ሕንዔሃ ዐባይ
ወሥነ ሡራሬሃ ያበርህ እምሥነ ፀሐይ
ፈለሰት ይእዜ ከብካበ ሰማይ
ተማኅፀነ ባቲ እምኵሉ እኵይ።

ምንጭ፡- ነግሥ (Call No. 3592, f10, date: 18th cent

በመልካም ምድር ላይ የሕንፃዋ ውበት ታላቅ የኾነ፣
የአሠራሯም ውበት ከፀሐይ ይልቅ የሚያበራ
የነቢይ ሄኖክ ቤት ለተባለች ለማርያም ሰላምታ ይገባል።
ወደ ሰማያዊ የሰርግ አዳራሽ ዛሬ አረገች፤
ከክፉ ኹሉ ታድነን ዘንድ በእርሷ እንማጸናል።

የድርሰቱ ዋና መልእክት ነቢዩ ሄኖክ በራእይ ባያት ቤት የተመሰለቻው ድንግል ማርያም መኾኗንና ነገረ እርገቷ ላይ የሚያተኩር ሲኾን መሠራታዊ ሐሳቡም የተወሰደው ከመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 90 ቁጥር 27 ነው። በዚኽ ራእዩ ሄኖክ በመልካም ምድር ላይ የተሠሩ ኹለት ቤቶችን በቅደም ተከትል ወይም ተራ በተራ (አንዱ ፈርሶ ሌለው ሲተካ) የተመለከተ

ሲኾን የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቃውንት እነዚኽን ቤቶች፡- በሕገ ኦሪትና በሕገ ወንጌል፣ በምኩራብና በቤተ ክርስቲያን ምሳሌነት እንደ ቅደም ተከተላቸው ተርጕመዋቸዋል።

ከላይ ባላው አርኬ ውስጥ ግን ደራሲው ቤተ ሄኖክ የተባለች ድንግል ማርያም ናት የሚል ሲኾን እንዲኹም ሄኖክ ባያት ቤት ሲመስላት ከዚያች ቤት ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በነቢዩ የተነገሩት ኹሉ እርሷንም የሚመለከቱ መኾናቸውን እያሰበ በመኾኑ ወደምሳሊያዊ ትንታኔው ከመሄዳችን በፊት እነዚኽን ነገሮች ማየቱ ተገቢ ነው። በመኾኑም ሄኖክ ያያት ቤት ምን ትመስል ነበር? ስንል፡-

- ይኽችን ቤት ያመጣት የበጎች እረኛ ነው።
- "ምድር ሐዋዝ" (ያማረ ምድር) ላይ የተመሠረተች ናት።
- ከመጀመሪያዋ ቤት የበለጠ ውበቷ ኹለመናዋ አዲስና ታላቅ ነው።
- ምሰሶወቿ ኹሉ አዳዲስ ናቸው።
- በውስጧም የበጎች እረኛ የተቀመጠበት ዙፋን አለ።

እነዚኽን ነጥቦች መሠረት አድርገን ከላይ ደራሲው ስለ ለገረ ማርያም ሊያስተምረን የፈለገውን ብንመለከት እጅግ በጣም ሰፊና ጥልቅ ኾኖ እናገኘዋለን። በመጀመሪያ ድንግል ማርያምን በቤት መስሎ ማቅረቡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይትበሀል አንጻር "ቤት" የሚለው ቃል " ሰው፣ ሰውነት" የሚለውን ሐሳብ ወክሎ የሚነገር በመኾኑ አማናዊ ምሳሌነቱን መገንዘብ ይቻላል[29]።

"ምድር ሐዋዝ" ተብላ የተገለጸቻው ያች ቤት የተሠራችበትን ቦታም አማናዊት ቤተ መቅደስ የተባለች ድንግል ማርያም የተፀነሰችበትን ማኅፀነ ሃናን ይመለከታል። ይኽንንም አገላለጽ አባቷ ቅዱስ ዳዊት "መሠረታቲሃ ውስተ አደባር ቅዱሳን"[30] (መዝ. 87፥1) ካለው ጋር ተዛማጂ መኾኑን ልብ ይሏል። ሃናም "ምድር ሐዋዝ" ተብላ መጠራቷ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ባማረና በተቀደሰ አኗኗር ትገኝ ስለነበር ነው።
ይኽች ቤት ከመጀመሪያዋ ቤት እንደምትበልጥ መነገሩ፣ ድንግል ማርያም ከእነ ሔዋን፣ ከነ ሣራ፣ርብቃ በጠቅላላው ከቅዱሳት አንስት የምትበልጥ መኾኗን ሲያስረዳ ነው ።

[29] 2ኛ ነገ. 20፥1፤ ዮሐ. 2፥19።

[30] መዝ. 87፥1 (*መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው*፣(1982)፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ይኽንም እውነታ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ "አንቲ ተዐብዪ እምብዙኃት አንስት እለ ነሥአ ጸጋ ወክብረ" ሲል በግልጽ መስክሮላታል፡፡ በዚች ቤት ውበቷ ሁለመናዋ አዲስ ነው መባሉም ድንግል ማርያም በውስጥ በአፍአ፣ በነፍስ በሥጋዋ፣ በኀልዮ፣ በነቢብ በገቢር ንጽሕት እንደኾነች ያጠይቃል፡፡ ደራሲው "በምድር ሐዋዝ ሥነ ሕንፄሃ ዐባይ" በሚለው ስንኙ ድንግል ማርያም በእናቷ ማኅፀን ስትፀነስ ጀምሮ ከጥንተ አብሶ ንጹሕ በኾነ መንገድ መኾኑን ያስረዳናል፡፡ በዚች ቤት ውስጥ ያሉት ምሰሶዎች አዲሶች ናቸው የሚለው አገላለጽ ድንግል ማርያም በነፍሷም በሥጋዋም ኹል ጊዜ አዲስ ናት፤ በኹለት ምሰሶዎች በሚመሰሉት በድንጋሌ ሥጋ ወነፍስ በዘለዓለማዊ ሕዳሴ ውስጥ ተጠብቃ የምትኖር መኾኗን እንድናስብ ያመላክተናል፡፡ በተጨማሪም በዚች ቤት ውስጥ የበጎች እረኛ የተቀመጠበት ዙፋን መታየቱ ኖላዊ አባግዕ[31] ተብሎ የሚመሰገን ክርስቶስ ለዙፋንነት የመረጠው ማኅፀነ ማርያም መኾኑ የታመነ ነው፡፡ ይኽችን ቤት "ምድር ሐዋዝ" በተባለች ቦታ የሠራት የበጎች እረኛ እንደኾነ መገለጹ፣ድንግል ማርያምን በማኅፀነ ሃና አስቀድሞ ያዘጋጀ፣ ለእናትነት የመረጠ እውነተኛው የበጎች እረኛ ሰው የኾነ አምላክ መኾኑን እንረዳለን፡፡ በዚኽም ድንግል በማኅፀኗ የፀነሰቸውና በድንግልና የወለደችው ፈጣሪዋን መኾኑን፣ አንድም ከድንግል ማርያም የተወለደው ቅድመ ዓለም የነበረ ፈጣሬ ዓለማት መሆኑን እንድንረዳና ጥልቅ ወደኾነው ወደ ነገረ ሥጋዌ ዐይነ ልቡናችንን እንድናቀና ይጋብዘናል፡፡

በመጨረሻም ከላይ ባለው ግጥም የመዝጊያ ስንኞች ላይ እንደምንረዳው ቤተ ሄኖክ ተብላ የተጠራች ድንግል ማርያም ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም መሸጋገሯን ነው፡፡ እርሷ አኹን ያለችበትንም ዓለም "ከብካበ ሰማይ- በሰማይ ያለ የሰርግ አዳራሽ" በማለት የገለጸው ሙሽራው ክርስቶስ ባለበት ሙሽራዪቱ ድንግል ማራይም በሰርግ አዳራሽ በተመሰለች በመንግሥተ ሰማይ የምትኖር መኾኑዋን ያስረዳል፡፡ ይኽም አገላለጽ ነቢዩ ዳዊት ሙሽራውና ሙሽራይቱን በንጉሥና በንግሥት መስሎ "ወትቀውም ንግሥት በየማንከ በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኍብርት"[32] በማለት የዘመረላትን መዝሙር ያስታውሰናል፡፡

## ፯. መጽሐፈ ሄኖክ በቅኔ ውሥጥ

የቅኔ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክን የቅኔዎቻቸው የሐሳብ ምንጭ፣ የምሥጢር ማፍለቂያ አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡ ይኽንም የሚያስረዱ ብዙ ቅኔዎች ቢኖሩም በዚኽ ክፍል

[31] የሐ. 10፥1-18

[32] መዝ. 45፥9

ግን ኹሉንም ማቅረብ ስለማይቻል ለምሳሌ ይኸነን ዘንድ የሚከተለውን ቅኔ እንመርምር፡

ኢያስተፍሥሕዎ ነዳያን
ሙሴ ወኖኅ ለዘመደ ሥጋ ልደት
ጽውመ እስመ አኅደርዎ በብርሃን ቤት
ባዕለ ጸጋሰ ወልድ አክባሬ ልደት ብሑት
እስመ ምስለ መዓር አቅረበ ሀሊበ ሕይወት
ወኅብስተ ዘአልቦ መስፈርት[33]፡፡

ነዳያን የኾኑ ሙሴና ኖኅ የሥጋ ዘመድ ልደትን
አላደሰቱትም፤ በብረሃን ቤት ጦሙን አሳድረውታልና፡፡
ባለጸጋ ወልድ ግን ልደትን የሚያከብር የሠለጠነ ነው፡፡
የሕይወት ወተትን ከማር ጋር አቅርቧልና፡፡
ሥፍር ቁጥር የሌለው ኅብስትንም (አቅርቧልና)፡፡

ይኽ ቅኔ ዋዜማ በመባል የሚታወቅ ባለ አምስት ስንኝ ቅኔ ሲኾን ቅኔው የተደረሰውም ኢትዮጵያዊ ባህልንና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክን በማቀናጀት ነው፡፡ በባህላችን እንግዳን ተቀብሎ ያለው ማሩን ቅቤውን ወተቱን ዳቦውን አቅርቦ የሌለው ደግሞ ቤት ያፈራውን አቅርቦ የሚያስተናግድ ከኾነ ያሰው ቸር፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ሰው አክባሪ ነው ይባላል፡፡ ይኽን የማያደረግ ከኾነ ደግሞ ንፉግ፣ ክፉ መባል አይቀርለትም፡፡

ባለቅኔው ይኽንን ሰም ተጠቅሞ ኖኅንና ሙሴን ከክርስቶስ ጋር በማነጻጸር እነርሱ በእንግዳ የተመሰለ ልደትን (መወለድን) በአግባቡ እንዳልተቀበሉት፣ በብርሃን ቤታቸው ጦሙን እንዳሳደሩት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ማሩን ወተቱን፣ ዳቦውን እንዳቀረበለትና በክብር እንደተቀበለው ይናገራል፡፡

ወደ ቅኔው ወርቅ ወደ ኾነውና ወደዋናው ወደተነሣንበት መልእክት ስናልፍ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክን እንድናስተውል ይጋብዘናል፡፡ ይኸውም በቅኔው የተጠቀሱት ጻድቁ ኖኅና ነቢዩ ሙሴ ሲኾኑ በብርሃን ቤታቸው ልደት እንግዳን ጦም አሳደሩት ማለት እነርሱ በተወለዱበት ዕለት ቤታቸው (የዘመዶቻቸው ቤት) ተአምራዊ በኾነ ብርሃን ተሞልቶ እንደነበር ባለቅኔው በምሥጢር መናገሩ ነው፡፡ በኖኅ የልደት ቀን የተከናወነውን ተአምራዊ ክስተት በተመለከተ መጽሐፈ ሄኖክ እንዲኽ ይላል፡-

[33] የግዕዝ ቅኔያት የሥነ ጥብብ ቅርስ፣ ንባቡ ከነ ትርጓሜው፣ቅጽ 3፣ገጽ 89፣(ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)፡፡

*...ወእምድኅረ መዋዕል ነሥአ ወልድየ ማቱሳላ ለወልዱ ላሜህ ብእሲተ ወፀንሰት እምኔሁ ወወለደት ወልደ። ወኮነ ሥጋሁ ጸዐዳ ከመ አስሐትያ ወቀይሕ ከመ ጽጌ ረዳ፤ ወጸጕረ ርእሱ ከመ ፀምር ጸዐዳ፣ ወድምድማሁ ወሠናይ አዕይንቲሁ። ወሶበ ከሠተ አዕይንቲሁ አብርሃ ኵላ ቤተ ከመ ፀሐይ ወፈድፋደ በርሀ ኵሉ ቤት። ወሶበ ተንሥአ እምእዴሃ ለመወልዲት ከሠተ አፉሁ ወተናገረ ስብሐቲሁ ለእግዚአ ጽድቅ። ... ወፈርሀ ላሜህ አቡሁ እምኔሁ ወጐየ ወመጽአ ኀበ አቡሁ ማቱሳላ። ወይቤሎ አነ ወለድኩ ወልደ ውሉጠ ወኢኮነ ከመ ሰብእ ወይመስል ደቂቀ መላእክተ ሰማይ ወፍጥረቱ ካልዕት ወኢኮነ ከማነ፤ ወአዕይንቲሁ ከመ እገሪሁ ለፀሐይ ወገጹ ስቡሕ...(ሄኖክ 106፥1-5)*

*ትርጉም፡- ... ከዘመናት በኋላ ልጅ ማቱሳላ ለልጁ ሚስት ወሰደ። ከእርሱም ፀነሰች፣ ልጅም ወለደች። ሥጋው እንደ አመዳይ ነጭ፣ እንደ ጽጊረዳ ቀይ ሆነ። የእራሱ ፀጉርም እንደ ነጭ ግምጃ ነው። ቅንድቡና ዓይኖቹ ጥሩ ናቸው። ዓይኑን በገለጠ ጊዜ ቤቱን ሁሉ እነደ ፀሐይ አበራው። ቤቱ ሁሉ ፈጽሞ በራ። ከአዋላጅቱ በተነሳ ጊዜ አፉን ከፈተ፣ ምስጋና ለእውነት ጌታ ብሎ ተናገረ። ... አባቱ ላሜህ ፈራ፣ ከእሱም ሸሸ። ወደ አባቱ ወደ ማቱሳላም መጣ ። ለአባቱም አለው የተለየ ልጅ ወለድኩ። እንደሰው አይደለም። የሰማይ መላእክት ልጅ ይመስላል አፈጣጠሩም የተለየች ናት። አንደኛ አይደለም ዓይኖቹ እንደ ፀሐይ እግሮች ናቸው ፊቱም ብሩሕ ነው (ሄኖክ 106፥1-5)*

ነቢዩ ሙሴ በተወለደ ጊዜም እንዲኹ ተመሳሳይ ታሪክ እንደነበረው መተርጕማነ መጻሕፍት ያስረዳሉ[34]። ይኹን እንጅ በነዚኽ በኹለቱ አባቶች የልደት ቀን ማርና ወተት፣ ዳቦም አልቀረበም። በኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን ግን የተወለደባት ቦታ ቤተ ልሔም በብርሃን ከመሞላቷ ባሻገር[35] ወንዞች ወደ ወተትና መዓር፣ ተራሮችም ወደ ኅብስት እንደ ተቀየሩ ትውፊት ያስረዳል። ይህንኑ የዜማው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ "በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ አድባር ኮኑ ኅብስተ ሕይወት፡ ወዕፀወ ገዳምኒ ፈረዩ አስካለ በረከት፤ ማየ ባሕርኒ ኮነት ሐሊበ ወመዓረ..."[36]በማለት በልደት ዝማሬው አካቶታል።

# ፰. ማጠቃለያ

በዚኽ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው መጽሐፈ ሄኖክ በግዕዝ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍ እና በቅኔ ውስጥ በጣም ሰፊ ቦታ ይዞ የሚገኝ ነው። ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በስፋት አጥንተውታል፤ ተርጉመውታል፤ ተመራም

[34] ዘፀ. 2፥2 (መጻሕፍተ ብሉያት ፪ቱ እሉ እሙንቱ ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደት) ኦሪት ዘፀአት (አንድምታ ትርጓሜ)፣ . (1999)፣አዲስ አበባ፣ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።

[35] ሉቃ. 2፥9

[36] ያሬድ (ቅዱስ)፣ (1986)፣ *ዝማሬ መዋሥዕት፣* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።

ረውበታል፡፡ ነገረ እግዚአብሔርን፣ ነገረ-ማርያምን፣ ነገረ-መላእክትን ለመማርና ለማስተማር በጽሑፎቻቸው ውስጥ ጠቅሰውታል፡፡ እንዲኹም ስለ ሥነ-ፍጥረት (ስለ ፀሐይ፣ጨረቃ እና ከዋክብት)፣ስለ መልክዓ ምድር (ለምሳሌ የገነት መገኛ አቅጣጫ)፣ ልዩ ልዩ መዓዛ ስላላቸው ዕፅዋት ወዘተ ለመግለጽ ሊቃውንቱ መጽሐፈ ሄኖክን ተጠቅመዋል፡፡ በተጨማሪም ሰዎች ከክፉ ሥራ (ለምሳሌ ከጥንቆላና ከሟርት) እንዲርቁ አስተምረውበታል፡፡

ይኹን እንጂ ይኽንን ብርቅየ የኾነ የሀገራችን ብሎም የዓለማችን የሥነ-ጽሑፍ  ሀብት የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሊቃውንት እንዴት እንዳጠኑት የሚያሳይና ላሁኑ ዘመን ትውልድ ለማስተዋወቅ የሚደረግ ሳይንሳዊ የጥናት ትኩረት በተገቢው ደረጃ ያገኘ አይመስልም፡፡ ይልቁንም በተዛማጅ ሥራዎች ዳሰሳ ላይ እንደተገለጸው የመጽሐፉ ይዘት ያልገባቸውና ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎች መጽሐፉን የጥንቆላና የኮከብ ቆጣሪዎች (ሟርተኞች) መጽሐፍ አድረገው ሲቆጥሩት ይታያል፡፡ ከዚኽም አልፈው የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ደምራ የክብር ቦታ የሰጠችው ትምህርተ ሃይማኖት ስለሚያንሳትና የቀኖና መጻሕፍትን መለየት ስለማትችል ነው ብለው በድፍረት ጽፈዋል፡፡ ይኽ ግን ፍጹም ስሕተት ነው፡፡ ስለ ነገረ እግዚአብሔር፣ ነገረ ማርያም፣ ነገረ መላእክት ምሥጢራተ ብርሃናትንና ልዩ ልዩ መንፈሳዊም ኾነ ዓለማዊ ዕውቀቶችን የያዘን መጽሐፍ እንደ ኢምንት ከመቁጠር ይልቅ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ማጥናትና መመርመር አስፈላጊ ነው ብየ አምናለሁ፡፡

# የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊ ፎክሎር

*በ ፍሬሕይወት ባዩ* [37]

## Abstract

The focus of this study is to show the relics used by the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church (EOTC) in terms of religious folklore. Two churches from Addis Ababa Diocese and two churches from Arsi Diocese were selected for the study. The main purpose of the study was to analyze the scriptures from a religious point of view. The data was collected through observation, interview, and documentary data collection methods. Sanctification means: They are the various properties or resources of the church in which the various spiritual and divine services of God are performed. While the rules governing the EOTC are the same, sometimes the written rules and regulations apply differently. The fact that the church written law is unenforceable and shows that religious folklore implements the practice without changing the rule formally. If the EOTC can create a way for the sacraments to be completely self-sufficient according to the canon, or if it is established that they are orthodox traditions and canons before they are used, it may be a solution to the conflict.

[37] *ፍሬሕይወት ባዩ (ዶ/ር) (በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ የፎክሎር ተመራማሪ)።*

# አኀፅሮተ ጽሑፍ

የዚኽ ጥናት ትኩረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን (የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ) የምትገለገልበትን ንዋያተ ቅድሳት ከሃይማኖታዊ ፎክሎር አንጻር ማሳየት ነው። ለጥናቱ መረጃ ለማሰባሰብ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ኹለት ከአርሲ ሀገረ ስብከት ኹለት አድባራት ተመርጠዋል። የጥናቱ ዋና ዓላማ ንዋያተ ቅድሳትን ከሃይማኖታዊ ፍክሎር እሳቤ አኳያ መተንተን ነው። መረጃዎቹ በምልከታ በቃለ መጠይቅ እና በሰነድ ምርመራ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኙ ናቸው። ንዋያተ ቅድሳት ማለት፤ የተለያዩ መንፈሳዊና መለኮታዊ የኾነው የእግዚአብሔር ቅዱስ አገልግሎትና ሥርዓት አምልኮ የሚፈጸምባቸው የተለዩ የቤተ-ክርስቲያን ንብረቶች ወይም ሀብቶች ናቸው፡፡ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የምትተዳደርበት ሕግ አንድ ኾኖ ሳለ የተጻፈው ደንብ እና የሚተገበረው የተለያየ መኾን ይስተዋላል። የተጻፈው ሕግ ሳይሻር በተግባር የሚታየው ከሕጉ ውጪ መኾኑ ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ያሳያል፡፡ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ በቀኖናው መሠረት ንዋያተ ቅድሳቱን ሙሉ በሙሉ ራሷን ችላ መሠራት የምትችልበትን መንገድ ብትፈጥር ወይም የተሠሩት ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትንና ቀኖናቸውን የጠበቁ ስለመኾናቸው ብታረጋግጥ ለተቃርኖው መፍትሔ ሊኾን ይችላል።

# 1. መግቢያ

ጥናቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ)ንዋያተ ቅድሳት በሚል መጠሪያ የሰየመችውንና ደንብ አውጥታ የምትገለገልባቸውን ቁሶች የሚመለከት ነው። ይኸ ጥናት በይበልጥ ትኩረት አድርጎ የሚመለከተው፤ ንዋያተ ቅድሳቱ ሃይማኖታዊ ደንብና መመሪያቸው በተግባር የተሻረ መኾናቸው ላይ ነው። ንዋያተ ቅድሳት ሲሠሩና አገልግሎት ላይ ሲውሉ ሃይማኖታዊ ደንብና መመሪያን ሽረው መመልከት በፎክሎር የጥናት መስክ ሃይማኖታዊ ፎክሎር በሚባል የጽንሰ ሐሳብ ትኩረት የሚጠና ነው።

ንዋያተ ቅድሳትን በተመለከተ ይኸ ጥናት ከመደረጉ ቀደም ብሎ[38] የተለያዩ ግለሰቦች በተለያየ ምክንያት አጥንተዋል፤ ጽፈዋል። ንዋያተ ቅድሳትን በተመለከተ ለዚኽ ጥናት የዳሰሳ ንባብ ሲደረግ ከተገኙት መካከል ቀዳሚው ሥራ ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ በ1963 ዓ.ም የተጠናው ነው[39]። ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ንዋያተ ቅድሳቱን በስም በመጥቀስ አገልግሎታቸውን እና ቅርጻቸውን በሥዕል አስደግፎ በገለጻ ማቅረብ ላይ ነው። ኹለተኛው በ1996 ዓ.ም "ኖኅተ ሰማይ" በሚል ርእስ የተጻፈ መጽሐፍ ነው[40]። የዚኽ መጽሐፍ ትኩረት ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊ ይዘታቸውን በተመለከተ የእያንዳንዱን ንዋያተ ቅድሳት ምንነት፣ ተግባር፣ ሃይማኖታዊ ተምሳሌት ፎቷቸውን ጭምር በዝርዝር ያስረዳል። ኹለቱም ሥራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና ንዋያተ ቅድሳት የሚለውን ርእሰ ጉዳይ ይዘው መነሣታቸው ነው። ልዩነቱ ኹለቱም በሃይማኖታዊ ይዘቱ ላይ ብቻ ያተኩራሉ። የዚኽ ጥናት ትኩረት ደግሞ ኹሉንም ንዋያተ ቅድሳት መዘርዘር ሳይኾን ከሃይማኖታዊ ፎክሎር ጽንሰ ሐሳብ አኳያ ቁሶቹ ሲሠሩ፣ አገልግሎት ላይ ሲውሉ በማየት የሚገለገሉባቸውን በመጠየቅ ሃይማኖታዊ ደንቡን ያልተከተሉት ላይ ብቻ ያተኩራል።

[38] ይኸ ጥናት ለዚኽ መጽሔት እንዲኾን ተጨማሪ መረጃ እና ሐሳብ ታክለበት እንጂ ቀደም ብሎ፤ "የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ንዋየተ ቅድሳት ፎክሎራዊና ሃይማኖታዊ ገጽታ" በሚል ርእስ በ2000ዓ.ም (በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር" ለኹለተኛ ድግሪ ማሟያ) የተጠና ነው። እንዲኹም በኋላ ርእሰ ጉዳዩን በተለያየ መልኩ አስፍቶ በማጥናት መቐለ ዩንቨርሲቲ ያሬድ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥነ-ጽሑፍና ብራና ጥናቶች ማእከል ግንቦት 8/2009ዓ.ም በዚኽ ጽሑፍ አቅራቢ ለመድረክ ቀርቦ ነበረ።

[39] ዐብይ ፍትሐአወቅ፣ "ንዋየ ቅድሳት" (ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1963ዓ.ም)።

[40] ያሬድ ገ/መድህን፤ ኖኅተ ሰማይ፤ (ዐዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፤ 1996 ዓ.ም)።

የጥናቱ ዓላማ፤ የጥናቱ ዋና ዓላማ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ንዋያተ ቅድሳትን ከሃይማኖታዊ ፎክሎር አንጻር ማሳየት ይኾናል። ዝርዝር ዓላማዎቹ፡-ሃይማኖታዊ ፎክሎር የሚታይባቸውን ንዋያተ ቅድሳት መለየት። እንዲኹም ንዋያተ ቅድሳትን ከሃይማኖታዊ ፎክሎር ትኩረት አኳያ መተንተን የሚሉ ናቸው።

የጥናቱ ጠቀሜታ፤ ለኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ንዋያተ ቅድሳት ያሉበትን ኹኔታ ይጠቁማል። የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ንዋያተ ቅድሳት በተመለከተ የቁሶቹን ቅርጽ፣ ማን መቼ እንዴት አገልግሎት ላይ ማዋልና መጠቀም እንደሚችል ምክንያቱን ጭምር በማብራራት ሃይማኖታዊ ደንብ ደንግጋላቸዋለች። ይኽንንም ደንብ በኹሉም አብያተ ክርስቲያናት በተግባር እንዲውሉ ታዛለች። ኾኖም ቤተ ክርስቲያኗ ሰፊ አገልግሎት ከመስጠት እና ንዋያተ ቅድሳቱ ለረዥም ዘመናት አገልግሎት ሲሰጡ በመኖራቸው በተለያየ ምክንያት ለውጦች ይታዩበታል። እነዚኽን ለውጦች ርእሱ በፈቀደ መጠን በዚኽ ጥናት የሚታዩ ይኾናል። ስለዚኽ በንዋየ ቅድሳቱ ላይ የሚታዩት ለውጦች ምን እንደኾኑ ምክንያቱን በመለየት መፍትሔ ለመስጠት ይኽ ጥናት ጠቀሜታ አለው።

የጥናቱ ዘዴ፤ የንዋያተ ቅድሳቱን አሠራር አጠቃቀም፣ አያያዝና የት እንደሚገኙ ለመወሰን አሳሽና ገላጭ ዘዴዎች ተግባራዊ ኾነዋል። ለጥናቱ መረጃ የተሰባሰበው ከኹለት አህጉረ ስብከት ነው። አንዱ ከአርሲ ሀገረ ስብከት፤ በቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ሌሙ ማርያም ሲኾን። ኹለተኛው ደግሞ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም እና ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ነው።

የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የራሷ የኾነ ወጥ ዶግማ፣ ቀኖና፣ ሥርዓትና ትውፊት ያላት እነዚኽ ሃይማኖታዊ መመሪያዎቿ በማዕከላዊው ሲኖዶስ የሚዘጋጁና ለኹሉም አጥቢያ አብያተ-ክርስቲያን የሚደርሱ በመኾኑ አንዱን ቤተ-ክርስቲያን ብቻ በመመልከት ጥናቱን ማከናወን ይቻላል። ለዚኽ ጥናት አራቱ (ከከተማ እና ከገጠር ማቀላቀል ያስፈለገው) የጥናቱ ዓላማ ለኾነው ሃይማኖታዊ ፎክሎር ትንተና አስፈላጊ በመኾኑ ነው። ምክንያቱም ሃይማኖታዊ ፎክሎር ትኩረቱ ንዋያተ ቅድሳቱ በጽሑፍ የሰፈረ ሃይማኖታዊ ዝርዝር መመሪያ ምን ያኽል ተግባራዊ እንደኾነ ማየት በመኾኑ አራት አብያተ ክርስቲያን ተመርጠዋል። አራት አጥቢያ አብያተ-ክርስቲያን ከኹለት አህጉረ ስብከቶች ለመምረጥ፤ አብያተ-ክርስቲያኒቱን በቅርበት ማወቁና ተጠቃሚዎችን በቀላሉ ለማግኘት መፈለጉ የምቾት ናሙና ሲኾን ንዋየ ቅድሳቱ በተግባር ላይ ሲውሉ ለመመልከት የተለያዩ አህጉረ ስብከቶች ገጠርና ከተማ ማቀላቀሉ ደግሞ የዒላማ ናሙና ነው፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ፤ ለጥናቱ አስፈላጊ ኾነው የተገኙት ከአራቱ አብያተ ክርስቲያን አንድ አንድ ካህን በአጠቃላይ አራት ካህናትና ኹለት ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን በዓላማ ናሙና ለቃለ-መጠይቅ ተመርጠዋል፡፡ ለቃለ-መጠይቅ የተመረጡበት

ምክንያት የንዋያተ ቅድሳቱ ጠባቂዎችና ኀላፊዎች እነርሱ በመኾናቸው በህልውናቸውና በጠቀሜታቸው ላይ የተሻለ ዕውቀትና ልምድ ስለሚኖራቸው የጥናቱን ዓላማ ያሳካሉ። ኹለቱ ሊቃውንት ከንዋየ ቅድሳት ጋር ዝምድና ያላቸው ጽሑፎች በመጻፍና በማስተማር ጥልቅ የኾነ ዕውቀት አንዳላቸው በስሚ ስሚ (snow ball) ናሙና አወሳሰድ የተመረጡ ናቸው።

መረጃ ለማግኘት ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና የሰነድ ምርመራ፤ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ምልከታ የተደረገባቸው በተመረጡት አብያተ ክርስቲያን፤ ንዋያተ ቅድሳት አገልግሎት ላይ ሲውሉ፣ እንዲኹም በዕቃቤቶች እና በሙዝየም የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳትን ናቸው። በምልከታ ወቅት ጥያቄ የፈጠሩ ሐሳቦችን ከካህናቱ እና ከሊቃውንቱ በመጠየቅ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል። በሰነድ ምርመራ ወቅት በጽሑፍ ስለሰፈሩት ንዋያተ ቅድሳት ደንብ በተግባር ከሚታየውና ከሚተገበረው ጋር በተዛመደ ለጥናቱ የተዘጋጁ ጥያቄዎች ከእያንዳንዱ መረጃ ሰጪ ጋር አጥኚዋ በአካል በመገኘት በመጠየቅ ምላሽ አግኝተዋል። በኹለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኙት መረጃዎች የጥናቱ ዋነኛ አካል ኾነው በዚኽ ጥናት ውስጥ ቀርበዋል።

# 2. የጽንሰ ሐሳብ ማዕቀፎች

## 2.1 ንዋያተ ቅድሳት

ንዋያተ የንዋይ ብዙ ቍጥር ነው፡፡ ንዋይ ገንዘብ ማለት ነው፡፡ ቅዱሳት ደግሞ ቅዱስ የሚለው ብዙ ቍጥር ነው፡፡ ቅዱስ ማለት ደግሞ የተለየ፣ የተከበረ፣ የተመረጠ ማለት ነው፡፡ ንዋያተ ቅድሳት ማለትም በቤተ-ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት የሚፈጸምባቸው የተቀደሱ ዕቃዎች ማለት ነው፡፡[41] ስለዚኽ ንዋይ ገንዘብ፣ ቅዱስ ደግሞ ልዩ የሚል ፍቺ በመያዝ ንዋያተ ቅድሳት ይኾናል። ንዋያተ ቅድሳት ሲባል ከመሰል ቁሶች ልዩ የኾነ በካህን የተባረከና ተለይቶ ለተቀደሰው አገልግሎት ብቻ የሚውል ማለት ነው። ኾኖም ቁሱን ልዩ ያደረገው ለአገልግሎት ከመዋሉ በፊት የሚደረገው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው። የሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ዋነኛ መሠረትም መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ለምሳሌ፡-

የመገናኛውንም ድንኳን፣ የምስክሩንም ታቦት፣ ገበታውንም፣ [ዕ]ቃውንም ኹሉ መቅረዙንም፣ የዕጣን መሠውያውንም፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚኾነውን መሠውያና

[41]. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ መዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ (ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948ዓ.ም)፣ ገጽ 632።

[ዕ]ቃውንም ኹሉ የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውንም ትቀባበታለህ፡፡ ኹሉንም ትቀድሳቸዋለህ፣ ቅዱሳተ ቅዱሳንም ይኾናሉ፣ የሚነካቸውም ኹሉ ቅዱስ ይኾናል፡፡[42]

የብሉይ ኪዳንን መሠረት በማድረግ በሐዲስ ኪዳንም ንዋያተ ቅድሳት የሚባሉት ቅብዐ ቅዱስ[43] የተቀቡ ወይም በቅባት እና በቡራኬ የከበሩ ንዋያት ናቸው።

ወንጌላዊው ‹‹ደቀመዛሙርትማ መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ፡፡›› (የሐዋ. 11÷ 26) እንዳለው ቤተ-ክርስቲያን በአንጾኪያ ከተመሠረተች በኋላ የክርስትና እምነት ተከታዮች ቍጥራቸው ዕለት ተዕለት ይበዛ ነበር። የክርስትና እምነት ተከታይ ከኾኑት መካከል የተለያየ ሙያ ያላቸው ምእመናን ነበሩ። እነዚኽ ምእመናንም የቤተ-ክርስቲያን ምሥጢራት መገለጫ መገልገያ ዕቃዎችን ሠሩ፡፡ “የቤተ-ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ጻሕል፣ ጽንሐሕ፣ መስቀል እነርሱንም የመሳሰሉት ኹሉ ተሠሩ፡፡”[44]

ንዋያተ ቅድሳትን መሥራት ያለባቸው የተመረጡ የተሾሙና ጥበቡ ያደረባቸው ሰዎች ናቸው፡፡ በብሉይ ኪዳን እንደነ ባስልኤልና ኤልያብ በእግዚአብሔር ተመርጠው “ጥበቤን በጥበበኞች ልብ አሳድራለሁ” ባለው መሠረት የተሾሙ ሰዎች መሥራት አለባቸው፡፡ በሚሠሩበት ጊዜ ምሳሌነታቸውንና የሚሰጡትን አገልግሎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ቅርጾችንና መልኮችን በማውጣትና በማስዋብ ይኾናል። የቤተ-ክርስቲያንን የአምልኮና ቀኖና ትውፊት ያልጠበቁ ዕቃዎች እንዲኹ ተሰብስበው ንዋያተ ቅድሳት አይኾኑም፡፡ ስለዚኽም ከመባረካቸው በፊት ይኽ ኹኔታ ይረጋገጣል፡፡ ትክክለኛ መኾናቸው ከታወቀ በኋላ ተባርከው ተገቢው ጸሎት ተደርሶላቸው ሜሮን ይቀባሉ፡፡ በሜሮንም ይከብራሉ፡፡[45]

አዲስ የተሠራ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ከኾነ ንዋያተ ቅድሳት በኹለት መልኩ ይባረካሉ፡፡ በተናጠልና በጋራ ጸሎታቸውም የተለያየ ነው ለምሳሌ ለጻሕል የሚደረግ ጸሎት፡-

> ኹሉን የሚይዝ እግዚአብሔር ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያኑን በንጽሕና ያጸናት ካህናቱንም ንዋያተ ቅድሳቱንም ቸር የምትኾን አብ ሆይ ከቸርነትህ እንለምንሃለን፡፡ ሰው ወዳጅ

---

[42]. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘጸ. 30፥26-30።

[43] ቅብዐ ቅዱስ - የተባረከ ቅባት በቤተክርስቲያን ለሥርዓተ ክርስትና መፈጸሚያ የሚያገለግል ከልዩ ልዩ ዕፅዋት ተቀምሞ የሚሠራ የሽቱ ዓይነት፡፡

[44] ሉሌ መልአኩ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ (ዐዲስ አበባ፤ 1996ዓ.ም)፣ ገጽ 40።

[45] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘጸ. 40።

ሆይ ፊትህን ግለጽልን ባርከንም፡፡ ይኸችንም ያኽል ለሥርዓትና ለንጽሕና እንድትኾን ባርካት፡፡ የአንድ ልጅህን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውን ያደርጉባት ዘንድ ይኸች ጻሕል የንጽሕና ጻሕል የበኍነትም ጻሕል ትኾን ዘንድ በርስዋም ላይ የአንድ ልጅህ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው ይቀመጥ ዘንድ ከአንድ ልጅ ለሚገኝ ኃጢአት ስርየት አሜን።[46]

ከዚኽ በኋላ ካህኑ ሜሮኑን አንሥቶ ጻሕሉን በትእምርተ መስቀል በአራት ማዕዘን ውስጡንና ዙሪያውን ይባርከዋል፡፡ በዚኽ ዓይነት መልኩ ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት ለየራሳቸው የተዘጋጀው ጸሎት እየተጸለየላቸው በካህኑ እጅ በቅብዐ ቅዱስ በመስቀል አርአያ እየተባረኩና እየተቀቡ ይቀደሳሉ፡፡ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ንዋያተ ቅድሳት ይባላሉ፡፡ ከቤተ-መቅደሱ አገልግሎት ውጭ ሌላ ምንም ነገር አይደረግባቸውም፡፡ ስማቸውና ትርጉማቸውም ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር የተያያዘ ይኾናል፡፡ ኹሉም በአዲስነታቸው ከተባረኩ በኋላ በየጊዜው አገልግሎት ሲሰጡም እንዲሁ ካህኑ በንጽሕና መጠበቃቸውን እያረጋገጠ ይባርካቸዋል፡፡ ለኹሉም ንዋያተ ቅድሳት የሚጸለይና በተናጠል ለእያንዳንዱ የሚጸለይ ተብሎ ይከፈላል፡፡ ለአዲስ ንዋያተ ቅድሳትና አገልግሎት መስጠት ለጀመሩት ጸሎት ያስፈለገበትን ምክንያት ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> ንዋያተ ቅድሳት ከገበያ ተገዝቶ ሲመጣ የሚደረገው ጸሎት ሙሉ ለሙሉ ለውጥን የሚጠይቅ ጸሎት ነው፡፡ ምክንያቱም በረከሰ ወይም በቆሻሻ ቦታ የዋለ ያደረ የቆየ ዕቃ ስለኾነ ይኸንን ዕቃ ከርኩሰት ወደ ቅድስና ለመለወጥ የሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ ይኸኛው ደግሞ ለጊዜው በዲያቆን እጅ ስለተነካ፣ በዲያቆናዊት እጅ ስለተነካ ያንን መጠነኛ ርኩሰት ለመለወጥ የሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ ስለዚኽ ኹለቱ ጸሎታት ይለያያሉ፡፡[47]

ንዋያተ ቅድሳት ለተለየ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ስለኾነ ማንም ለግሉ ወይም ለቤት ውስጥ አገልግሎት እንዲፈጸምባቸው፣ አስመስሎም እንዲሠራ አይፈቀድለትም፡፡ ይኽን አድርጐም ቢገኝ ስሕተተኛና በደለኛ ይኾናል፡፡ የባቢሎን ንጉሥ ብልጣሶር ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የዘረፋቸውን ንዋያተ ቅድሳት በድፍረት ለመኳንንቶቹና ሚስቶች እንዲጠጡባቸው በማዘዙ እንደተዋረደና እንደተነቀፈ መንግሥቱም ከእርሱ እንደተወሰደች እንዲኹ መርገም ይኾንበታል[48]።

---

[46] ዳንኤል ሰይፈ ስላሴ፣ "ንዋየ ቅድሳትና የመስቀል 'የንዋያተ ቅድሳት' የቅዱሳን መጻሕፍት ሥርዓት"፣ (1994) ያልታተመ፣ ገጽ 4::

[47] Ibid

[48] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ት.ዳን. 5፥25-31።

የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት የሚተላለፍባቸው ቁሳዊ ሀብቶች ስለኾኑም በቤተ-ክርስቲያን ለእነርሱ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ በክብርና በንጽሕና ይቀመጣሉ አገልጋዮች "ወደ ውጭም ወደ አደባባይ በሚወጡበት ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን ያውልቁ፤ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ውስጥ ያኑሩት..."።[49]

## 2.2 ፎክሎር

ፎክሎር "ፎክ እና ሎር" የሚሉ ኹለት ቃላት ቅንጅት ነው፡፡ "ፎክ አንድ የጋራ ነገር ያላቸው የትኛውንም የሰዎች ስብስብ ይመለከታል።" ፤ "ሎር ደግሞ የጋራ የኾነውና የሚያገናኛቸው ጉዳይ ነው። ሰዎችን ከሚያገናኛቸው ጉዳይ ወይም "ሎር" አንዱ ትውፊት(tradition) ነው፡፡[50] ለምሳሌ በዚኽ ጥናት የፎክ ቡድን የሚባሉት የጋራ ጉዳያቸው ሃይማኖት ኾኖ የተሰባሰቡ ሰዎች ናቸው፡፡

ንዋያተ ቅድሳቱ ከቁስነታቸው ባሻገር በሚሰጡት አገልግሎት በሃይማኖት ዐይን መታየት ይገባቸዋል፡፡ ሃይማኖት በራሱ አንድ የጥናት መስክ ሲኾን ፎክሎር ደግሞ ከታሪክና ተጨባጭ ኹኔታዎች ጋር ተያይዞ የሚሰፋና የሚለጠጥ ልዩ የኾነ ኺደት ነው፡፡[51] በተለይ የሃይማኖትና ፎክሎርን ግንኙነቱንና ልዩነቱን በስፋት መመልከቱ ለዚኽ ጥናት ወሳኝ ጉዳይ ነው።

## 2.3 ሃይማኖታዊ ፎክሎር

"ሃይማኖታዊ ፎክሎር ሃይማኖታዊ ልማድንና ሃይማኖታዊ ያልኾነ ልማድን የሚመረምሩበት መነፅር ነው፡፡[52]" ሃይማኖታዊ ፎክሎር ሀገረ-ሰባዊ ልማድንና በሃይማኖት ሥርዓቶች መካከል ያለውን ቁርኝት ያሳያል። ትኩረቱ በታወቁት የሃይማኖት መጻሕፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጭ፣ ሰዎች በየራሳቸው (የሃይማኖቱ አማኝና ተከታይ መኾናቸው ሳይቋረጥ ማለት ነው) በሚከተሏቸው እምነቶችና በሚፈጽሟቸው እምነታዊ ድርጊቶች ላይ ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ ከንዋያተ ቅድሳቱ መካከል ሃይማኖታዊ ግልጋሎቱ ሳይቀር፣ ሃይማኖታዊ ደንቡ ሳይለወጥ በተለያየ ምክንያት

[49] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ሕዝ.44፣18።

[50] Dundes, A.The study of Folklore, (Prentice-Hall, Inc, Engle wood, cliffs, N.J,1965), pp 2.

[51] Mathisen S. "Folklore" in Fekade Azeze, "Teaching Material selected and compiled riders for EtLi 621" of Ethiopian languages and literature, M.A. in Ethiopian literature and Folklore, 2003.

[52] Larry, D. "Religuse folklore", in Fekade Azeze, "Teaching Material selected and compiled, riders for EtLi 621" of Ethiopian languages and literature MA in Ethiopian literature and Folklore, 2003.

ከደንቡ ያፈነገጡ ንዋያተ ቅድሳትን ለመመልከት የሚያስችል የጽንሰ ሐሳብ መነሻ ነው።

ሃይማኖታዊ ፎክሎር በተለያዩ ሃይማኖታዊ ቡድኖች ውስጥ ሊገኝ ይችላል። በታወቀው ሥርዓተ አምልኮ ወይም ከታወቀው ሥርዓተ አምልኮ ውጭ ዶክትሪኑ የሚያዘውን ሊያሟላ አንዳንዴ ሊቃረን፣ እንዲኹም ልዩ ልዩ የተዛመዱ ዘውጎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ተመሳስሎውን ወይም ተቃርኖውን አልያም ዝምድናውን ለመለየት ሃይማኖታዊ ደንቡን እና ተግባራዊነቱን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ለመመርመር መነሻው ሃይማኖታዊ ይዘቱ መኾን አለበት።[53] የሃይማኖታዊ ፎክሎር ጽንሰ ሐሳብን በመያዝ በዚኽ ማዕቀፍ ውስጥ ሊታዩ የሚችሉትን ንዋያተ ቅድሳት ብቻ ይዳሰሳሉ። ንዋያተ ቅድሳቱ ያላቸውን ሃይማኖታዊ ይዘት በቅድሚያ በመግለጽ፣ ፎክሎራዊ መልኮቹን ደግሞ በማስከተል የሚተነተን ይኾናል።

# 3. የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊ ፎክሎር

ንዋያተ ቅድሳት የምንላቸው በጥቅሉ ከሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ጀምሮ መገልገያ ቁሶቹን በሙሉ ነው። የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የምትገለገልበት ንዋያተ ቅድሳት የአሠራሩን መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በተግባር የሚሠሩት የሃይማኖቱ ተከታዮች ወይም ጥበቡ ያላቸው ግለሰቦች ሲኾኑ ለንዋያተ ቅድሳቱ መሥሪያ የሚውለው ጥሬ ዕቃ በአብዛኛው በሀገራችን የሚገኝ ነው።[54]

የንዋያተ ቅድሳት አጠቃላይ ዝርዝሮቹን ስንመለከት፡- ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን እና በሮቹ፣ ጉልላት፣ ሻኩራዎች፣ በአጸድ ውስጥ የሚገኙ ቤተ-ልሔም፣ ግብር-ቤት፣ ክርስትና-ቤት፣ ደወልና ሌሎችም ይገኙበታል። በሕንጻ ቤተ-ክርስቲያኑ ሦስት ክፍል (ቅድስት[55]፣ መቅደስ[56]እና ቅኔ ማሕሌት[57]) ከነመገልገያ ቁሶቹ ንዋያተ ቅድሳት ናቸው። ከእነዚኽህም፤ በቅኔ ማሕሌት፡- ለመዝሙር አገልግሎት የሚውሉ ንዋየ ቅድሳት ከበሮ፣ ጸናጽል፣ መቋምያ፣ ሥዕላት፣ መጻሕፍት፣ አትሮንስ፣ መቅረዝ እና መጋረጃ ናቸው።

[53] Ibid.

[54] ፍሬሕይወት ባዩ። "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ"ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለ ኤም ኤ. ዲግሪ ማሟያ በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር፤(አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 2000)፣ ገጽ 63።

[55] ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉ ምእመናን፣ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት የሚፈጽሙ ሙሽሮችና ከቀዳስያን ውጪ ያሉ ካህናት ተሰጥኦ በመቀበል ቆመው የሚያስቀድሱበት ክፍል ሲኾን ማንኛውም ምእመን እዚኽ መቆም አይችልም።

[56] በብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን በመባል የሚታወቅ ሲኾን ሦስት በሮች አሉት፡፡ በሦስቱም በሮች ላይ መጋረጃ እኩል ይጋረዳል፡፡ መሥዋዕት የሚቀርብበት ታቦተ ሕጉ የሚቀመጠው በዚኽ ክፍል ሲኽን ከካህናት በስተቀር ማንም አይገባም፡፡ ካህናትም የሚገቡት ለአገልግሎት ብቻ ነው(የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን፣ 1994፡26)፡፡

[57] ወደ ቤተ-ክርስቲያን የውስጥ ክፍሎች ስንገባ የመጀመሪያው ክፍል ቅኔ ማሕሌት ይባላል፡፡

በመቅደስ አገልግሎት የሚሰጡ ንዋየ ቅድሳት በርካታ ናቸው። እነዚኽም፡-ታቦት፣ ልብሰ ተክህኖ፤ ዘውድ፣ መንበር፣ ጽዋዕ፣ ዕርፈ-መስቀል፣ ጻሕል፣ ዐውድ፣ አጎበር፣ መነሳነስ(ጭራ)፣ መሶበ ወርቅ፣ ብርት፣ ሰን፣ ጽንሐሕ፣ ሙዳይ፣ መጎናጸፊያ፣ ቀጸላ፣ ቃጭል፣ መስቀል(የመጾር መስቀል)፣ ማኅፈድ፣ ጥላና ሌሎችም ይገኙበታል። ጥላ፣ ቃጭልና ሌሎችም በቅኔ ማሕሌትና በመቅደስ እየተዘዋወሩ አገልግሎት የሚሰጡ ሲኾኑ በተለያዩ ዓመታዊ ክብረ በዓላት ላይ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ንዋያተ ቅድሳትም አሉ።

## 3.1 የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር ቅርጽ

ከንዋያተ ቅድሳት መካከል አንዱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ነው። የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር ቅርጽ የተለያየ ነው፡፡ "በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሦስት ዓይነት የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር አሉ፡፡ እነዚኽም ሰቀላማ፣ ክብ(ቤተ-ንጉሥ) እና ፍልፍል፡፡"[58] በዚኽ መሠረት የአራቱን ቤተ-ክርስቲያን ቅርጽ ስናይ ሶስቱ ክብ ሲኾኑ የውስጥ ክፍላቸው ቅድስት መቅደስና ቅኔ ማሕሌት አላቸው። ለሐዲስ ኪዳን ቤተ-ክርስቲያን መሠረቱ ብሉይ ኪዳን ነውና ሦስት ክፍል መኾኑና ክብ መኾኑ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ምሳሌ ነው፡፡ የሐዲስ ኪዳን ቤተ-ክርስቲያን በፊልጵስዩስ የተሠራችው ክብ ነበረች፡፡ ክብ መኾኗም የፍጹምነት ምሳሌ ነው፡፡

"ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ሲታነጽ ምሥጢር እንዳይፋለስ፣ አሠራሩ ትርጉም አልባ እንዳይኾን አበው ይጠነቀቁበታል፣ ቅርጹ ከክርስቶስ የዓለም ቤዛነት ጉዞ፣ ከቅዱሳን መላእክት አገልግሎትና ተጋድሎ ጋር እንዲያያዝ ኾኖ ነው፡፡[59]" የሦስቱን ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ክብ የመኾንና በውስጥ ክፍሎቻቸው ክፍፍል እንዲኾም ከውጭ ያሉትን ጉልላት እና ሻኩራ ምሳሌነት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የበቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ክብ አይደለም፤ የውስጥ ክፍሎቹ ኹለት ሲኾኑ ጉልላትና ሻኩራም የለውም። ክብ ላለመኾኑ እና ኹለት ክፍል ለመኾኑ ምክንያት የኾነው የቀድሞዎቹ ሕንጻ አብያተ-ክርስቲያን አርጅተው በምትካቸው አዲስ ሲሠራ ክብ የነበረ ቅርጻቸው ይቀየራል። የደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንም በዚኹ ምክንያት ቅርጹ ተቀይሯል። የቀድሞ ክብ እና ባለሦስት ክፍል ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ለምን እንደተቀየረ የአዲሱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሲጣል የነበሩት የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሲገልጹ፡_ "ዘመናዊ የኾነው የቤተ

58 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን፣ ትላንትና ዛሬና ነገ፣ (ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተር ፕራይዝ፣ 1994 ዓ.ም)፣ ገጽ፣ 27፡28።
59 ያሬድ ገ/መድህን፣ ኖኅተ ሰማይ፣ (ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ 1996ዓ.ም)፣ ገጽ 47።

ክርስቲያን አሠራር ቅርጽ ይኸ ስለኾነ መርጠነዋል፤[60]" በማለት መልሰዋል። የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በተለይም ክብ የኾነውን የቅርጽ ለውጥ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሲገልጹ "ቤተ-ክርስቲያን ምኩራብ እንጂ ቤተ-ክርስቲያን አይመስልም፤ ስሙን ግን ካቴድራል ይሉታል።[61]" በማለት ይመልሳሉ።

**ጉልላት፤** በቤተ-ክርስቲያን አናት ላይ የሚቀመጥ ክብ ኾኖ በንጉሥ ዘውድ ወይም በቁም መሶብ ቅርጽ የሚሠራ፤ በአናቱ ላይ መስቀል ያለው፤ በመስቀሉ ዙሪያ የእንቁላል ቅርጽ ያላቸው ብረት ነክ ማዕድናት በዚያም ላይ የሰጐን እንቁላል የተሰካበት ነው፡፡ በመስቀሉ ላይ መሰካት ያለበት የሰጐን እንቁላል እንደኾነና ቁጥሩም ሦስት አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት ወይም ዐሥራ ኹለት መኾን አለበት፡፡[62] እንጦጦ ማርያም የሰጎን እንቁላል ለምን በጉልላቱ ላይ አልኖረውም ለሚለው ምላሽ ሲሰጡ፡_"አኹን የሰጐን እንቁላል ከየት ይገኛል? የሰጐን እንቁላል መኾኑ ግን ብዙ ሐተታ ነበረው።[63]" በማለት የሰጎን እንቁላል አለመገኘቱን በምክንያትነት ጠቅሰዋል።

**ሻኩራ(መርገፍ)፤** ከብረት ነክ ማዕድናት ይሠራል። በክብ ቅርጽ በሚሠራ ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ጣሪያ ላይ ክፈፉን ይዞ ዙሪያውን የሚንጠለጠሉ ናቸው። ሻኩራ ነፋስ ሲነፍስ በመንቀሳቀስ እርስ በእርስ ሲነካኩ ድምጽ ይሰጣሉ፡፡ ድምጹ እና እንቅስቃሴያቸው ሃይማኖታዊ ተምሳሌትነቱ፡-"ቅዱሳን መላእክት ሌሊትና ቀን በቤተ-ክርስቲያን አጸድ ያሸበሽባሉ ይዘምራሉም።[64]" የሚለውን ማሳያ ነው። በእንጦጦ ማርያም እና ሌሙ ማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሻኩራ ያላቸው ሲኾን ኹለቱ ግን የላቸውም።

በአጠቃላይ የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ ሲለወጥ ሙሉ በሙሉ ከቀሩ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ጉልላት እና በጉልላቱ ላይ ያለው የሰጎን እንቁላል (የሰጎን እንቁላል ቅርጽ) እንዲኹም ሻኩራ ናቸው። ክብ የኾነው እና ጉልላት የነበረው የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ቅርጽ ሲቀር ቀድሞ የነበረው የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር ቀኖና ተምሳሌታዊ ፍቺ አዲስ በተተኩት የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ አልተሻሻሉም።

## 3.2 ልብሰ ተክህኖ

ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ከሚያሳዩ ንዋየ ቅድሳት ልብሰ ተክህኖ ይገኝበታል። ልብሰ ተክህኖ በቅዳሴ ጊዜ ቀዳስያን የሚለብሱት ልብስ ነው፡፡ የቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች

60 መረጃ ሰጭ፡- በኩረ ትጉሀን ቀሲስ በለጠ ኃይለማርያም፣ እድሜ 32፣ (ቃለ-መጠይቅ መጋቢት 17 2000)፡፡

61 መረጃ ሰጭ፡- ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ እድሜ 62፣ (ቃለ-መጠይቅ ግንቦት 15 2000)፡፡

62 ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ሥርዓተ ቤተክርስቲያን፣ (ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992ዓ.ም)፣ ገጽ 12።

63 መረጃ ሰጭ፡- መምህር ቃለ ጽድቅ፣ እድሜ 71፣ (ቃለ-መጠይቅ ሚያዝያ 6 2000)፡፡

64 ያሬድ ገ/መድህን፣ ኖኅተ ሰማይ፣ (ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ 1996ዓ.ም)፣ ገጽ 60።

በአገልግሎት ወቅት የሚለብሷቸው ልብሰ ተክህኖ የመልበሻ ጊዜ፣ የልብሱ ዓይነት፣ አዘገጃጀቱ (አሰፋፉ)፣ መጠኑ፣ ቀለማቸውና ሌሎችም የየራሳቸው ደንብ እና ሃይማኖታዊ ተምሳሌት ያላቸው ናቸው።

ካህናት መሥዋዕት ለማቅረብ ሲዘጋጁ፣ ልብሰ ተክህኖውን በኤጲስ ቆጶስ አስባርከው ኤጲስ ቆጶስ ከሌለ ራሳቸው ባርከው ይለብሳሉ፡፡ ካህናት የሚለብሱት የስረኛው ቀሚስ፣ የላይኛው ካባ ላንቃ ነው፡፡ ካባ አምስት መንዲል ያለው ሲኾን ኹለቱ በፊት ለፊት ሦስቱ ከጀርባ ይወርዳል፡፡ አምስት መሆኑ የካህኑ እምነት በአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ላይ የተመሠረተ መኾኑን ያመለክታል፡፡ ከአናታቸው ላይ የሚደፉት አክሊል ይባላል፡፡ ጌጥ ያለው ክብ ሆኖ አናቱ ላይ መስቀል፣ ከውስጥ ከቀላልና ጠንካራ ቁስ ይሠራል[65]፡፡ ምሳሌነቱ 'የክርስቲያን ፍጻሜው የድል አክሊል ነው' የሚል ነው።

የዲያቆናት ልብስና አክሊል ከካህኑ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ካህኑም ኾነ ዲያቆኑ ልብሰ ተክህኖ ሳይለብሱ መቀደስ አይችሉም፡፡ ጳጳሳት ግን በልብሳቸው መቀደስ ይችላሉ፡፡ ክህነት ያላቸው መነኮሳት ሞጣህት ብቻ ደርበው በራሳቸው ቀሚስ መቀደስ ይችላሉ፡፡ የጳጳሳትና የመነኮሳት አክሊል ሳይኾን አስኬማ ይበላል፡፡ አስኬማ ጌታ ሲሰቀል አይሁድ በስቅለቱ ጊዜ እሾህ ጉንጉነው በራሱ ላይ የመድፋታቸው ምሳሌ ነው። የጳጳሳትም ልብስ እጁ ሠፊ ሲኾን ስፋቱ ብዙ መክሊት እንደተሰጣቸው ለማመላከት ነው፡፡

ተክህኖ ልብስን በተመለከተ ከቀኖናው የወጣ ስለመኾኑ ለዚኽ ጥናት ምልከታ ሲደረግ በተደጋጋሚ የታየው ቀለማቸው ከተጻፈው ደንብ ጋር አለመመሳሰል ዋነኛው ነው። የካህናት አለባበስን በተመለከተ ሃይማኖታዊ ደንቡ "ካህናት የሚቀድሱባቸው አልባሳት ቀይ ቀለም የገባባቸው ያይደለ፣ ነጫጭ ይኹኑ። ነጭ ልብስ ደስ እንዲያሰኝ በሥጋ ወደሙ የተገኘ ክብርም ደስ ያሰኛልና።[66]" በማለት ይገልጻል።

በአራቱም አብያተ ክርስቲያናት ያሉ የመቀደሻ ልብሶች ለምልከታ ከተሔደባቸው አራት አራት ቀናት ሌሙ ማርያም ከአራቱ ቀን በአንዱ ነጭ ለብሰው ቀድሰዋል፡፡ በቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ አንድ ቀን በጥቁር (የጸሎተ ሐሙስ ዕለት)፣ አንድ ቀን ነጭ (የትንሣኤ ዕለት) እንጦጦ ማርያም አንድ ቀን (የሆሣዕና ዕለት) ነጭ ሲለብሱ፣ በሌላው ቀን ግን የተለያየ ቀለም ያላቸው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ሲቀድሱ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የካህናት ልብሰ ተክህኖ ቀለም ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ነጭ አለ። ከላይ በፍትሐ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ እንደተገለጠው ሕጉ እና ትውፊት ነጭ እንዲለብስ ቢያዝም በተግባር ግን ተዘውትሮ ሲከወን እንመለከታለን።

[65] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘሌ.8፣9፣ ማር.15፣1።

[66] ፍትሐ ነገሥት ሥጋዊ ወመንፈሳዊ፣ አሥመራ፣ (ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት፣ 1956፣)፣ አን.12፣196

ነጭ ቀለም ያለው ልብሰ ተክህኖ ለምን እንደማይለብሱ አገልጋዮች እንደ ምክንያት የሚያነሡት ልብሱን የሚሸጡ ነጋዴዎች ነጭ በብዛት አለማቅረባቸውን ነው። በገበያ ላይ እንደልብ ላለመገኘቱ ምክንያቱ ሲጠቁሙ በካህናቱ ልብስ ላይ የተለያዩ ጌጣ ጌጦች ይሰራሉ። ነጭ ላይ ደግሞ ጌጣጌጡ አያምርም ወይም ለገዢው ሰው አይን(ቀልብ) አይስብም፡፡ በልብሰ ተክህኖ ላይ የሚደረገው ጌጥ ከቀኖናው ውጭ ነው፡፡ ሌላው ሊቃውንቱ የተክህኖ ልብሶች ቀለም በቀኖናው መሠረት ነጭ ላለመኾኑ ከሚያነሧቸው ምክንያቶች "ከእኅት አብያተ-ክርስቲያን የተወረሰ ልምድ ሊኾን ይችላል[67]" የሚል ግምት ነው፡፡

የተክህኖ ልብስ ኹለተኛው ሃይማኖታዊ ፎክሎር ማሳያ ቀሚሱ እስከ ተረከዝ የረዘመ መኾን እንጂ አጭርም ከመጠን ያለፈ ረዥምም መኾን እንደሌለበት ሲገልጽ፣ "ካህናት በቅዳሴ ጊዜ የሚለብሱት ልብስ እስከ ተረከዛቸው የሚደርስ ይኹን … ልብሱ ተርፎ አካሉ ቢያጥር በመለኮት ሕፀፅ አለበት፤ ሥጋ ምልዓት ኾኖታል ያሰኛል፡፡[68]" በማለት ሃይማኖታዊ ደንቡ ተጽፎ ይገኛል። ስለዚኽ ቀዳስያን የሚኾናቸውን ልብሰ ተክህኖ አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት መርጠው መልበስ አለባቸው፡፡ ለረዘመ ቀሚስ መታጠቂያ (ዝናር) እንዲታጠቁ ምሳሌው ጭምር አለ፡፡ ቀሚስ የመለኮት ምሳሌ ነው፡፡ ቀሚሱን የሚለብሰው ካህኑ የሥጋ ምሳሌ ነው፡፡ መታጠቂያው ጌታ መስቀሉን ተሸክሞ ሲኼድ አይሁድ ወገቡን በገመድ አስረው የማንገላታታቸው ምሳሌ ነው፡፡

በምልከታ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በበቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስና በእንጦጦ ማርያም የለበሷቸው ልብሰ ተክህኖ አጫጭር ነበሩ፡፡ በአጠቃላይ የልዑካን ልብስ ቀለሙ፣ አሰፋፉ፣ እንዲኹም መጠኑ ከቀኖና ውጭ እንዳይኾን አገልጋዮች በየ ጊዜው ስለ አልባሳት ቀለም ትርጉምና ትውፊቱን መጠበቁ ስለሚያስገኘው ጠቀሜታ ትኩረት የሚያሻው መኾኑን አጥኚዋ በምልከታው ተገንዝባለች፡፡

---

[67]ለምሳሌ የግሪክን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን የቅዳሴ ልብሶች ቀለም፤ በነቢያት በዓል የሚቀድሱት አረንጓዴ ለብሰው ሲሆን ምሳሌነቱ የነቢያት ስብከት "ጌታ ይወለዳል፣ ዓለምን ያድናል" የሚል ተስፋ የነበረው ነው፡፡ አረንጓዴ የቅጠሎች ቀለም በመሆኑ ፍሬ የማፍራትን ተስፋ የሚያሳይ ቀለም ያለው ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ በሐዋርያትና በሰማዕታት በዓል ቀይ ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ ቀይ ሰማዕታትና ሐዋርያት በዚህች ምድር ሲኖሩ ስለ ክርስቶስ የሰበኩት በቃል ብቻ ሳይሆን መከራዎችን እየተቀበሉ፣ ደማቸውን እያፈሰሱ ስለነበረ ቀይ ቀለም የደማቸው ምሳሌ ሆኖ ተመርጧል፡፡ የጻድቃንና የጌታ በዓል ከሆነ ደግሞ ነጭ ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ የነጭ ምሳሌ ጌታ ከሙታን ተለይቶ በተነሳ እለት መቃብሩ አጠገብ ነጫጫ የለበሱ መላእክት ታይተዋል። እንዲሁም ጌታ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ገልጿል። ብርሃን ደግሞ እንደ ነጭ ቀለም የሚታይ ስለሆነ በጌታና በጻድቃን በዓላት ነጭ ለብሰው ይቀድሳሉ፡፡ በአጠቃላይ ቀዳስያን በኢ.ኦ.ተ.ቤ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ልብሶች ለብሰው የሚቀድሱበት ምክንያት ከእህት አብያተ ክርስቲያናት በመጣ ልማድ ሊሆን ይችላል( ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ ቃለመጠይቅ)፡፡

[68] ፍትሐ ነገሥት ሥጋዊ ወመንፈሳዊ፣ አሥመራ፣ (ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት፣ 1956፣)፣ አን.12፣196።

# 3.3. ድባብ/ጥላ

ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ከሚያሳዩ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ጥላ ይገኝበታል። ድባብ(ጥላ)፤ ድባብ የሚባለው ትልቅ ጥላ ነው። ድባብ ለክብረ በዓል ታቦት ሲወጣ (ሲነግሥ) አገልግሎት ላይ የሚውል ነው፡፡ ድባብም ኾነ ጥላ ዘንጉ፣ ከብረት ነክ ማዕድናት እንዲኹም ከእንጨት ይሠራል። ከላይ ያለው ጨርቅ ሲኾን ጨርቅነቱ የተለያየ ሊኾን ይችላል፡፡ ጥላ አገልግሎቱ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ ኅብስቱን ከቤተ-ልሔም ወደ ቤተ-መቅደስ ይዞ ሲኼድ፣ ካህኑ ማዕጠንት ይዞ ከመቅደስ ወደ ቅድስት ለማጠን ሲወጣ በዲያቆኑ የሚያዝ ነው፡፡ ወንጌል ሲነበብ ሥጋ ወደሙ ለምእመናን ሲሰጥ (በዕርገት ጊዜ) ከቅዳሴም ውጭ አስከሬን ወደ መቃብር ሲወርድ ይዘረጋል፡፡ ምሳሌነቱ ሕዝበ እስራኤል አርባ ዓመት ሙሉ ሲጓዙ የፀሐዩ ግለት እንዳያቃጥላቸው የእግዚአብሔር መልአክ በደመና ይጋርዳቸው ነበር፡፡ ዛሬም ክርስቲያኖች ወደ መንግሥተ ሰማያት በሚያደርጉት ጉዞ የእግዚአብሔር ጥበቃ (ከለላ) እንደማይለያቸው ማሳያ፤ እንዲኹም ሙሴ ጽላቱን ሲቀበል በደብረ ሲና ተራራ የጋረደው ደመና ምሳሌ ነው፡፡ በደብተራ ኦሪት ታቦት ሲወጣ እግዚአብሔር ለነሙሴ ሲገለጥላቸው ድንኳኗ በደመና ተሞልታ በደመናው መካከል ክብና ልዩ ብርሃን መጥታ በታቦቱ ላይ ትረብ ነበር፡፡ ድባቡም የዚኽ ብርሃን ምሳሌ ነው፡፡ ያኔ በደብተራ ኦሪት በታቦቱ ላይ ይገለጥ የነበረው ብርሃን ዛሬም እንዳልተለየ ለማጠየቅ ነው[69]፡፡

በአራቱም አብያተ ክርስቲያናት በተለያየ ቀን በተደረገ ምልከታ በድባብና በተለያዩ ጥላዎች ላይ ሥዕለ ቅዱሳን ተሥሎባቸው ይታያል። በጥላ ወይም በድባብ ላይ ሥዕል እንዲሳልበት አልተፈቀደም። አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ጥላዎች ላይ ግን በብዛት ቅዱሳት ሥዕላት ተለጥፎባቸዋል። ኾኖም በቀኖናው ሥዕለ ቅዱሳን በጥላ ላይ እንዲሳሉ አልታዘዘም፡፡ ምክንያቱም ሥዕለ ቅዱሳን በራሳቸው ንዋየ ቅድሳት ሲኾኑ ሊሰጣቸው የሚገባ አክብሮት በጥላው የላይኛው ክፍል ላይ እንዳይኾኑ ምክንያት ይኾናል።

# 3.4 ተቋመ ማኅቶት (መቅረዝ)

የተቋመ ማኅቶት አሠራር ቅርጽ የሃይማኖታዊ ፎክሎር ማሳያ ነው። ተቋመ ማኅቶት፣ ተቋመ ወርቅም ይባላል፡፡ ተቋም፣ መቅረዙን መሸከሚያ ማለት ሲኾን፣ ማኅቶት መብራት ነው፡፡

[69]የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሀፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ 1ኛ ነገ. 6፡2 ፤ ዘጸ.19፡9፤ 9፡3።



ስእል 1 ማኀቶት

የሚበራው ቀንዲል ወይም ሻማ ሊኾን ይችላል፡፡ በብሉይ ኪዳን ሙሴ እንዲሠራቸው ከታዘዛቸው ሦስት ንዋያተ ቅድሳት አንዱ ነው[70]። ተቋመ ወርቅ የተባለው የሚበራው በዘይት ስለነበረ አሠራሩም ከወደታች ቀጥ ብሎ እንዲቆም እንደ ጽዋዕ ያለ እግር ይሠራለታል፡፡ መካከለኛውን አንድ ወጥ አድርጐ እንዲያበጅና ሦስቱን የመቅረዙን ቅርንጫፎች ከግራና ከቀኝ በማድረግ በመካከለኛው ላይ የተሞላውን ዘይት በስድስቱም እንዲሞላ መኮስተሪያ እንዲያበጅለት አዟል፡፡ ምሳሌነቱ ተቋሙ የድንግል ማርያም፣ ፈትሉ አምላክ የነሣው ሥጋ፣ ዘይቱ የመንፈስ ቅዱስ እሳቱ የመለኮት ቅርንጫፎቹ ሰባት መኾናቸው የፍጹምነት ምሳሌ ነው፡፡ ሰባት በዕብራውያን ፍጹም ነው[71]፡፡ በቀኝና በግራ ሦስት ሦስት መኾናቸው በዘመነ መሳፍንት፣ በዘመነ ነገሥት፣ በዘመነ ካህናት የተጻፉ መጻሕፍት ምሳሌ ነው፡፡ የተቋመ ማኀቶት ቅርጽ ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት የሚከተለውን ይመስላል።

ከላይ ፎቶ ላይ የምንመለከተው በቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የተነሣ ፎቶ ሲኾን ቀኖናውን ተከትሎ የተሠራ ነው። ቀኖናውን ካልጠበቁ ንዋያተ ቅድሳት አንዱ ተቋመ ማኀቶት ነው፡፡ ቀኖናውን ያላሟሉ ሌሎች ተቋመ ማኀቶት በዚኹ ቤተ ክርቲያን የሚገኙ ሲኾን ማብሪያቸው ባለ አምስት፣ ባለሦስት እና ባለኹለት ናቸው። እንዲኹም ሌሙ ማርያም ባለ ሦስት እንጦጦ ማርያም ባለ አንድ ማብሪያ ተቋመ ማኀቶት ይገኛሉ፡፡

70 የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር፥ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘፀ.25፥31-40፤ 37፥24፤ ዘዳ. 9፥4።

71 የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር፣ መጽሀፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ምሳ. 24፣ 16 ።

# 3.5 ከበሮ

በሚሰጡት አገልግሎት ሃይማኖታዊ ፎክሎር ከሚታይባቸው ንዋያተ ቅድሳት ከበሮ ይገኝበታል። ከበሮ ለማሕሌት አገልግሎት ከሚውሉ ንዋያተ ቅድሳት አንዱ ነው። ከበሮ ቋሚው አካል ከዕንጨት ወይም ከከበሩ ብረት ነክ ማዕድናት ለምሳሌ ከብር ወይም ከወርቅ ተሠርቶ ከላይና ከታች እንዲኹም የሚጠላለፈው መወጠሪያና ማንገቻው በከብት ቆዳ የሚሠራ የዜማ መሣሪያ ነው፡፡ ቅርጹ ከአንድ ወገን ሰፊ፣ ከአንድ ወገን ጠባብ ሲኾን ሲመታ በመቺው አንገት ላይ በማንጠልጠል ሰፊው እና ከፍ ያለ ድምጽ የሚያሰማው ክፍል በቀኝ እጅ ጠባቡ በግራ እጅ ይመታል፡፡ የመዝሙር መሣሪያ ስለመኾኑም "ስሙን በማሕሌት ያመስግኑ፣ በከበሮና በመስንቆም ይዘምሩለት[72]" በማለት ስለአገልግሎቱ ተገልጿል፡፡ ታቦተ ጽዮንን ከአሚናዳብ ቤት ባወጡ ጊዜ ዳዊትና የእስራኤል ቤት ኹሉ በቅኔና በበገና በመስንቆና በከበሮ በነጋሪትና በጸናጽል በእግዚአብሔር ፊት…ይዘምሩ ነበር፡፡[73] በተጨማሪም ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን ከበሮ እየመታችሁ አመስግኑ፡፡[74]

የከበሮ ምሳሌነቱ፤ ከላይና ከታች ተጠላልፎ እንደመወጠሪያ የሚያገለግለው ጠፈር(ቆዳ) አይሁድ ጌታን በገረፉት ወቅት ሰውነቱ ላይ የወጣዉን ሰንበር ያስታውሳል። በአንገት መነገቱ በአንገቱ ገመድ አስገብተው ያንገላቱት፣ ከላይ ሰፊ መኾኑ ኹሉ ነገር ያለውን እግዚአብሔርን ሲያመለክት ከታች መጥበቡ ወልድ በጠባብ ደረት የመወሰኑ ምሳሌ ነው፡፡ በዚኹ መሠረት በአራቱም አብያተ ክርስቲያን በእያንዳንዱ ከኹለት በላይ ከበሮ ይገኛል።

በምልከታ በተገኘው መረጃ በንግሥ በዓል(በዓመታዊ ክብረ-በዓል) በተለይ በሌሙ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ካሉት ከበሮዎች አንዱ ለዘፈን ሲገለገሉበት ነበር። በተጨማሪም ከቤተ-ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ ጋብቻ ለሚፈጽሙ ምእመናን ለሰርግ ዘፈን ማጀቢያ ከበሮ በውሰት ከቤተ-ክርስተያን ለምእመናን ይሰጣል። በከበሮ ላይ የሚታየው ሃይማኖታዊ ፎክሎር አጠቃቀም ላይ ነው። ይኸውም ለአምልኮ ተግባር ለምስጋና የሚያገለግልን ንዋየ ቅድሳት ለዓለማዊ ተግባር ወይም ለዘፈን መዋሉ ነው።

72. የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ መዝ.148፥3።

73 የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ 2ኛ ሳሙ.6፥5።

74 የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስአበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዮዲት፣ 16፣ 2።

## 3.6 ሥዕል

*ሥዕል፤* "በቁም መልክ፣ የመልክ ጥላ፣ ንድፍ፣ አምሳል፣ ንድፍ በውኃ፣ በመጽሔት፣ በጥልፍ፣ በስፌት ወይም በቀለም በወረቀት ገዝፎ ተጽፎ ከደብር፣ ከዕብን፣ ከዕፅ፣ ከማዕድን ታንጦ፣ ተቀርጦ፣ ተሸልሞ፣ አጊጦ የሚታይ የሚዳሰስ ነገር ነው፡፡[75]››

ሥዕለ ቅዱሳን በሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን የሚሳሉበት ደንብ አላቸው። በብሉይ ኪዳንም በታቦተ ሕጉ ላይ ሥዕለ ኪሩብን እንዲሥል ሙሴ ታዞ ነበር፡፡[76] እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ቅዱሳት ሥዕላት ለሥርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ ይውላሉ፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ትእዛዝ አብነት አድርጐ ጠቢቡ ሰሎሞን ታላቁን ቤተ መቅደስ ካሠራ በኋላ ሥዕለ ኪሩቤልን በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አስቀምጧል፡፡ በቤተ መቅደስ ግንብ ዙሪያ በበሮች ላይ የኪሩቤልንና የዘንባባ ዛፍ የፈነዳ አበባ ሥዕሎችን ሠርቷል።[77] ሥዕለ ቅዱሳንን ከክርስትና ሃይማኖት በፊት አይሁዶች ለአምልኮ ሥርዓት ይገለገሉባቸው ነበር፡፡

በቤተ-ክርስቲያን ሥዕል ለመሣል ምክንያት የነበረው የክርስትናን ሃይማኖት ለማስተማር በቂ መጻሕፍት ስላልነበሩ እና እንደልብ ለማስተማር ስለማይፈቀድ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በሥዕል እያቀረቡ በቀላሉ ለማስተማር ይገለገሉበት ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ይሣሉ የነበሩ ታሪኮች ክርስቶስ በእርሱ ያመኑትን በእርሱ አምነው የሞቱትን ኹሉ የሚያድናቸው ቸር እረኛ ስለመኾኑ እረኛው በጎቹን እንደተሸከመ አድርገው ይሥሉት ነበር፡፡ ሌላው የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን እንዴት እንደተሳሳቱ ያሳሳታቸውን[78] ታሪክ የሚያሳይ እንዲኹም[79] በምሕላና በጸሎት ያለችን ነፍስ በኖኅ መርከብ አስመስለው ይሥሉ ነበር፡፡ የሐዲስ ኪዳን ታሪክም በተመሳሳይ መልኩ ይሣል ነበር፡፡ እንዲኹም ስንክሳር የድንግል ማርያምን ሥዕል በመጀመሪያ የሣለ ወንጌላዊው ሉቃስ እንደኾነ ይገልጻል[80]። የሥዕሎቹ አገልግሎት ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ለማስረዳት እንዲኹም ስለ ሃይማኖቱ በሰማዕትነት የሞቱትን ወይም በሕይወት

---

[75] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ (ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948ዓ.ም)፣ ገጽ 673።

[76] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘፀ. 25፥19፤ 37፥7፤ 1ኛ ነገ.6፣ 23፤ 2ኛ ነገ. 6፥2-7፣ ሕዝ. 9፥3፤ 10፥3፤ ሄኖክ 14፥11።

[77] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ 1ኛ ነገ. 7፥23-36።

[78] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘፍ. 3፥1-7።

[79] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት)፣ (ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980)፣ ዘፍ. 7፥1-24።

[80] ስንክሳር ጥቅምት 22 የሚነበብ፡፡

ዘመናቸው በጸሎትና በመንፈሳዊ ትጋት ያሳለፉትን ጻድቃን ለማሰብ ነው፡፡ የሥዕሎቹ አሳሣል የሚሣሉበት ቦታ እና ቅርጽ የጌታ ስቅለት፣ የቅዱሳን፣ የመላእክት እየተባለ አቅጣጫቸው የቀለሙ አመራረጥና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ትኩረትና ጥንቃቄ ይደረግባቸዋል፡፡

ሥዕል እንዴት መሣል እንዳለበት የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ቀኖና ቢኖራትም፣ ያሉት ሥዕሎች ግን በአብዛኛው ሥርዓቱን የተከተሉ አይደሉም፡፡ እንዲያውም በቤተ-ክርስቲያኗ ቀኖና መሠረት የተሣለ ሥዕል የለም ለማለት ያስደፍራል፡፡ "…ሥዕሎቹ በፈረንጅ ፎቶግራፍ ተተክተው ይታያሉ፡፡ በቤተ-ክርስቲያናችን ሥርዓትም ይኼን ታሪክ የማይታወቀው የቅርፅ ምስል የቀለሙን ሥዕል ቦታ እያስለቀቀው ነው[81]።" በእንጦጦ ማርያም በቅርፅ የተቀረፀ ሥዕል ይገኛል፡፡ መረጃ ሰጪዎች የነበሩት ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን "ቅርፅ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክልክል ነው። ቅርፅ ራሱ ጣዖት ነው፡፡ ነገር ግን በትልልቅ አድባራት ጭምር ቅርፅ እናያለን።[82]

ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ የምንመለከታቸው ሥዕሎች የጥንቱን የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የአሳሣል ስልት የተከተሉ እንዳልኾኑና "በከተማው ሕዝብ እየተገዛ ለቤተ-ክርስቲያን የሚሰጠውና ከቤቱ የሚይዘው የላቲንን የግሪክን ኪነጥበብ የሚያሳዩና የሚመሰክሩ ሥዕሎችን ነው፡፡[83]

በመስቀል ላይ ሥዕል ሊሣል ይችላል፤ ነገር ግን ቅርፅ መቅረፅ አይቻልም፡፡ ኾኖም ከእነዚኽ ንዋያተ ቅድሳት ውጭ ለምሳሌ በመጐናፀፊያ፣ በጥላ የላይኛው ገጽ ላይ ተለጥፈው አንዳንዴ ሥዕለ ቅዱሳን ተሥለው ይታያሉ። በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በቀኖና መሠረት ሥዕለ ቅዱሳን በእነዚኽ ንዋያተ ቅድሳት ላይ እንዲሣሉ አልታዘዘም፡፡ ባልተለመደ ኹኔታ ሥዕለ ቅዱሳን የሚታዩባቸው ንዋያተ ቅድሳት መካከል በተለይ ጥላ(ድባብ) በአራቱም አብያተ ክርስቲያን ይገኛል።

## 3.7 የንዋያተ ቅድሳት ስያሜ፣ ምርትና ሥርጭት

በእያንዳንዱ ንዋያተ ቅድሳት ላይ ከምናየው ሃይማኖታዊ ፎክሎር በተጨማሪ የንዋየ ቅድሳትን ብያኔ፣ የማምረቻ ቦታና ከባለቤትነት መብት ጋር በተያያዘ የሚታየው ሃይማኖታዊ ፎክሎር እንደሚከተለው ቀርቧል።

---

[81] ሐመር መጽሄት (አስኳል አማረ)፣ "ንዋየ ቅድሳትን ለአገልግሎት ሊያውሏቸው ይገባልን?"፣ (ዐዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት1994)፣ ሐምሌ እና ነሐሴ ገጽ፡13።
[82] ለምሳሌ በአዲስ አበባ አራት ኪሎ ቅድስት ሥላሴ፣ ስድስት ኪሎ መንበረ ማርቆስ በአፀድ ውስጥ ቅርጾች አሉ። በተለይም ካቴድራል ሥላሴ ቤተ-ክርስቲያን የሕንጻው የውጭ ግድግዳ ላይ እንዲሁም በአጸድ ውስጥ በብዛት ይታያሉ፡፡
[83] መረጃ ሰጭ:- ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ እድሜ 62፣ (ቃለ-መጠይቅ ግንቦት 13 2000)፡፡

ንዋያተ ቅድሳት በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ቀኖና መሠረት፣ ኦርቶዶክሳዊ የአሳሣል ትውፊቱን ጠብቆ መሠራት ያለባቸው በቤተ-ክርስቲያኗ ባለሙያዎች መኾን መቻል ይኖርበታል፡፡ ማንኛውም ሰው መሥራት ስለሚችል ብቻ አይሠራቸውም፡፡ ኾኖም በተግባር በማን ይሠራሉ? ሲባል በአብዛኛው የሚሠሩት ሥራውን መሥራት በፈለገ እና መሥራት በቻለ ግለሰብ ወይም ተቋም ነው። ባለሙያው ቁሶቹን የሚሠራበት፣ ነጋዴው ለገበያ የሚያቀርብበት ዋናው ምክንያት ገንዘብ ለማግኘት ነው። ስለዚኽ ሠሪውም ኾነ ሻጩ ዋና ጉዳዩ ገንዘብ ከኾነ ሃይማኖታዊ ይዘታቸውን መጠበቅ አለመጠበቃቸው ገገር እስካገኘ ድረስ ጉዳዩ ላይኾን ይችላል። ስለዚኽ ሠሪውም ኾነ ለገበያ አቅራቢው ገቢ እስካስገኘለት ድረስ ያመርታል። ይሸጣል። ማንም ያምርተው ወይም ይግዛው አገልግሎት የሚሰጡት ግን በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ነው። የንዋያተ ቅድሳት ገበያ ደግሞ ቤተ-ክርስቲያን እስካለች አለ። ምክንያቱም ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ያለ ንዋያተ ቅድሳት ቤተ-ክርስቲያን አይኾንም።

በየቤተ-ክርስቲያኑ "የንዋያተ ቅድሳት መሸጫ ሱቅ" ቢኖርም ኹሉንም ንዋያተ ቅድሳት የያዙ አይደሉም። ያሉትም ሱቆቹ ባሉበት ቤተ-ክርስቲያን ተመርተው ለሽያጭ የሚቀርቡ ሳይኾን ከነጋዴ ላይ የተገዙና ለትርፍ ተብለው የሚቀርቡ ናቸው፡፡

"የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻ እና መሸጫ ሱቅ" የሚለው ስያሜ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ ንዋያተ ቅድሳት ለማለት ሙሴ በታዘዘው መሠረት "የቅብዐቱንም ዘይት ወስደኽ ማደሪያውን በእርሱም ያለውን ኹሉ ትቀባለህ እርሱንም ዕቃውንም ኹሉ ትቀድሳለህ ቅዱስ ይኾናል[84]፡፡" በተባለው መሠረት ከመቀደሳቸው በፊት ንዋየ ቅድሳት አይባሉም፡፡ ሱቅ ውስጥ የሚሸጡ ቅብዐ ቅዱስ ተቀብተው የከበሩና ተገቢው ጸሎት የተደረገላቸው ሳይኾኑ ገና ወደ ቤተ-ክርስቲያን ያልገቡ በመኾናቸው "ንዋያተ ቅድሳት" የሚለው ስያሜ ተገቢ አይደለም፡፡ "ንዋያተ ቅድሳት ናቸው" ከተባለ ደግሞ ንዋያተ ቅድሳት አይሸጡም፣ አይለወጡም፡፡ ስለዚኽ እንዴት ንዋያተ ቅድሳት ሊባሉ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ ያስነሣል። "ቤተ-ክርስቲያኗ የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ አላት፤ ነገር ግን በቂ አይደሉም[85]፡፡"

ንዋያተ ቅድሳት የትኞቹን ያካትታሉ? የትኞቹንስ አያካትቱም? ለሚለው በተለይ የነገሥታት መገልገያ የነበሩና ለቤተ-ክርስቲያን የተሰጡ እንዲኹም በቤተ-ክርስቲያን ሙዝየም ውስጥ የሚገኙትን አንዳንዶቹ "ንዋያተ ቅድሳት ናቸው" ሲሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ "ንዋያተ ቅድሳት ሳይኾኑ ቅርስ ናቸው" በማለት በቅርስነት ብቻ ይፈርጁዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ እንጦጦ ማርያም ሙዝየም ውስጥ ያሉ የነገሥታት መገልገያ የነበሩና ለነገሥታቱ የተለያዩ ሰዎች የተበረከቱ ዕቃዎች "ቅዱስ የሚያሰኛቸው ቅዱስ ቦታ

[84] ዘጸ. 40፥8።)

መገኘታቸው ካልኾነ ንዋያተ ቅድሳት ሊባሉ አይገባም።[86]" በሙዝየሙ ውስጥ ያሉ የነገሥታት ልብስ፣ የጦር መሣሪያ እንዲኹም የተለያዩ መገልገያዎችን በአስጎብኝዎች በሚደረግ ገለጻ "ንዋያተ ቅድሳት ናቸው" በማለት ለጎብኚዎች ይተዋወቃሉ፡፡ ከነገሥታት መገልገያ ለምሳሌ የንግሥና ልብስ፣ ዘውዶች እና መሰል መገልገያዎች ቅርስ እንጂ ንዋያተ ቅድሳት ሊባሉ እንደማይገባ መረጃ ሰጪ ሊቃውንት ይናገራሉ[87]፡፡ ንዋያተ ቅድሳት የሚባሉት በቡራኬና በቅብዐ ቅዱስ ከብረው ለአገልግሎት ተለይተው ያሉ የቤተ ክርስቲያን መገልገያዎችን መሆን መቻል አለበት፡፡ ከዚኽም ባሻገር በአገልግሎት የከበሩ ፓትሪያርኮች አልባሳት፣ ዘውድ፣ የጳጳሳት አስኬማ፣ የካህናቱ፣ የዲያቆናቱ…ልብሰ ተክህኖ ናቸው።

በሙዝየም ውስጥ ከሚገኙት መካከል ነገሥታቱ ለቤተ-ክርስቲያን በስጦታ የተሰጡት "ንዋያተ ቅድሳት ናቸው" በሚል ነው። ኾኖም ከእነዚኽ መካከል አንዳንዶቹ ሥርዓተ ቤተ-ክርስቲያንን ያልጠበቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በእንጦጦ ማርያም ሙዝየም ከሚገኙ ሥዕሎች መካከል ከዐድዋ ጦርነት በኋላ ለዓፄ ምኒልክ ከኢጣልያን መንግሥት የተላከ፣ በ1882 ከራሽያ ቤተ-ክርስቲያን ለአፄ ምኒልክ የተበረከተ "የድንግል ማርያም ቅርጽ" የሚል ነው፡፡ እነዚኽን ስንመለከት የቤተ-ክርስቲያኗን ቀኖና ያፋለሱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ቅርፅ እንደ ጣዖት ይቆጠራል፤ ጣዖት ደግሞ ቀኖናን ብቻ ሳይኾን ዶግማንም ያፋልሳል[88]፡፡ ቅርፅ ከመሠረቱ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊት የሚደግፈው ሃይማኖታዊ መገለጫ አይደለም፡፡

# 4. ማጠቃለያና ይኹንታ

በጥናቱ የተገኘው ውጤት በቤተ-ክርስቲያን ግቢ (አጸድ) ውስጥ ያለ ነገር ኹሉ በጥቅል ስሙ ንዋያተ ቅድሳት ይባላል፡፡ ለሃይማኖታዊ ተግባር የሚውሉ የተለያዩ "ቁሳቁሶች" በሃይማኖቱ ሥርዓት መሠረት አገልግሎት ላይ ከዋሉ በኋላ ስማቸውም ኾነ ግብራቸው ተለውጦ ንዋያተ ቅድሳት የሚለውን ስያሜ ያገኛሉ። ቤተ-ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊዉን መሠረት እና ኦርቶዶክሳዊ ትውፊቱን በመያዝ የሚሠሩትን ንዋያተ ቅድሳት በታዘዘው መሠረት እንዲሠሩና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ፤ በአገልግሎቱም ወቅት ማን መቼና እንዴት? መገልገል እንዳለበት ዝርዝር ሕግና ምሳሌያቸው ጭምር በጽሑፍ ሠፍሮ ይገኛል፡፡

[86] መረጃ ሰጭ፡- መምህር ቃለ ጽድቅ፣ እድሜ 71፣ (ቃለ-መጠይቅ ሚያዝያ 6 2000)፡፡
[87] መረጃ ሰጭ፡- ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ እድሜ 62፣ (ቃለ-መጠይቅ ግንቦት 13 2000)፡፡
[88] መረጃ ሰጭ፡- ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ እድሜ 62፣ (ቃለ-መጠይቅ ግንቦት 13 2000)፡፡

ኾኖም ኹሉም ንዋያተ ቅድሳት በተግባር በተጻፈው ሃይማኖታዊ ሕግ መሠረት የሚሠሩና አገልግሎት ላይ የሚውሉ አይደሉም። እነዚኽህ ተቃርኖዎች መታየታቸው የንዋያተ ቅድሳቱን ሃይማኖታዊ ፎክሎር ማሳያ ነው። በዝርዝር ጥናት ውስጥ እንደቀረበው ሃይማኖታዊ ፎክሎር የሚታይባቸው፤ አንደኛ "ንዋያተ ቅድሳት" የሚለው ስያሜ በተገቢው ቦታ አለመጠቀም። ለምሳሌ "የንዋያተ ቅድሳት መሸጫ ሱቅ"፣ ከዚኹ ጋር በተያያዘ ሌላው የንዋያተ ቅድሳቱ አምራች ከቤተክርስቲያን ውጭ መኾን፣ ኹለተኛ ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሠራር ቅርጽ መለወጥ፣ የቅርፅ ለውጥ ጉልላትና በጣራው ክፈፍ ዙሪያ ይደረግ የነበረ ሻኩራ እንዲኹም ጉልላት እንዲቀር ማድረጉና የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ክፍሎች ወደ ኹለት እንዲቀንሱ እና ምሳሌያቸው አብሮ እንዲቀር አድርጓቸዋል። ሦስተኛው፤ ልብሰ ተክህኖ ሲኾን ይኸም የልብሱ ቀለም መለዋወጥ እና የአሰፋፍ ቅርፅ በአግባቡ አለመኾን ታይቶባቸዋል። አራተኛው የከበሮ ለዓለማዊ ዘፈን መዋል ነው። አምስተኛው ተቋመ ማኅቶት እንዲሠራ በታዘዘበት ሕግ በተግባር ሲሠራ አለመታየቱ ነው። ስድስተኛው ሥዕለ ቅዱሳን ሲኾን ይኸም በአዋቂዎች በምን መልክ መሣል እንዳለበት የተጻፈው ሕግ እንዳለ ኾኖ በተግባር ግን መለወጡ ነው። ሰባተኛው ጥላ(ድባብ) ሲኾን በጥላው ላይ የሚለጠፉ ቅዱሳት ሥዕላት ያለተገቢ ቦታቸው መገኘታቸው የሃይማኖታዊ ፎክሎር ማሳያዎች ናቸው።

በአጠቃላይ ቤተ-ክርስቲያን የምትተዳደርበት ሕግ አንድ ኾኖ ሳለ በተለያዩ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የተጻፈውና የሚተገበረው የማይገናኝ ኾኖ በንዋየ ቅድሳቱ ላይ ይስተዋላል። ንዋያተ ቅድሳትን በተመለከተ የተደነገጉ ሃይማኖታዊ ደንቦች በተግባር ካለው ጋር እንዳይፋለሱ የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች በአጥኚዋ ተጠቁሙዋል።

- ✓ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ለሃይማኖታዊ ተግባር የምትገለገልባቸው ቁሶቹ አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት ሃይማኖታዊ እና ኦርቶዶክሳዊ ትውፊታቸውን የጠበቁ ስለመኾናቸው ማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ ቢኖር፣
- ✓ ስለ ንዋየ ቅድሳት በጽሑፍ የሰፈሩ ደንቦች በተግባር ላለመዋላቸው ምክንያቶቹ በሰፊውና በዝርዝር ተጠንቶ ቢለይና መፍትሔ ቢሰጠው፣
- ✓ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻ ተቋማትን በስፋት ማቋቋም ብትችል የሚሉ ናቸው።

# ቅኔ ዘዝክረ አድዋ ወዘመነ ፋሽስት፡ ፍቺና ሐተታ

# (Qəne - Commemorating the Victory of Adwa and the Era of Fascist: Translation and Analysis)

ኃይለ ኢየሱስ አለባቸው ሞላው[89][90]

## ABSTRACT

This article is aimed at exploring how poem (ቅኔ) Scholars of Ethiopian Orthodox Tewahedo Church recoded and narrated the Italian invasion in general and the Victory of Adwa in particular in their Qəneyat (poems). To achieve this purpose, the researcher employed qualitative methodology with secondary sources (document analysis) as instruments of data collection. Findings of the study show that the Qəneyat were composed before and after the Battle of Adwa. The pre-Adwa Qəne yat are found to be prophetic and provoking in their message. The post-Adwa Qəneyat, whereas, praise our patriots fathers, mothers, and the king. In addition, the findings attest that the message depicted in the Qəneyat is quite similar with other historical books written on the event. This also assured that besides its spiritual value, Qəne can be used as a means of channel to transfer national values and histories from generation to generation.

*Keywords: Qəne, Victoy of Adwa, Italian invasion, Battle of Adwa, patriots*

[89] የአድዋ ድል በአልን 121ኛ ዓመት ለመዘከር የተዘጋጀ ጥናት፡፡

[90] ኃይለ ኢየሱስ አለባቸው ሞላው፣ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፊሎሎጂ (በግእዝ የጥንታዊ ጽሑፎች ጥናት) 3ኛ ዲግሪ ምሩቅና በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ አስተማሪ፡፡

# መግቢያ

የመላ አፍሪካ የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ባንዴራ የኾነው የአድዋ ድል በዓል 121ኛ ዓመቱን በማስቆጠር ላይ ይገኛል፡፡ ታሪክ እንደሚዘክረው ነጮች መላ አፍሪካን ሲወሩ አፍሪካም አንገቷን ለነጮች የባርነት ቀንበር ዝቅ ስታደርግ ይኽንን ኢሰብአዊ ድርጊት በመቃወምና ለቅኝ ገዥዎች ባለመንበርከክ ሉዓላዊነቷን አስከብራ የኖረች ብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያ መኾኗ የታወቀ ነው፡፡ ምንም እንኳ ፋሽስት ኢጣልያ በዘመናዊ መሣሪያውና በሠለጠነ ወታደራዊ ኀይል በመመካት ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ ለማጥቃት ቢሞክርም አልተሳካለትም፡፡ ይኽን እንጅ የኢትዮጵያ ነጻነት በልጆቿ አጥንትና ደም ላይ የተገነባ መኾኑን ማስተዋል ያሻል፡፡

በዚኽ የነጻነት ጉዞ ኹሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግምባር ቀደም ተሰላፊ በመኾን ሀገራዊና ሃይማኖታዊ ድርሻዋን ተወጥታለች፡፡ ቀሳውስቱና ካህናቱ በጾምና በጸሎት እግዚአብሔርን በመለመን ሠራዊቱንም በማበረታታት ከጦር ሜዳ አልተለዩም፡፡ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስም መስቀላቸውን በእጃቸው ይዘው የኢትዮጵያን ወታደሮች ለትግል እያደፋፈሩ በጦርነቱ ላይ መሳተፋቸውን ታሪክ ያስረዳል[91]፡፡ ከድል በኋላም ንጉሠ ነገሥቱ ዓጼ ምኒልክና ሠራዊታቸው በአኵሱም ካቴድራል በሥርዓተ ቅዳሴና በዝማሬ ለእግዜአብሔር ምስጋና በማቅረብ ደስታቸውን ገልጸዋል፡፡[92] ይኽም ቤተ ክርስቲያኒቱ ለዚኽ ሀገራዊ ድሉ መገኘት የነበራትን አስተዋጽኦ በግልጽ ያመለክታል፡፡

ኢትዮጵያውያን በአድዋ ጦርነት በጣልያን ላይ የተቀዳጁት ድል ለመላ አፈሪካውያን ከነጭ ቅኝ ተገዥነትና ከባርነት መውጣት እንደሚችሉ በተግባር ያረጋገጠ ምሳሌ በመኾን ያገለገለ የነጻነት ደወል ነው፡፡ በአፍሪካውያን የጦርነት ታሪክ ውስጥ ከተከበሩና ከተደነቁ ጦርነቶች መካከል አንዱ ኢትዮጵያውያን አውሮፓውያንን ድል የነሡበት የአድዋ ጦርነት መኾኑ በታሪክ ይታወቃል[93]፡፡ ሃይማኖት ቋንቋ ጾታ እድሜ ሳይገድባቸው መላ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት[94] የድል አድራጊዎችና

[91] አንደርዜይ ባርትኒስኪ እና ዮዓና ማንቴል-ኒዮችኮ፣(ዓለማየሁ አበበ፣ተርጓሚ)፣የኢትዮጵያ ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ አሁኑ ዘመን (2005፣350)፡፡
[92] ዝኒ ከማሁ (2005፣ 352)
[93] ጳውሎስ ኞኞ፣አጤ ምኒልክ፣(ማንኩሳ አሳታሚ ድርጅት፣ 1984፣217)፡፡
[94] ዝኒ ከማሁ

የአሸናፊዎች በዓል ሊከበር የሚገባው በአባት አርበኞችና በቤተ ክርስቲያን መድረክ ብቻ ሳይኾን በወጣቱና በሁሉም ማኅበረሰብ፤ ከዚኽም አልፎ የጥቁር ሕዝብ ድል በመኾኑ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን በመላ አፍሪካ ጭምር በዓሉ ከፍ ብሎ መታሰብ እንዳለበት ማሰብ ተገቢ ነው፡፡

ለሀገራቸን ለልዕልናችን ለሰብእናችን ደማቸውን ላፈሰሱት አጥንታቸውን ለከሰከሱት አባቶቻችንና እናቶቻችን የመታሰቢያ ሻማ እያበራን ልንዘክራቸው ይጋባል፡፡ የነበራቸውን የሀገር ፍቅርና የአንድነት መንፈስ በማሰብ ማድነቅ፤ የአርበኝነት ታሪካቸውን እያነበብን የመወያያ አጀንዳዎቻችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አርበኞች አባቶቻችንና እናቶቻችን መኳንንቱ መሳፍንቱ ከጦርነቱ በፊት የነበሩትን ወራትና ቀናት በምን መልኩ እና ምን እየተወያዩ አሳለፏቸው? ወደጦር ሜዳ ሲዘምቱስ ምን እያሉ ይፎክሩና ያቅራሩ ነበር? በምን ዓይነት ሥነ-ልቦና ዘመቱ? ድል አድርገው ከተመለሱ በኋላ የነበሩትን ቀናትና ወራትስ እንዴት አሳለፏቸው? በጦር ሜዳ ለተሰዋው ምን ዓይነት መታሰቢያ አደረጉ? የአርበኞቹን ቤተሰቦች በምን መልኩ አጽናኗቸው? በጦርነቱ የቆሰለው አርበኛስ በምን መልኩ ቁስሉ ታከመ? ከአርበኞቹ በኋላ የተነሣው ትውልድስ ስለእነርሱ ምን አለ? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እያነሡ በመወያየት ይኽንን ታሪካዊና የነጻነት በዓል ማሰብና ማክበር ታሪካዊ ግዴታችን ነው፡፡ ይኽ ጥናት በዚኽ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥረቶች ምሳሌ ኾኖ ሊያገለግል ይችላል::

ለዚኽ ጽሑፍ ግባት የሚኾኑ ቅኔዎች የተሰበሰቡት ከታለያዩ የቅኔ መዛግብትና ቤተ መዘክር ነው፡፡ ይዘታቸውም በፋሽት ኢጣሊያ ተዳጋጋሚ ወረራና በኢትዮጵያውያን አርበኞች የነጻነት ትግል ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ቅኔዎቹ ከይዘታቸው አንጻር ቅድመ አድዋና ድኅረ አድዋ ተብለው ተፈርጀዋል፡፡ የመረጃ ትንተናው ሂደትም የግእዙን ቅኔ ፍቺ (ትርጉም) በአማርኛ በማስቀመጥ[95] በቅኔው ውስጥ በሰምና ወርቅ እንዲኹም በምሳሌ የተገለጠውን ሐሳብ በመዘርዘር ነው፡፡ በቅኔዎቹ ውስጥ ያሉትን ሐሳቦች በታሪክ መጻሕፍት ከተመዘገቡ እውነታዎች ጋር በማዛመድና በማነጻጸር ባለቅኔው ሊያስተላልፈው የፈለገውን መልእክት የጽሑፉ አዘጋጅ ተንትኗል፡፡

[95] በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ቅኔዎች የተተረጎሙት ጽንሰ ሀሳብን መሠረት በማድረግ ነው፤ ቀጥተኛና ቃል በቃል ትርጉምን መሠረት አያደርግም

ይኽን ጥናት በተፈለገው መጠንና ጥራት ለማጠናቀቅ እንዳይቻል የተለያዩ ችግሮች ያጋጠሙ ሲሆን ከነዚኽም ውስጥ፡-

- በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት አንዳንዶቹ ቅኔዎች ደራሲያቸው (ባለቅኔው) ባለመታወቁና ቅኔዎቹ የተደረሱበት ዘመን (ዓመት) አለማታወቁ ቅኔዎቹን በዘመን ቅደም-ተከተል ማስቀመጥ አልተቻለም፡፡
- በጊዜና በገንዘብ ውስንነት ምክንያት በርእሰ ጉዳዩ ላይ ትኩረት የሚያ ደርጉ በርካታ ቅኔዎችን መሰብሰብ ባለመቻሉ በጥናቱ ውስጥ ለናሙናነት የተካተቱት ቅኔዎች ቁጥር አናሳ ኾኗል፡፡

# ከአድዋ ጦርነት በፊት የተደረጉ ቅኔዎች

አስቀድሞ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፋሽስት ጣሊያን ጋር ባደገረችው ጦርነት ኹሉ አልተለየችም፡፡ ቀሳውስቱና ካህናቱ በጾምና በጸሎት ከማገዝ ባሻገር በእጃቸው የጦር መሣሪያ ይዘው ከጠላት ጋር ለመፋለም ቁርጥ ኀሊና እንደነበራቸው የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

ተምሮ ተምሮ ካልሰበሰቡት

እንዴት ያሳዝናል ሲባክን ዕውቀት፡፡

ሂጂ ተመለሽ ግቢ አገርሽ ቅኔ

ወንዶች ከዋሉበት መዋሌ ነው እኔ፡፡[96]

እያሉ የዘረጉትን ጉባዔ ሳይቀር አጥፈው ከጠላት ጋር ለመፋለም ወደ ሰልፉ ይወጡ ነበር፡፡ ቅድመ አድዋ ቅኔዎች ጦርነቱ በኢትዮጵያውያን ድል አድራጊነት እንደሚጠናቀቅ የሚጠቁሙ ትንቢታዊ ቅኔዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን ቀድመው አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚያነቃቁ (የሚያበረታቱ) ናቸው፡፡ ቅኔዎቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል[97]፡፡

---

[96] ይህ ግጥም አለቃ መርሻ ወልደ ማርያም የተባሉ የቅኔ ምሁር የገጠሙት ሲኾን እርሳቸውም ሽምግልና ሳይገድባቸው በ70 ዘመናቸው ከፋሺስት ጣሊያን ጋር በመዋጋት ብዙዎችን ገድለው ለጀግኖች የሚገባውን የሞት ጽዋ መቀበላቸውን ታሪክ ይዘክራል፡፡ (አስረስ የኔሰው፣ *ትቤ አኩሱም መኑ አንተ?*፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣1951፣91)፡፡

[97] በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱት አብዛኛዎቹ ቅኔዎች (አንዳንዶቹ ከነትርጉማቸው) የተወሰዱት

**ቅኔ**

ምኒልክ ግበር ላዕለ ሮምያ መጠነ እዴከ ትክል፣
አምጣነ ለአጺድ በጽሐ ማዕረራ ወመዋዕሊሃ ለንጉል፣

ዓዲ ተዘከር ውስተ ወንጌል፣
ላዕለ ሮምያ በለስ ኢሀሎ አስካል፣
ከመ ይቤ ወልደ ያሬድ ቃል።

**ትርጉም**

ምኒልክ፣ በሮምያ ላይ እጅህ እንደቻለ መጠን አድርግ
መከሯ ለመታጨድ ዘመኗም ለጥፋት

ቀርቧልና።

ዳግመኛም በወንጌል ያለውን አስብ፣ በሮምያ በለስ ላይ ፍሬ የለም፣
እንዳለ ወልደ ያሬድ /ቃል (ወልድ)።

ይኽ ቅኔ አሠረ ነጋሢ በመባል የሚታወቅ የእዝል ዕጣነ ሞገር[98] ቅኔ ነው። ቅኔው የተነገረውም ከአድዋ ጦርነት በፊት በ1883 ዓ.ም የሐምሌ ሚካኤል አዲስ አበባ አለቃ ለማ ኀይሉ በተባሉ ሊቅ[99] ነው።

ዓፄ ምኒልክ በወቅቱ የጠላታቸው ጠላት (ዓፄ ዮሐንስ) ከጣሊያን ጋር የተወዳጁና ስምም የነበሩ ቢኾንም[100] ባለቅኔው ወዳጅነታቸው እንደማይዘልቅና ሮማውያን በዓፄ ምኒልክና በሠራዊታቸው እጅ እንደ መከር አዝመራ እንደሚታጨዱ በትንቢታዊ

---

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ተዘጋጅቶ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያሳተመው የግእዝ ቅኔያት የሥነ ጥበብ ቅርስ ኹለተኛና ሦስተኛ ቅጾች ነው። በቅኔዎቹ ግርጌ ማስታወሻ የተወሰዱበት ቅጽና ገጽ ተገልጧል።

[98] ዕጣነ ሞገር ከቅኔ አርእስት (ስያሜዎች) አንዱ ነው። ከጉባዔ ቃና ጀምሮ ያሉ ቅኔዎች የሚጠሩባቸው የራሳቸው ስሞች አሏቸው። የተለያዩ ጸሐፍት በተለያየ መንገድ ስለሚቆጥሯቸው የቅኔ አርእስትን ብዛት አንዳንዶች 22 ሲያደርጉት ሌሎች ደግሞ 17 አድርግው ጽፈዋል። ለምሳሌ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ 22 ናቸው ሲሉ ይኸውም የሃያ ኹለቱ አርእስተ ድጓ፤ የ22 ሥነ-ፍጥረታት ምሳሌ እንደኾኑ አትተዋል። ማርየ ይግዛው ደግሞ በዋናነት 9 መኾናቸውን በመግለጽ በዝርዝር ሲቆጠሩ ደግሞ 17 መኾናቸውን ሀብተ ማርያም ወርቅነህን እና የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚን ዋቢ በማድረግ ጽፏል። የአርእስቱ ስያሜ አመጣጥና እንዲኹም ምሳሌያዊ ትርጉሙ የተለያየ መኾኑን ለመረዳት ከላይ የተገለጹት ጸሐፍት የዘገቡትን ይመለከቷል።

[99] ማርየ ይግዛው፣ ቅኔያዊ የእውቀት ፈጠራ፣ የጀርመን ባህል ማእከል፣ 2006።

[100] 10ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣ 1984 ገጽ 138።

ቅኔያቸው አመልክተዋል። ሊቁ ለቅኔያቸው መነሻ ያደረጉት ክርስቶስ በወንጌል ፍሬ የማትሰጥ በለስ እንደምትቆረጥ ያስተማረውን ነው (ሉቃ ፲፫፡፯)። ሮምን ፍሬ (መልካም ነገር) በማይገኝባት በለስ መስለው መቆረጫዋም (መውደቂያዋም) ተቃርቧልና ብትወጋት ድል ታደርጋለኽ በማለት ንጉሡን በቅኔያቸው መክረዋል። ቅኔው የማነቃቂያ ቅስቀሳ ነው። ይኽንን የጦርነት ቀስቃሺና ትንቢታዊ ቅኔ የሰሙ ብዙ ሰዎች በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ጦርነት መነሣቱ እንደማይቀር ገመቱ። ቅኔው በተነገረ በአምስተኛ ዓመቱ የአድዋው ጦርነት ተንሥቶ ንጉሡ የጣሊያንን ጦር እንደተመከሩት ድል አድርገዋል። ይኽም ቅኔ ከምሥጢሩ ባሻገር ስለ ባለቅኔው ማንነት ስናስብ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በእውቀት ብቻ ሳይሆን በጾምና በጸሎት ሕይወታቸው የታነጸ ስለነበር አንዳንዶቹ መጻእያትን/ ወደፊት የሚኾኑትን ነገሮች የማወቅ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ያመለክታል።

**ቅኔ**[101]

በሕፅነ ምኒልክ ይረፍቅ ሰማዕተ ልዕልና

ወበሕፅነ ሰማዕት ይትሃወስ አሠረ ምኒልክ ላእከ እስመ እምሮምያ ፈተተ አድባረ ድንጋዬ ወሐውክ ምኒልክ ንጉሠ አድኅኖ ዘኢዮር መልአክ

ወእግረ ምኒልክ ኢይትሐወክ

እስመ በቅድሜሁ የሐውር ጸያሔ ፍኖት ወልደ አምላክ

ቡርክትሂ ገነተ ጽጌ እስመ ውእቱ ቡሩክ

በስመ ምኒልክ ቀዳማዊ ዘይመጽእ ምኒልክ ወሎቱ ሶርያ ትሰግድ ወታስተበርክ

በጽባሕ እስመ አቅረበ ሙስና ሮምያ

መሥዋዕተ ሠርከ

**ትርጉም**

የልዕልና ሰማዕት በምኒልክ ጭን (ጎን) ይቀመጣል።

በሰማዕት ጭንም (ጎንም) የንጉሥ

101 መናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መዘክር፣ አዲስ አበባ።

ምኒልክ ምልክት ይንቀሳቀሳል፡፡

የድንጋጤና የሁከት ተራሮችን ከሮም ቀራርሷልና

የማዳን ንጉሥ ምኒልክ የኢዮር

መልአክ ነው፡፡

የምኒልክ እግር አይታወክም፤

መንገድን የሚያቀና ወልደ አምላክ በፊቱ ይሄዳልና፡፡

ገነተ ጽጌም የተባረከች ናት፤

በቀዳማዊ ምኒልክ ስም የሚመጣ ዳግማዊ ምኒልክ የተባረከ ነውና፡፡

ሶርያም ለእርሱ ትሰግዳለች፤ ትንበረከካለች፤

የሮም ጥፋት (መደምሰስ) መሥዋዕተ ሠርክን

በማለዳ አቅርቧልና፡፡

ይህ መወድስ ቅኔ ይባላል፡፡ የቤተ መዘክሩ አስጎብኝ እንደገለጹት የቅኔው ባለቤት መልአከ ገነት ጽጌ የሚባሉ ሊቅ ናቸው፡፡ ቅኔውን የተቀኙት ከአድዋው ጦርነት ቀደም ብለው ነው፡፡ የቅኔው ዋና ምሥጢር ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በከበረ ሰማዕት (ቅዱስ ጊዮርጊስ) ተራዳኢነት ልባቸው በትዕቢት እንደ ተራራ የገዘፈ ፋሽስት ጣሊያኖችን በአድዋ ጦርነት ድል ማድረጋቸውን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ዓፄ ምኒልክ ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ኢትዮጵያን ከጠላት ወረራ በመታደጋቸው ባለቅኔው ንጉሠ አድኅኖ (የማዳን ንጉሥ) ዘኢዮር መልአክ (የኢዮር[102] መልአክ) በማለት ያሞግሳል፡፡ እንዲኹም ባለ ቅኔው ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወልደ አምላክ ክርስቶስ መንገዳቸውን (ሥራቸውን) የሚያከናውንላቸው መኾኑን ስለሚያምኑ እግረ ልቡናቸው ከአድዋ ጦርነት ወደኋላ እንደማይልና ልባቸው እንደማይታወክ ገልጠዋል፡፡ ይኽንንም እውነታ ጳውሎስ ኞኞ አጤ ምኒልክ በሚለው መጽሐፉ አንዳንድ ሰዎች የጣልያንን ገናናነት ለምኒልክ በመንገርና ዘመናዊ መሣሪያ ከታጠቀ ጣሊያን ሠራዊት ጋር ለመግጠም እንደማይቻል ወሬ ሲያናፍሱ ንጉሠ ነገሥቱ መኳንንቱን ሰብስበው በአንደበታቸው

102 የመላእክት ከተማ

የተናገሩትን በመጥቀስ እንዲህ ይላሉ "... አንፍራ! እኔ እንደኾንሁ መዝመቴን አልተውምና ስለኢጣሊያ ዘመናዊ መሣሪያና ገናናነት አትንገሩኝ፡፡ ኃይል የእግዚአብሔር ነውና እጋጠማለሁ፡፡ ብትዘምቱም ብትቀሩም ሬሳየን ከጦር ሜዳ ፈልጉት ..."[103]፡፡ በተጨማሪም በዚሁ መጽሐፍ ዓፄ ምኒልክ ለራስ ወልደ ጊዮርጊስና ለደጃዝማች ተሰማ ያስተላለፉት መመሪያ እንዲኽ የሚል ነበር "... ከእኔ ጋር ያለው ሠራዊት ብዙ ነው፡፡ ልክና መጠን የለውም፡፡ እግዚአብሔር ካልተለየን በትግሬ በኩል ላለው ጦር ይበቃል፤ እናንተም ወደ አውሳ ዝመቱ"[104] ብለዋል፡፡ እነዚኽ ጥቅሶች የሚያስረዱን ከላይ ባለቅኔው እንደተናገረው ንጉሠ ነገሥቱ በኃይለ እግዚአ ብሔር የሚታመኑና ከድንጋጤና ከሁከት የራቁ መኾናቸውን የሚያሳይ ነው[105]፡፡

የቅኔው ኹለተኛ ክፍል ምሥጢር ደግሞ "በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው" (ሉቃ. 19፥38) የሚለውን የወንጌል ቃል መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ድርሰቱ በቀዳማዊ ምኒልክ ስም የመጣውን ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያን የተባረከ ነው በማለት ያወድሳል፡፡

በመቀጠልም ከቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮ ውስጥ "መሥዋዕተ ነግህ መሥዋዕተ ሠርክ"[106] የሚለውን እንደ ምሳሌ በመጠቀም ባለቅኔው በሠርክ መሥዋዕት የተመሰለ የሮማውያን ድምሳሴ መኾኑን ይገልጻል፡፡ "ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ በማለዳ መሥዋዕት አቅርቧልና ሶርያ ትሰግድለታለች ትንበረከክለታለች" የሚለው ኃይለ ቃል የሚያስረዳን በአድዋ ጦርነት ጊዜ የጣሊያን ሠራዊት በኢትዮጵያውያን አርበኞች እጅ የካቲት 23 ከንጋቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ እንደ መሥዋዕት በግ አንገቱን መቀላቱንና ሥጋው መቆራረጡን ያሳያል፡፡

በመጨራሻም ባለቅኔው "ወሎቱ ሶርያ ትሰግድ ወታስተበርክ /ሶርያም ትሰግድ ለታለች ትንበረከክለታለች" በማለት በትንቢታዊ ቅኔያቸው የገለጹት የታሪክ እውነታ ነው፡፡ ለምሳሌ ጳውሎስ ኞኞ[107] እንደገለጡት በአድዋ ድል ጊዜ በመላው ዓለም ያሉ

---

103 ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣1984፣165፡፡

104 ዝኒ ከማሁ፣ 1984፡167፡፡

105 አበው "ባልና ሚስት ካንድ ወንዝ ይቀዳሉ" እንዲሉ የንጉሠ ነገሥቱ ባለቤት እቴጌ ጣይቱም ደፋርና ልበ ሙሉ በመኾናቸው ኮንት አንቶኔሊ የኢጣሊያ መንግሥት መልእክተኛ የውጫሌውን ውል በጦር ኃይል እንደሚያስከብር በዛቻ መናገሩን ሲሰሙ "የዛሬ ሳምንት አድርገው፡፡ በዚኽ የሚደነግጥልህ የለም፡፡ ሂድ የፎከርክበትን አድርግ፡፡ እኛም የመጣውን እናነሣዋለን፡፡ እግሩን ለጠጠር ደረቱን ለጦር ሰጥቶ አገሩን የማያድን ሰው በዚኽ የሌለ አይምሰልህ፡፡ የገዛ ደሙን ገብሮ ለገዛ አገሩ መሞት ጌጥ ነው እንጅ ሞት አይባልም፡፡ አሁንም ሂድ፤ አይምሽብህ፤ የፎከርክበትን በፈቀደህ ጊዜ አድርገው እኛም ከዚኽ እንቆይሃለን" በማለት ነበር የተናገሩት፡፡ (ዝኒ ከማሁ ፣148)

106 ጧትና ማታ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የምስጋና መሥዋዕት

107 ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣1984፣217-19፡፡

ጋዜጦች በመጀመሪያ ገጻቸው የምኒልክንና የጣይቱን ፎቶ ግራፍ በማውጣት የድሉን ዜና ለመላው ዓለም አሰምተዋል፡፡ ይኽንን የድል አድራጊዎች ዜና የሰማው ሕዝብ ሁሉ በፈረንሳይ በጀርመን በሩሲያና በአሜሪካ ታላላቅ ሕዝባዊ የደስታ ስብሰባዎች ማድረጉ የታሪክ ሐቅ ነው፡፡ “ እንኳን ደስ አለዎት” የሚሉ የተለያዩ ደብዳቤዎች ከዓለም ዙሪያ ካሉ መሪዎች እንደተላኩላቸውና አንዳንዶቹም የምኒልክን መልክ ለማየት ከመጓጓታቸው የተነሣ ለደብዳቤዎቻቸው መልስ እንዲጻፍላቸውና የምኒልክ መልክ ያረፈበት የኢተዮጵያ ቴምብር ተለጥፎ በፖስታ ቤት እንዲላክላቸው መጠየቃቸው ታውቋል፡፡ ጳውሎስ ኞኞ እንደሚያስረዱት ከኹሉም በላይ ከአውስትራሊያና ከቤኑዚላ የተጻፉት ደብዳቤዎች “የእርስዎ ወታደሮች መኾን እንፈልጋለን” የሚሉ ጥያቄዎችን የያዙ ነበሩ፡፡ ይኽም የትንቢታዊውን ቅኔ እውን መሆን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ ባለቅኔው በመወድሱ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ እንደገለጸው አጤ ምኒልክ በእግዚአብሔር ቸርነት እንዲሁም በሰማዕቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ መሪነትና ተራዳኢነት የሚተማመኑ መሆናቸውን ለማጠየቅ በራሳቸውና በሠራዊታቸው ኹሉ እጅ ባለው ሰይፍ “የምኒልክ ተስፋው እግዚአብሔር ነው”፣ “ቅዱስ ጊዮርጊስ” የሚለው ተጽፎ መገኘቱ የሚቀጥለው ሥዕል ምስክር ነው፡፡




**ሥዕል ፩፡- ዳግማዊ አፄ ምኒልክ**



**2ሥዕል ፪፡- የቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የተጻፈበት ሰይፍ**

(source:https://tse2.mm.bing.net/th?id=OIP.aa2C_gmpdfEjgZPOenDjLwHaDl&pid=15.1&P=0&w=318&h=155)

# ከአድዋ ድል በኋላ የተደረሱ ቅኔዎችና ምሥጢራዊ ትርጉም

የቅኔ ሊቃውንት የተለያዩ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበረሰባዊ፣ ተፈጥሯዊና የመሳሰሉ ክስተቶችን ለቅኔ ዘረፋቸው (ድርሰታቸው) መነሻ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህም የተነሣ ጥልቅና ረቂቅ ምሥጢርን ባዘለ ቅኔያቸው የአድዋን ድልና ተያያዥ ጉዳዮችን ሲያመሠጥሩት ኑረዋል፤ አሁንም ያመሠጥሩታል፡፡ ወደፊትም ታሪክንና የቅኔን ጥበብ የተካኑ ሊቃውንት እስካሉ ድረስ ይኽ ታሪካዊ የአድዋ ድል በቅኔ ጥበብ ሲዘከር ይኖራል፡፡ በዚኽ ክፍለ ርእስ ሥር ለናሙናነት የተካተቱት ቅኔዎች ከአድዋ ድል ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ገጽታዎችን ያንፀባርቃሉ፡፡ ለማስረጃ የሚከተሉትን ቅኔዎች እንመለከታለን፡፡

| **ቅኔ**[18] | **ትርጉም** |
|---|---|
| ፩ ሙሴ ፋሽስት ግብረ ማኅበር ይዜኑ | ሙሴ ፋሽስት የማኅበር ሥራን ያወራል፣ |
| ጽዋዐ እብሬት ይትወከፍ በዐለ ሰሙን አኮኑ፡፡ | የተራ ፅዋን ይቀበል ዘንድ ባለ ሳምንት ነውና፡፡ |

ይኽ ቅኔ የግእዝ ጉባኤ ቃና ሲኾን ባለ ቅኔው ለሐሳባቸው መነሻ ያደረጉት የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ሥርዐት መሠረት ምእመናን በየሳምንቱ እሑድ ወይም በወር ውስጥ ከሚውሉት ቅዱሳን በዓላት መካከል አንዱን መርጠው በመሰባሰብ፣ ማኅበር (አንድነት) መሥርተው መንፈሳዊ ጽዋ ይጠጣሉ። የማኅበሩ ሰብሳቢ ሙሴ[108] ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ኀላፊነቱም ማኅበሩን መምራትና የሚቀጥለው ሳምንት (ወር) ተረኛ ማን እንደሆነ በማሳወቅ ጽዋውን እንዲቀበል ማድረግ ነው። በዚህ አንጻር ፋሽስት ጣሊያንን በሙሴ በመመሰል ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያውያንን በግፍ ከጨፈጨፈ በኋላ የዕልቂቱን ጽዋ በተራው መቀበሉን፣ የሽንፈት ጽዋ መጎንጨቱን አመሥጥረዋል።

**ቅኔ** (አሠረ ንጉሥ)[109]

በወርኀ ምኒልክ ሰላም ዘአግበርክሙ
መጥባሕተክሙ ማኅረሰ
ኰናተ ሐራ ግበሩ ይእዜ ማዕጸደክሙ ሐዲሰ
ማእረሩ ለዔሳው እምድኅረ የብሰ
ሐመልማለ ገመል ኢያውፅእ ወጽጌ ፈረሰ
በአትልዎ ዘነበ ወርእሰ።

**ትርጉም**

በምኒልክ ሰላም ወራት ሾተላችሁን ማረሻ
ያሠራችሁ (የሠራችሁ)፤
አዲስ ማጭዳችሁን የወታደሮች

108 ሙሴ ተብሎ መሰየሙ በኦሪት ዘመን የነበረው ነቢዩ ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን በአንድነት መርቶ ባሕረ ኤርትራን አሻግሮ ሕገ እግዚአብሔርን እያስተማረ ከአምልኮ ጣኦት ወደ አምልኮ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኀጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ እንደመለሳቸው ኹሉ እርሱም ቃለ እግዚአብሔርን እያስተማረ፣ የታመሙትን እየጠየቀ፣ የተጣሉትን እያስታረቀ፣ የተቸገሩት እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ እያመቻቸ የማኅበሩ አባላት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ልዕልና እንዲኖራቸው ለማገዝ የተመረጠ በመሆኑ ሙሴ ተብሎ ተሰይሟል።

109 የግእዝ ቅኔያት የሥነ-ጥበብ ቅርስ 2ኛ ቅጽ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ 1984፣112።

ጦር አድርጉ።

የዔሳው አዝመራ ከደረቀ በኋላ

ገመል ልምላሜን፣ አበባ ፈረስንም

እንዳያወጣ

ጅራትንና ራስን በማስከተል።

ይኽ ቅኔ የእዝል እጣነ ሞገር ቅኔ ሲሆን በተለየ ስሙ አሠረ ንጉሥ በመባል ይታወቃል። የቅኔው ዋና ጭብጥ ጦርነት በሌለበትና ሰላም በሰፈነበት ዘመን ሾተልን (ሰይፍን፣ ጋሻን ወዘተ) ማረሻ ማሠራት እንደተለመደ ኹሉ፤ በጠብ ዘመን ደግሞ ማጭድን ወይም ማረሻን ወደ ጋሻና ጦር ቀይሮ ለማሠራት የሚያስመኝ መሆኑን ይገልጻል። በዚኽም መሠረት ባለቅኔው ዓፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት ጣልያንን ድል ከነሱ በኋላ አርሶ አደሩ ያለ አንዳች ጦርነት በሰላም እያረሰ መኖሩን በማስታወስ አሁን ግን ጣልያኖች የአድዋን በቀል ለመበቀል ለጦርነት መንቀሳቀስ ሊጀምሩ እንደሚችሉ በመጠቆም አርሶ አደሩ ያለ አገር ነጻነት ማረስና ማዝመር ስለማይችል ወደአርበኝነት ተግባር እንዲንቀሳቀስ ባለቅኔው ያሳስባሉ። አዝመራ ከደረቀ በኋላ እንደማያለመልምና እንደማያብብ ቢታወቅም የዔሳውም (የአረቦችም ጠብ) ደጀንና ፊታውራሪን በማከታተል የግመልን በቀልና[110] በፈረስ የሚካሄድ ጦርነትን እንዳያመጣ በመስጋት ባለቅኔው በዘመናቸው የነበሩትን ኢትዮጵያውያንን በቅኔያቸው አስጠንቅቀዋል። በበቀለኛነቱ በግመል የተመሰለው ጣሊያን በአድዋ ጦርነት የሽንፈትን የሞት ጽዋን ቀምሶ ከተመለሰ በኋላ ለብዙ ዓመታት ሲዘጋጅ ቆይቶ ኢትጵያን በድጋሜ ለመውረር መነሣቱ ሊቁ በቅኔያቸው የገለጹት ሥጋት እንዳልቀረ ያስረዳል።

**ቅኔ**[111]

፫ ምኒልክ ኢበልዓ ኀፍረተ ቀትል

እምነ ይሁዳ ዘተርፈ

ወበበትረ እድ ዘኮነት ለከንቱ ዘባነ ፀሩ

ቀሠፈ

---

[110] የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቃውንት የግመልን በቀለኛነት እንዲህ በማለት ይገልጡታል "ግመል በቀለኛ ናት፤ አጥብቆ የመታትን እስከ ስድስትና ሰባት ዓመት አትዘነጋም፤ ባጥ ብላ (ዘልላ) ትረግጠዋለች ስፍራ ሲመቻት ገደል ገፍታ ትጥለዋለች" (ማቴ.3፥4)፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣1988።

[111] የግእዝ ቅኔያት፣ ሁለተኛ ቅጽ፣1984፣381።

እስመ ፀር ስመ ዘተሳተፈ
ትምክህተ ሰናክሬም ቈጽለ ጊዜ ነግህ ተዐጽፈ
ወበሠርክ ፍሬሁ ተነግፈ።

**ትርጉም**

የይሁዳ ትራፊ የሆነ የጦር ጎፍረትን
ምኒልክ አልበላም፤
ለከንቱ በኾነች የእጁ በትርም (ሰይፍ)
የጠላቱን ጀርባ ገረፈ (ቆረጠ)
በስም የተሳተፈ (አንድ የሆነ ጠላት)
የሰናክሬም ትምክህት ቅጠልን በነግህ ጊዜ
ተጎናጽፏልና፤
በምሽትም ፍሬው ረግፏልና።

የዚኽ ቅኔ ዋናው መልእክትም በባህል ላይ በተመረኮዘ ምሳሌና በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው። በባህላችን አንድ በማዕረግም ሆነ በዕድሜ አነስተኛ የሆነ ሰው ያስተረፈውን ፍርፋሪ (ምግብ) ከእርሱ የሚልቅ ሰው አይበላውም። በታሪክ ደግሞ ይሁዳ (ከዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ የነበረው) ጦረኛ (ወታደር) እንደነበረና አባቱንና እናቱን ማርኮ አሳፋሪ ተግባር እንደፈጸመ ይታወቃል[112]። ባለ ቅኔው የይሁዳን ጦርነት ከአድዋው ጦርነት ጋር በማነጻጸር ዓፄ ምኒልክን የጦርነት ትራፊን አልበላም (በጦርነቱ ድል አልሆነም) በማለት ያመሠጥራል። ይልቁንም የአህያ ጀርባ በበትር እንደሚመታ ዓፄ ምኒልክም የጠላታቸውን የጣሊያንን ጀርባ በእጃቸው (በሠራዊታቸው) እጅ ላይ ባለች በትር (ሰይፍ) ቆራረጡት ይላል። በተጨማሪም በንቀትና በትዕቢት በይሁዳው ንጉሥ በሕዝቅያስ ላይ ሲዘብት የነበረውን የአሦርን ንጉሥ ሰናክሬምን በእግዚአብሔር ቸርነት ሕዝቅያስ ድል እንዳደረገው[113] እንዲሁም ገና ሳይዋጋ "… በቅርብ ቀን ምኒልክን በቀፎ ውስጥ አስሬ ሮማ አመጣዋለሁ…"[114] በማለት በሮም አደባባይ ጉራውን ሲቸረችር የነበረውን የጀኔራል ባራቲየሪን ሠራዊት በኃይለ እግዚአብሔር የሚመካው ዓፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት ላይ ጧት ታይቶ ማታ እንደሚረግፍ ጤዛ እንዳረገፈው ባለቅኔው ገልጸዋል።

---

[112] አባቱን ሰልቦ ገድሏል፤ እናቱንም በግብር አውቋታል። (የማርቆስ ወንጌል አንድምታ ትርጓሜ "…ወምስሌሆሙ ትልቁ ዝኩ ዘፍጥረቱ ክርዳድ … ይሁዳ ዘአግብአ" የሚለውን ተመልከት።

[113] ነገሥት 19፥35

[114] ጳውሎስ ኞኞ፣አጤ ምኒልክ፣1984፡163።

**ቅኔ**[115]

ሰላም አልብነ ምስለ ሰብአ ሮሜ ወለሰብአ
ሮሜ ምስሌነ ኢሀለዎሙ ሰላም
ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመደ ሥጋ ወአጽም
እስመ ከተረነ ደምከ ቀለም።
ኦ ዘትሠይም
ቀስተ ሕይወታ ለነፍስ በደመና
ገቦ ንዝሀተ ደም
አንተሰ ታስተዴሉ በውስተ ዛቲ ዓለም
ኪያሆሙ ለጥኢና ወኪያነ ለሕማም
ወእንዘ እምጥንትነ ጴጥሮስ በተዓድዎ ሕግ ፍጹም
ለዘተፃብዐከ ንፃብዖ ወዘተቃወመከ
ንትቃወሞ።

**ትርጉም**

የአጥንትና የሥጋ ዘመድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ
ከሮም ሰዎች ጋር ሰላም የለንም።
ለሮም ሰዎችም ከእኛ ጋር ሰላም የላቸውም
ደምህ ቀለም ከትሮናልና (ለይቶናልና)። የነፍስ የሕይወቷ በጎን/ ደመና የደም ርጭት የምትሸም አንተ ነህ፤
አንተ ግን በዚህች ዓለም እነርሱን
ለጤንነት፣ እኛን ለሕማም ታዘጋጃለህ።
ከጥንታችን /ጴጥሮስ ጀምረን ፍጹም
ሕግን በመተላለፍ
የተጣላህን እንጣላዋለን፣የተቃወመህንም
እንቃወማለን።

የዚኽ ቅኔ ምሥጢር መሠረት ያደረገው ባህልን ነው። ይኸውም አንዱ የአንዱን ወንድም በመግደሉ ምክንያት በደም የተለያዩ ሰዎች በማንኛውም ማኅበራዊ ጉዳይ አይገናኙም። ባለ ቅኔው በዚኽ ባህላዊ እውነታ ላይ ተመሥርተው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ ባፈሰሰው ደም ላይ በተመሠረተው እምነት (ሃይማኖት) የሮማ ካህናትና

[115] አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)፣ መጽሐፈ ቅኔ ዝክረ ሊቃውንት፣ 1963፡718።

የኢትዮጵያ ካህናት አይተባበሩም፣ አንድ አይደሉም፡፡ ከዚኸም የተነሣ የሮም ካቶሊክና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት አብረው አይቀድሱም፤ በአንድነት አይቆርቡም፡፡ ዳግመኛም ዓለምን በጥፋት ውኃ እንዳያጠፋት ቀስትን በደመና/ ቀስተ ደመና (የቃል ኪዳን ምልክት) አምላክ እንዳደረገ፣ የሰዎችን የነፍስ መዳንም በደሙ ፈሳሽነት አደረገ፡፡

በክርስቶስ ኹለት ባሕርይ ሁለት ፈቃድ በማለት የሃይማኖትን እውነተኛ መንገድ የለወጡ የሮም ካህናት ተቃዋሚዎች ሲሆኑ (በመቃወማቸው)፣ ኢትዮጵያውያን ለሥጋዊ መከራ ተዳረጉ፡፡ ይኸም ማለት ሃይማኖትን የሚለውጥና የሚያጠፋ ፋሽስትን በመዋጋት ኢትዮጵያውያን ብዙ መከራ የደረሰባቸው መኾኑን ያስገነዝባል፡፡ ጠቅለል ባለ አገላለጽ፣ ሮማውያን (ጣልያኖች) ግዛትን የማስፋፋት ፍትወታቸውን ለመፈጸም ይረዳቸው ዘንድ፣ የሮም ካህናት ሃይማኖትን እንሰብካለን በማለት በሃይማኖት ሰበብ ያደረጉት ሙከራ የስለላ ተግባር[116] መኾኑን የተረዱት ባለቅኔው "ሰላም አልብነ ምስለ ሰብአ ሮሜ፤ ከሮም ሰዎች ጋር ሰላም የለንም" በማለት አመሥጥረውታል፡፡

**ቅኔ**

አልብየ ምት ብሂሎትኪ ኢትዮጵያ
እሙን ወኢይትሔሰው ቃልኪ ለመርዓዊ
ሕግ እስከ ምጽአቱ
ምትኪ አምጣነ ኢኮነ ዘሀሎ ምስሌኪ[117]

**ትርጉም**

ኢትዮጵያ ሆይ፣ ባል የለኝም ማለትሽ
የታመነ ነው፤ ቃልሽም አይታበልም፡፡
እስከ ሕግ ሙሽራው መምጣት ድረስ
ካንች ጋር ያለው ባልሽ አልሆነምና፡፡

ይኽ ቅኔ ሕንጼሃ ወይንም ሣህልከ ይባላል፡፡ ባለ ቅኔው የተጠቀሙት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሳምራዊቷን ሴት ባነጋገራት ጊዜ "ሂጅና ባልሽን ጥሪው" ቢላት እርሷም "ባል የለኝም" አለችው፡፡ ጌታም መልሶ "ባል የለኝም ማለትሽ እውነት ነው አምስት ባሎች ነበሩሽና፡፡ አሁን

[116] አስረስ የኔሰው፣ትቤ አክሡም መኑ አንተ? 1951፡2፡፡
[117] የግእዝ ቅኔያት የሥነ-ጥበብ ቅርስ 3ኛ ቅጽ፣1995፡194፡፡

ግን ካንች ጋር ያለው ባልሽ አይደለም"[118] አላት፡፡ ባለ ቅኔው ይኽን የወንጌል ቃል ምሳሌ በማድረግ ኢትዮጵያ በአምስቱ የኢጣልያ ወረራ ዓመታት መሪ እንዳልነበራት ለጊዜው ኢትዮጵያን እገዛለሁ ይል የነበረው ግፈኛው ፋሽስትም መሪዋ አለመሆኑን ከማመሥጠራቸው ጋር፣ የራስዋ መሪ እንደሚመለስና ፋሽስት ኢጣልያም የኢትዮጵያ ገዥ ሆኖ እንደማይቀጥል ተንብየዋል፡፡ ከዚኽም መረዳት ያለብን ሌላው ጉዳይ ባለቅኔው ንጉሥንና ሀገርን በባልና ሚስት የመመሰላቸው ምሥጢር ነው፡፡ ይኸውም ባልና ሚስት በመተማመንና በመፈቃቀር ላይ የተመሠረተ ትዳር ከሌላቸው ትዳራቸው ሊጸና ጎጇቸው ይቀናል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ልጅ ወልደው በምግባር በሃይማኖት አንጸው ማሳደግ አይችሉም፡፡ ቤታቸው ኹል ጊዜ እንደበረዶ የሚቀዘቅዝ ወይም እንደ እሳት የሚያቃጥል ድባብ ይሰፍንበታል፡፡ ከዚኽም አልፎ ባል በኀይልና በጉልበት ሚስትን አስገድዶ ለመግዛት ቢሞክር አይሳካለተም፤ መጠፋፋትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡ እንዲኹም መንግሥት (ንጉሥ) እና ሀገር (ሕዝብ) በመተማመንና በመደማመጥ ካልኾነ ምንም ዓይነት መልካም ውጤት ማስመዝገብ አይቻሉም፡፡ መንግሥት የሚያወጣቸው ሕጎችና ደንቦች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡ ከዚኽም የተነሣ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል በየጊዜው በሚደረጉ ፍጥጫዎች የብዙ ሰዎች ደም ይፈስሳል፡፡ በተቃራኒው ባልና ሚስት አንድነታቸውን በመተማመንና በመግባባት ላይ የመሠረቱ እንደኾነ አንድነታቸው ይጸናል፤ትዳራቸው ይቀናል፤ ሀብታቸው ይበዛል፤ ጎረቤት ዘመድ አዝማድ ምሳሌ ያደርጋቸዋል፡፡ እንዲኹም መንግሥትና ሕዝብ ልብ ለልብ ተናቦ በመወያየትና ችግሮችን በጋራ በመፍታት የሚጓዝ ከኾነ ሀገር ትለማለች፤ ሰብአዊ መብት ይከበራል፤ ኹሉም እንደሚገባው የድርሻውን ያገኛል፡፡

## ቅኔ

አልቦ እምሕዝብ ዘአጠየቀነ
ከመ እምአይቴ ምጽአቱ ወኀበ አይቴ ነገዱ
 ለዘእምርትቅ መጽአ ያርብኃ ገዳም አሐዱ
ፍጹመ እስመ ይመስሎ ለሉቃስ በእዱ
ወካዕበ ይመስል
ዮሐንስሃ ነቢየ እምነ ርእሱ እስከ ክሳዱ
አስይፍትሂ ኀለይተ ሞት እለ ተአንገዱ
በቅድመ ባዕል ያርብሃዊ በክሣድ ይወርዱ

[118] ዮሐ 4፥1-18

አኮኑ ውእቱ ለያርብሐዊ መፍቅዱ
ሥጋሁ ከመ ይብልኡ ባዕዳኒሁ ምስለ
አዝማዱ፡፡

**ትርጉም**

ከሩቅ የመጣ አንዱን የዱር አርበኛ
አመጣጡ ከየት ነገዱም ከወዴት እንደኾነ
ከሕዝብ ያስረዳ የለም፡፡
ሉቃስን በእጁ ይመስለዋልና፤
ዳግመኛም ከራሱ እስከ አንገቱ
ነቢዩ ዮሐንስን ይመስላል፡፡
እንግዶች የሆኑ የሞት ዘፋኞች /ሰይፎችም
በባለጸጋ አርበኛ ፊት በአንገት ይወርዳሉ፡፡
ባዕዳኑ ከዘመዶቹ ጋር ሥጋውን ይበሉት ዘንድ ለአርበኛ ፈቃዱ ነውና፡፡

እንግዳ ሰው "ሲታይ ከየት መጣህ" "የማን ወገን ነህ" "ከራስ ቅልህ ከፊት አወራረድህ እገሌን ከእጂህ አካባቢ እግሌትመስላለህ"ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ እንዲሁም ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት በዱር በገደል በዋሻ በፍርኩታ ወድቆ ይገኝ የነበረው ኢትዮጵያዊ አርበኛ በእጁ ሉቃስን በራሱና በአንገቱ ዮሐንስን ይመስላል፤ ማለትም አርበኛው እንደ ሉቃስ እጁን፣ እንደ ዮሐንስ መጥምቅ አንገቱን መቆረጡንና በስም ይኽ እገሌ ነው ያ እገሌ ነው ተብሎ ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑን ባለቅኔው ያስረዳሉ፡፡ ይኽም ፋሽስት ኢጣልጣን በወገኖቻችን ላይ ያደረሰው መከራና ግፍ ምን ያኽል አሰቃቂ እንደነበር ከዚኽ ቅኔ መረዳት እንችላለን፡፡

በቅኔው ኹለተኛ ክፍል አዝማሪዎች በባለጸጋ ፊት እስክስታ በአንገት እንደሚወርዱ፣ ሰይፎችም (ጎራዴዎች) በአርበኛ ፊት በአንገት ይወርዳሉ ማለት አርበኛው በፋሽስት ጎራዴ አንገቱ እየታረደ ሥጋው እየተቀረደደ መገደሉ ተመስጥሯል፡፡ ባዕዳኑ ከዘመዶቹ ጋር ሥጋውን ይበሉ ዘንድ ለአርበኛ ፈቃዱ ነውና ማለትም ባዕዳን የተባሉ ፋሽስት ኢጣልያን ዘመድ ከተባሉ ኢትዮጵያውያን ባንዳዎች ጋር አርበኛውን ለመውጋት ቢተባበሩም አርበኛው ወደኋላ ሳያፈገፍግ አንገቱን ለሰይፍ ደረቱን ለጦር ለመስጠት ፈቃደኛ ኾነ በማለት ሊቁ ያመሠጥራሉ፡፡

ምኒልክ ከብካብ የዓለም
መጀመሪያ ኢትዮጵያ እምከ
ዘኢታፈቅር ደመኛ ከጥቁር ጋራ
ነጩን አቅርባልን ነበር ለእኛ

እኛም ብናየው በየጊዜው፣
ይሻላል ከነጩ
የወትሮው መናኛ፤
ጣልያን ጋለሞታ
ጋግራዋለችና ነጩን ወፍራም አድርጋ
ክፉኛ፣ አመትከሂ ምድረ ትግራይ
የማትገዛ ለዳኛ፣ የጸነሰችውን ሰብአ
ሮሜ አስወረደችው ለተኛ። ማእከለ
መትረየስ ወመድፍ ላእካነ ንጉሥ
ሰልፈኛ በደም አይቷታልና ጎራዴህ ክፉ
ቁራኛ።[119]

ከላይ ያለው መወድስ ቅኔ ምንም እንኳ ፍርንዱስ (ግእዝና አማርኛ) ቢሆንም በውስጡ የያዛቸው ሐሳቦች ግን ትንታኔ የሚያስፈልጋቸው ናቸው። ከብካብ ማለት ሠርግ ሲሆን ሠርግ ደግሞ በዚህ ዓለም የማኅበራዊ ኑሮ መጀመሪያ ነው። ማለትም አንድ ሰው ትዳር ከመሠረተ በኋላ በአካባቢው ያለው ማኅበረሰብ ጋር በሚተዳደርበት ሕግና ደንብ መገዛት ይጀምራል፤ ለምሳሌ በእድርና በመሳሰሉ ነገሮች ይሳተፋል። በዚኽ ምሳሌ መሠረት ከብካብ በተባሉ ዓፄ ምኒልክ አማካኝነት ኢትዮጵያ ከዓለም ሥላጣኔ ተቋዳሽ መኾኗን ቅኔው ያመሠጥራል። አሁንም ባለቅኔው በነጭ ጤፍና በጥቁር ጤፍ ማንጻሪያነት ጣሊያናዊውን እና ኢትዮጵያዊውን አስተዳደር እያነጻጸሩ የጥቁር ጤፍ እንጀራ ከነጭ ጤፍ እንጀራ የተሻለ ጥቅም እንዳለው ኹሉ እንዲኹም ሲያዩት የሚያምር ከሚመስለው ነገር ግን ጥቅም ከሌለው ከነጩ ጤፍ (ጣሊያናዊ ቅኝ ገዥ) መናኛ/የማይረባ የሚመስለው ጥቁሩ ጤፍ (ኢትዮጵያዊ መሪ) እንደሚሻል ቅኔው በምሥጢር ያስረዳል። ከመጠን በላይ ወፍራም ሆኖ የተጋገረ እንጀራ ለመብላት እንደማይመረጥ ኹሉ ጋለሞታ የተባለች ጣልያን ዜጎቿን ልበ ወፍራም/ ደንዳናና ጨካኝ አድርጋ ጋግራቸዋለችና ማለት አሳድጋቸዋለችና ለአገዛዝ አይመቹም እያለ ነው።

በመጨረሻም ዓይነ ወግ ክፉ ቁራኛ/ ሾተላይ የርጉዝ ሴት ፅንስን እንደሚያስወርድ፣ የምኒልክ ጎራዴም የኢጣልያንን ሠራዊት እንደውርጃ እየበጣጠሰ ከትግራይ ምድር ማስወጣቱን ቅኔው ያስረዳል። አንድም የምኒልክ ፓለቲካዊ ተቃዋሚ የነበረው ራስ መንገሻ በአድዋ ጦርነት ምክንያት ለጊዜው ከምኒልክ ጋር በመተባበር ለድሉ መሠረታዊ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢኾንም በኋላ ግን 80ሺህ ጦር አሰልፎ

[119]የግእዝ ቅኔያት የሥነ-ጥበብ ቅርስ 3ኛ ቅጽ፣1995፣135።

የምኒልክን ንጉሠ ነገሥትነት እንደማይቀበል አስታውቆ ነበር። ይኹን እንጂ ዓፄ ምኒልክ በራስ መኰንን የሚመራ 40ሺህ ጦር ሲያዘምቱበት ገና ወሳኙ ግጥሚያ ሳይደረግ የመንገሻ ሠራዊት መፍረክረክ መጀመሩን ታሪክ ያስረዳል።[120]

## ማጠቃለያና አስተያየት

ከላይ በተጠቀሱት ቅኔዎች ውስጥ እንደተመለከትነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዕውቀታቸው ጥልቅ አእምሯቸው ምጡቅ ከመሆኑ የተነሣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀታቸውን በሃያማኖታዊ አስተምህሮ ብቻ ሳይገድቡት ወቅታዊ ጉዳዮችንም ለመተንተን እንደአስፈላጊነቱ በምሳሌነት እንደ ተጠቀሙበት ያሳያል። ሊቃውንቱ ሐሳቦቻቸውንም ሲያቀርቡ ምክንያታዊ (Logical) የሆኑ ማስረጃዎችን በማቅረብ በመኾኑ የአድማጮቻቸውን ልቡና የመግዛትና የመማረክ አቅማቸው እጅግ ከፍተኛ መኾኑንም ከቅኔዎቻቸው እንገነዘባለን። በቅኔዎቹ ውስጥ የተንጸባረቀውና ልናስተውለው የሚገባን ሌላው ወሳኝ ጉዳይ፣ ፋሽስት ጣልያን ሀገራችንን በተደጋጋሚ ሲወር አርበኞች አባቶቻችን ሰይፍ መዝዘው ጦር ሰብቀው ጠላትን ለመመከት ሲዋጉ፤ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መንፈሳውያን አባቶቻችን ደግሞ ከጸሎታቸው ባሻገር በቅኔያቸው ነገሥታቱና አርበኞቹ አስቀድመው እንዲዘጋጁ የማስጠንቀቅና የማነቃቃት ሥራን በመሥራት ኃላፊነታቸውን በሚገባ ተወጥተዋል። በተጨማሪም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንነቱ እንዲኮራና ለነጻነቱ አስፈላጊውን መሥዋዕትነት እንዲከፍል ዋጋ ከሌለው ነጭ ጤፍ (ፋሽስት) ይልቅ ዋጋ ያለው ጥቁር ጤፍ (ኢትዮጵያዊ መሪ) ይሻልሃል፤ እውነተኛ ባሏ (ንጉሧ) እስኪመለስ ድረስ ኢትዮጵያ ትጠብቃለች፤ … እያሉ የአርበኛውንና የሕዝቡን ሥነ ልቡና በማነቃቃትና በማበረታታት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ከኹሉም በላይ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን ለአፍሪካ በሙሉ የነጻነት እንቅስቃሴ መሠረት የሆነውን ድል ያጎናጸፉን አባቶቻችን የከፈሉትን መሥዋዕትነት ለማወቅ እንችል ዘንድ ዘመን ተሻጋሪ በሆኑ ቅኔዎቻቸው ለአሁኑም ኾነ ለወደፊቱ ትውልድ የሚበቃ የታሪክ ገጸ በረከት አውርሰውናል።

በመጨረሻም በዚኽ ጥናት ውስጥ በናሙናነት ከተካተቱት በቁጥር ጥቂት ከኾኑ

[120] አንደርዜይ ባርትኒስኪ እና ዮዓና ማንቴል-ኒዮችኮ፣(ዓለማየሁ አበበ፣ተርጓሚ)፣የኢትዮጵያ ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ አሁኑ ዘመን (2005፣429)

ቅኔዎች ከላይ ያለውን ጠቋሚ መረጃን ማግኘት ከተቻለ በተነሣው ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ተጨማሪ ቅኔዎችን መሰብሰብና ማጥናት ቢቻል ላቅ ያለና ሚዛን የሚደፋ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል መገመት አይከብድም፡፡ በመኾኑም በዚኽ ጥናት በተዳሰሰውም ኾነ በሌሎች ተዛማጅ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ሊሎች አጥኝዎች ትኩረት እንዲያደርጉበት የዚኽ ጥናት ባለቤት መጠቆም ይወዳል፡፡

# የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ለዘመን አቆጣጠር፣ ለከዋክብት እና ለአየር ትንበያ ጥናት መጽሐፈ ሄኖክ መነሻ

ዮሐንስ ደምስ በለጠ[121]

## አኅፅሮተ ጽሑፍ

ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው የቍጥር ትምህርት ነው፡፡ ይኸ ትምህርት የፀሐይን፣ የጨረቃን፣ የክዋክብትንና የነፋሳትን ዑደታቸውንና የቆይታ ጊዜያቸውን ርዝማኔ ለይቶ ይቈጥራል፡፡ በእነዚኽ ዑደቶች አማካኝነት ዘመናትን ለመቍጠር፣ አንዳንድ ያለፉ እና ወደፊት የሚመጡ ክስተቶችን ጊዜያቸውን ለማስላት ይጠቅማል፡፡ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መነሻው ዘመነ ፍጥረት ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት መነሻ መጽሐፈ ሄኖክ መኾኑንና ለዘመን አቈጣጠር፣ ለከዋክብት እና ለአየር ትንበያ ጥናት ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተለያዩ ፍጥረቶችን ለመመራመር የሚጠቀሙበት ዐቢይ መጽሐፍ መጽሐፈ ሄኖክ ነው፡፡ ስለዚኽ መጽሐፈ ሄኖክ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር እንዲኹም የባሕረ ሐሳብ ፍልስፍናውና መሠረቱ ከሄኖክ መጽሐፍ የተቀዳ ነው፡፡ ይኽንንም ለማረጋገጥ የተለያዩ የጽሑፍ ማስረጃዎችን በማመሳከር፣ ሊቃውንትን በመጠየቅ ጥናቱ ተከናውኗል። የጥናቱ ውጤት የኢትዮጵውያን የዘመን አቈጣጠር ስልት በፀሐይ፣ በጨረቃና በከዋክብት እንደ አስፈላጊነቱ የሚቈጥር እንደኾነ፤ ባሕረ ሐሳብ ትምህርት በዘመናዊ ሳይንስ ከፍተኛ የሒሳብ ዕውቀት በተለይ “Algebira & Trigonometry” እንዲኹም የምርምር ችሎታ የሚጠይቀውን ትምህርት በቃል ብቻ ያለ ሒሳብ መሥሪያ ማሽን መሥራት እንደሚቻል የሚያሳይ ሀገር በቀል ጥበብ ነው፡፡ በተጨማሪም ቀደም ባሉት ዘመናት ባሕረ ሐሳብ ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው የትምህርት ዘይቤ የነበረውን አጠናን እና የማኅበረሰቡን ከፍተኛ የፍልስፍና ጥበብ በዘመን አቈጣጠር፣ የሰማይን ‹‹ምሥጢር›› ለማወቅ (astronomical studies)፣ ለኮከብ ቈጠራ (astrology)፣ ለአየር ንብረት ትንበያና ስለወቅቶች መፈራረቅ (meteorology and climate studies) ለመሳሰሉት ጉዳዮች የሚያገለግል ጥበብ ነው፡፡

**ቍልፍ ቃላት**:- *መጽሐፈ ሄኖክ፣ ባሕረ ሐሳብ፣ አቡ ሻኽር፣ ሥነ-ፈለክ*

[121] BSC mathematics & Msc Computational and data science, AAU, Email: yohannesd23@gmail.com

# መግቢያ

ጥንታዊዉ የኢትዮጵያ የቍጥር ትምህርት የዘመን አቈጣጠር እና የሥነ-ፈለክ ጥናት ዐጠቃሎ የያዘው ትምህርት ስያሜ በሊቃውንት ዘንድ አከራካሪ ነው። ለምሳሌ አለቃ ያሬድ ባሕረ ሐሳብ አጽዋማት እና በዓላትን፣ የፀሐይ፣ የጨረቃ፣ የከዋክብት እና ሐሳበ ነፋሳትን አጠቃላይ የያዘውን ባሕረ ሐሳብ ይሉታል። በሌላ በኩል አባ ገብረሥላሴ ወ/ሚካኤል ደግሞ በዓላት እና አጽዋማት የያዘውን መረጃ መጽሐፍ ብለው ሰይመውታል። መምህር ስቡሕ አዳምጤ ፣ጌታቸው ኀይሌ እና መሪጌታ ዘነበ ኀየሎም አጽዋማት እና በዓላት ላይ የሚያተኩረውን መጽሐፍ ባሕረ ሐሰብ ብለው ይጠሩታል። ይኹን እንጂ ይኽ ጥናት ኹሉንም አጠቃሎ የያዘውን የአለቃ ያሬድን ባሕረ ሐሳብ የሚለውን መጠሪያ የሚጠቀም ይኾናል። ሊቃውንት ጥልቅ የኾነውን የሥነ-ፈለክ ትምህርት ማለትም ሥለ ፀሐይና ጨረቃ ዑደት እና የነፋሳትን ምሥጢር የሚያጠናውን አቡሻኽር እንደኾነ እና የዘመን አቈጣጠር ደግሞ ባሕረ ሐሳብ ብለው የሚከፍሉ እንዳሉ ኹሉ ከስሙ ትርጓሜ በመነሣት ባሕረ ሐሳብ ኹሉን ያዘ ነው የሚሉ ሊቃውንት ደግሞ በርካታ ናቸው። በመኾኑም ይኽ ጥናት በዋናነት ባሕረ ሐሳብ የሚለውን እንደ አጠቃላይ በመውሰድ የተዘጋጀ ነው።

ከላይ አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው ባሕረ ሐሳብ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብትን በመጠቀም እንዲኹም የነፋስን አቅጣጫ በመረዳት፤ ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመትን የመሳሰሉ የጊዜ ርዝመቶችን መለኪያዎች አድርጎ በመከፋፈል፣ ለዚኽም የሚኾን ዘዴ ደንብና ሥርዓት በማዘጋጀት ለሃይማኖታዊም ኾነ ለተቋማዊ ሥራዎች የሚረዳ ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚጠቅም ነው። [122] ይኽም እንደ እርሻ፣ ንግድና ሌሎችም የኅብረተሰብ ጉዳዮችን በሥነ ሥርዓት ለመከወን ያግዛል። የዘመን አቈጣጠር ሥለ ማኅበራዊ ኑሮ ጠቀሜታና በሃይማኖት ተግባሮችን ለማከናወን በሚያገለግል መልኩ ተፈጥሮአዊዉን የወቅቶች ክፍፍል እርስ በእርሳቸው የሚያመ ቻችበት ዘዴ ነው። እንዲኹም ዓመት ወስኖ ወደ ትንንሽ ክፍሎች በመከፋፈል እነዚያ ትንንሽ ክፍሎች ደግሞ ስንት ቀኖች እንደሚኖራቸው የመወሰን ደንብ በመኾኑ የሕዝብና የሃይማኖት በዓላት ቀኖችን አስቀድሞ ለማወቅና ዕቅድ ለማውጣት ይረዳል።

[122] ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም. *ባሕረ-ሐሳብ የዘመን ቆጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ።*

የዚኽ ጥናት ዋነኛ ትኩረት መጽሐፈ ሄኖክ ለኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መነሻ መኾኑን ማጠየቅ ሲኾን፣ ጥናቱ 1980 ዓ.ም በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ታትሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የዋለውን መጽሐፈ ሄኖክ የሚዳስስ ነው፡፡

# የጽሑፉ አነሳሽ ምክንያት

የዚኽ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የኾነው የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንጩ በተለያዩ ሊቃውንት ዘንድ ያለው የሐሳብ ልዩነት ማጥናት እና የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ይዘትን በስፋት ማስገንዘብ ነው፡፡ አንዳንድ ምሁራን የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መነሻ የኾነው ባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንጩ ከግብፅ እና ከዕብራውያን እንደኾነ[123] በተጨማሪም ከጎርጎርዮሳውያን አቈጣጠር ጋርም አንድ ዓይነት እንደኾነ የሚያስረዱ ሲኾን ይህንን ሐሳብ በመሞገት የዚኽ ጥናት ዋነኛ ጉዳይ የኢትዮጵያ ዘመን መቍጠሪያ ባሕረ ሐሳብ ትምህርት መነሻው መጽሐፈ ሄኖክ እንደኾነ ከላይ የተጠቀሱት ሊቃውንት ሥለ ኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ካቀረቡት ምንጭ ልዩ መኾኑን ማሳየት ነው፡፡ እንዲኹም ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው የትምህርት ዘይቤ የነበረውን አጠናን (የዘመን አቈጣጠር ጥናት) እና የማኅበረሰቡን ከፍተኛ የፍልስፍና ጥበብ የሚጠቁም ሲኾን ለማኅበራዊ መስተጋብር ያለው ፋይዳ የጎላ እንደኾነ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ለሳይንሳዊ ጥናቶች የሕዋ ወይም ሥነ-ፈለክ (cosmos) እና የአየር ንብረት ምርምር ዓላማ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት አስፈላጊ መኾኑን ነው፡፡

## የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዓላማ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንጩ መጽሐፈ ሄኖክ መሆኑን ፤ ለዘመን አቈጣጠር፣ ለከዋክብት እና ለአየር ትንበያ ጥናት ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንጭ መጽሐፈ ሄኖክ መሆኑን ማስተዋወቅ፣
- ባሕረ ሐሳብ ስለከዋክብት እና የነፋሳት ዑደት ለማወቅ የሚያስችል መሆኑን መፈተሽ፣

123 ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም. ባሕረ-ሐሳብ የቀመር የሥነ-ፈለክ ምስጢር፡፡

- ጥንታዊ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ምንጩ ባሕረ ሐሳብ መሆኑን በማሳየት ልዩ ልዩ ጠባይዓትን መግለፅ፣

# የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚኽ ጥናት አስፈላጊነት የኢትዮጵያ ዘመን አቀጣጠር መነሻው አቡሻኽር ሳይኾን መጽሐፈ ሄኖክ እንደኾነ መነሻ ሐሳብ ማቅረብ ነው፡፡ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ከመጽሐፈ ሄኖክ አንጻር የሚዳሳስ እና ትምህርቱ ዘመን ከመቍጠር ባሻገር ጥልቅ የኾነ ሒሳባዊ (mathematics) ቀመሮችና የአሠራር ስልቶችን (Algorithms) በቃል የማጥናት[124] ክሂልን ማዳበር የሚያስችል መኾኑን ማሳየት እና የሥነ-ክዋክብት እና የአየር ትንበያ ትምህርት የያዘ መኾኑን ይዳስሳል፡፡

# የጥናቱ ዘዴ

ይኽን ጽሑፍ ለማዘጋጀት አጥኚው አንደኛ እና ኹለተኛ የመረጃ ምንጮችን የተጠቀመ ሲኾን፣ ከሚመለከታቸውን የባሕረ ሐሳብ መምህራን በቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ እንዲኹም የሰነድ ፍተሻ እና ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሒሳብ (Mathematics) ቀመሮች ለትንተና አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

# ባሕረ ሐሳብ እና ታሪካዊ ዳራው

ባሕረ ሐሳብ ማለት የቃሉ ትርጉም ቍጥር ያለው ዘመን፣ የዘመን ቍጥር ማለት ነው፡፡[125] ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው የቍጥር ትምህርት ነው፡፡ ይኽ ትምህርት የፀሐይን፣ የጨረቃን፣ የክዋከብትንና የነፋሳትን ዑደታቸውንና የቈይታ ጊዜያቸውን ርዝማኔ ለይቶ ይቆጥራል፡፡ በእነዚኽ ዑደቶች አማካኝነት ዘመናትን ለመቍጠር፣ አንዳንድ ያለፉ እና ወደፊት የሚመጡ ክስተቶችን ጊዜያቸውን ለማስላት ያገለግላል፡፡

ባሕረ ሐሳብ ያለፈውን፣ አኹን ያለውንና ወደፊት የሚኾነውን እየቈጠረ በስፍር(በልክ) የሚያስረዳ ነው፡፡ ለመጠሪያም የሚጠቀምባቸው በዋናነት የፀሐይን፣ የጨረቃንና የከዋክብትን ዑደታትን ሲኾን እነዚኽን ተጠቅሞ ዘመንን በዓመት፣

[124] በቃል ማጥናት ስንል፡- ጽሑፋዊ ማጣቀሻ ሳይመለከቱ በአእምሮ ክህሎት ብቻ ላይ ተመሥርቶ በቃል የሚደረግ ገለጻና እና ትንታኔ ማለት ነው፡፡

[125] አለቃ ያሬድ ፈንታ፡ 2004 ዓ.ም ባሕረ-ሐሳብ የቀመር የሥነ-ፈለክ ምስጢር፡፡

በወር፣ በቀን፣ በሰዓት፣ ወዘተ. በመከፋፈል ይሰፍራል። ለዚኽም በተለያየ ጊዜ የሚመላለሱ ዐውዶች ዘመንን ለመለየት (ለመቍጠር) ይጠቅማሉ።

የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መነሻው ዘመነ ፍጥረት ነው። ዘመን ራሱ የተፈጠረው ለፍጡር ነው። ባሕረ ሐሳብ ዘመንን ለመቍጠር መነሻ የሚያደርገው እግዚአብሔር ፍጥረትን መፍጠር የጀመረበትን ዕለት ዕለተ እሑድን አንድ ብሎ ይጀምራል። ይኽም በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ላይ የተመዘገበውን ታሪክ የተከተለ ሲኾን በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር ፍጥረታትን በስድስት ቀን እንደፈጠረ በሰባተኛው ቀን ደግሞ እንደዐረፈ ይናገራል።[126] ስለዚኽ በክርስቲያኑ ዓለም ያሉ መምህራን የአንድ ሳምንት የቀን ብዛት ሰባት እንዲኾን የተደረገበት ዋና ምክንያት ይኽ እንደኾነ ያብራራሉ።

መጽሐፈ ሄኖክ የአዳም ሰባተኛ ልጅ የኾነው እና ከቀደምት አበው አንዱ እንደነበረ የሚታወቀው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደው እና ሞትን እንዳያይ እግዚአብሔር የሰወረው[127] ሄኖክ የተባለ ደግ ሰው የጻፈው ነው[128]።

መጽሐፈ ሄኖክን ስንመለከተው የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር እንዲኹም የባሕረ ሐሳብ ፍልስፍናውና መሠረቱ ከሄኖክ መጽሐፍ የተቀዳ መኾኑን መረዳት ይቻላል። ምክንያቱም ባሕረ ሐሳብ የሚያስተምረው ከዚኹ መጽሐፍ ትርጓሜ መነሻነት የተዘጋጀ መኾኑን የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች አሉት። እንዲኹም የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ማጣቀሻ አድርገው በዋናነት የሚጠቀሙት መጽሐፈ ሄኖክን ነው። ይኽንን በጣራ ቅዱስ ኤውስጣጢዎስ ገዳም አገልጋይ የኾኑት አባ ኀይለማርያም የሚባሉ የአቡሻኽር መምህር እና የገዳሙ አበ ምኔት፤ በቃለ መጠይቅ በሚከተለው መልክ አስረድተዋል

‹‹ብዙ ሰዎች የባሕረ ሐሳብ ደራሲ የሚመስሏቸው አቡሻኽር[129] እና ቅዱስ ዲሜጥሮስ እንኳን የተጠቀሙት የሄኖክን ሥራ ነው። በእርግጥ አቡሻኽርና ቅዱስ ዲሜጥሮስ ለባሕረ ሐሳብ ትምህርት መስፋፋት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል››።[130]

---

[126] ኦሪት ዘፍጥረት 2፥2
[127] ኦሪት ዘፍጥረት 5፥24
[128] ዓለም ከተፈጠረ በ1486 ዘመን እንደተጻፈ መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ ፤ ገፅ 9 ይገልጻል። ይሁ ቍ.14-15
[129] ENCYCLOPAEDIA Aethiopica, volume 1, page 56
[130] ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም. ፣ገጽ 20

ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዲሜጥሮስ በ3ኛው መ/ክ/ዘ የነበረ የእስክንድርያ መንበር ሊቀ ጳጳሳት ሲኾን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በየዓመቱ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ዕለት[131]፣ እንዲኹም እነዚኹ ዕለታት በየጊዜው በምን ዓይነት መንገድ እንደሚገኙ የቀመሩን ሥርዓትም አዘጋጅቷል፡፡ ቅዱስ ዲሜጥሮስ በዓላትንና አጽዋማትን ሲያወጣ በጸሎትና በሱባኤ ተወስኖ እንደኾነ ይታመናል፡፡[132] እንዲኹም አቡሻኽር ደግሞ በ12ኛው/13ኛው መ/ክ/ዘ የነበረ የእስክድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ነው፡፡[133] አቡሻኽር ለትምህርቱ መዳበር ላደረገው አስተዋጽኦ ከባሕረ ሐሳብ ትምህርት ክፍሎች መካከል የአንዱን መጠሪያ በስሙ አቡሻኽር ብለው ሰይመውታል፡፡[134] አንዳንድ ጊዜ ባሕረ ሐሳብ የሚለውን አቡሻኽር በማለት የሚጠሩም አሉ፡፡ ስለዚኽ ቅዱስ ዲሜጥሮስና አቡሻኽር የነበረውን ዘመን መቍጠሪያ ተጠቅመው አበለጸጉት ወይም ለአገልግሎት እንዲመች አድርገው አስተካከሉት እንጂ አዲስ ትምህርት አላዘጋጁም፡፡ ይኽም ደግሞ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት መነሻ መጽሐፈ ሄኖክ እንደ ኾነ እንረዳለን፡፡

በዋናነት የሚጠቀሱ የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ፣ ኤጲፋኖስ፣ አቡሻኽር፣ ቅዱስ ዲሜጥሮስ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ ወዘተ. ዘመን ለመቍጠር አጠቃላይ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለውን የክርስቶስን ልደት መነሻ አድርገው ለኹለት ይከፍሉታል፡፡ መጀመሪያው ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ዘመን ዓመተ ፍዳ (የኵነኔ ዘመን) በማለት ይጠሩታል፡፡ የዘመኑ ርዝማኔ (ብዛት) 5500 ዓመት ያህል ነው፡፡[135] ኹለተኛውና ከጌታ ልደት በኋላ ያለው ደግሞ ዓመተ ምሕረት ብለው ይጠሩታል፡፡[136] ለምሳሌ፡ አኹን ያለንበት ዓመት ጌታችን ከተወለደ 2012 ዓመት ኾኖታል፡፡ ዓለም ከተፈጠረ ደግሞ 7512 ዓመት ኾኗል ማለት ነው፡፡ ይኽ ቁጥር የተለያዩ ዑደታዊ ስሌቶችን ለማውጣት በየፈርጁ ጥቅም ላይ እንደሚውል ወደፊት እንመለከታለን፡፡

---

131 የኔታ አባ ኃ/ማርያም በደቡብ ጉንደር ሀገረ ስብከት የሚገኘው የጣራ ቅዱስ ኤውስጣጢዎስ ገዳም አበ እምኔት እና ለደቀመዛሙርታቸው በነሐሴ ወር ፤ 2008 ዓ.ም. ጥናቱን ለማጥናት የተደረገ የድምጽ ወምስል ቃለ መጠይቅ

132 መ/ር አባ ገ/ሥላሴ ወ/ሚካኤል፡ 2005 ዓ.ም፣ ገጽ 9

133 ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም. ፣ ገጽ 20

134 ዝኒ ከማሁ

135 መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ዋቢ አድረገው "በሐምስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድሕከ ውስተ መርሕብከ ወእከውን ሕፃነ በእንቲኣከ በመስቀልየ ወበሞትየ" ይላሉ፡፡ መሪጌታ ዘነበ ሐየሎም፡ 2009 ዓ.ም. ኹሉም የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የሚጠቀሙት መነሻ ቍጥር ነው፡፡

136 አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም

# የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ለዘመን አቈጣጠር፣ ለከዋክብት እና ለአየር ትንበያ

## የተለያዩ ክስተቶች ዑደት ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር ያለው ግንኙነት

ዋናው ለዘመን አቈጣጠር አጀማመር ምክንያት የኾነው የሰው ልጆች ከታሪክና ከተፈጥሮ ክስተቶች ጋር ትስስር ያለውን በሕይወታቸው ትናንትና ወይም ዛሬ የተከናወኑ እንዲኹም ለነገ ተግባር አስቀድሞ ለመዘጋጀት ይቻል ዘንድ ታስቦ የተቀመረ ስሌት ነው።

ዘመን መጀመሪያም ኾነ መጨረሻ ባይኖረውም[137] በዓለማችን ውስጥ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተመልሰው የሚመጡና የተወሰነ ጊዜ ቆይተው የሚኼዱ ነገሮች ወይም የተፈጥሮ ክስተቶች[138] አሉ። ዘመንን መለካት ወይም መቊጠር ያስፈለገበት ዋናው ምክንያትም የተፈጥሮ ክስተቶች መመላለስ ነው። እነዚኽ የተፈጥሮ ክስተቶች ምልልሳቸው ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ ስለኾነ ተመልሰው የሚመጡበትን ጊዜ ማወቅና ሲመጡ እየጠበቁ መታዘዝ ወይም ከተቻለ ከተጽዕኖዎቻቸው ለማምለጥ ዘዴ መፈለግ የግድ ይኾናል።[139] የሰው ልጅ ሕይወቱን የሚመራው በአብዛኛው እነዚሁ የተፈጥሮ ክስተቶች በሚያዝዙት መሠረት ነው ፤ ከተፈጥሮ ተፅዕኖ ውጭ የኾነ ሙሉ ነፃነት የለንም።[140] እነዚኽ በዓለማችን ውስጥ ያሉት ተመላላሽ ክስተቶች በሰው ሕይወት ውስጥ የራሳቸውን ተፅዕኖ ስለሚያሳድሩ፤ ሰው በሰላምና በጤና ለመኖር ተመላላሽ ክስተቶችን ለይቶ ማወቅ አለበት። የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የዘመን መለዋወጥ ከከዋክብት፣ ከጨረቃና ከፀሐይ ዑደት ጋር የተያያዘ መኾኑን ይናገራሉ።[141] ስለዚኽ የዘመን መለዋወጥ በእነዚኽ ፍጥረታት ተፅዕኖ ውስጥ

[137] ኹለት ዓይነት ጊዜ አለ። "መጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድር ፈጠረ።" ዘፍ 1፥1 ይላል በዚኽ አገላለጽ "መጀመሪያ" የሚለው ቃል የሚታወቅና የማይታወቅ ነው። የሚታወቀው በእግዚአብሔር ነው። ለሰዎች ወይም ለፍጥረታት ደግሞ የፈጣሪ ጊዜ መጀመሪያውና መጨረሻው አይታወቅም።

[138] የተፈጥሮ ክስተት የሚባሉ እንደ ድርቅ፣ አውሎ ነፋስ፣ ከመጠን በላይ በኾነ ዝናብ የሚከሰቱ ክስተቶች ወዘተ. ለማለት ነው።በጌታቸው ኃይሌ አገለላለጽ ግን ክረምትና በጋ፤ ቀንና ሌሊት ፤ ወዘተ. እንደ ክስተት ተገልጸዋል።

[139] ጌታቸው ኃይሌ ፣ 1993 ዓ.ም።

[140] ዝኒ ከማሁ

[141] ዝኒ ከማሁ

ከወደቀው የሰው ልጅ ሕይወት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሰው በዘመን ውስጥ የሚያልፍ (ከዘመን ውጭ መኾን የማይችል) ስለኾነ ነው፡፡

# አዕዋዳት

ተመላላሽ ክስተቶች (የተፈጥሮ ምልክቶች) ተመላልሰው ለመከሰት የሚወስድባቸው ዘመን ወይም ጊዜ ዐውድ ይባላል፡፡ ዑደት ማለት ዙሪያ ማለት ሲኾን ዐውዶች (በግዕዙ አዕዋድ) ይመላለሳሉ፤ ዞረው ይገጥማሉ ማለት ነው፡፡[142]




ዘመን የሚቆጠረው በክስተቶች ዑደት ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡ በመጽሐፈ ሄኖክ መሠረት ሦስቱ አዕዋዳት ማለትም ዐውደ ዕለት፣ ዐውደ ወርኅና ዐውደ ዓመት በተጨማሪም ዐውደ ጳጉሜን በግልጽ በስም ተጠቅሰው የተጻፉ መሠረታዊ አዕዋዳት ናቸው፡፡ የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት በእነዚኽ መሠረታውያን አዕዋዳት ተነሥተው ሌሎችን የተለያዩ የተፈጥሮ ክስተቶችን የሚያመለክቱ አዕዋዳትን አዘጋጅተዋል፡፡ አዕዋዳትም፡-

## ሀ. ዐውደ ዕለት

በቀንና በማታ የሚከፈልና በየ24 ሰዓታት የሚመላለስ ዐውድ ነው፡፡ የአንዱ ዕለት ርዝማኔ በሰዓት ይለካል፡፡ በአኹኑ ጊዜ የአንድ ዕለት ርዝማኔ 24 ሰዓታት እንደኾነ

142 ዝኒ ከማሁ

በኹሉም የዘርፉ ሊቃውንት ዘንድ ስምምነት አለ፡፡ መጽሐፈ ሄኖክ ግን አንድ ዕለት 18 ክፍሎች እንዳሉት ይናገራል፡፡[143]

በመጸሐፈ ሄኖክ አገላለጽ መሠረት የአንድ ቀን ርዝማኔ 18 ክፍል ነው፡፡ አኹን በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት የአንድ ዕለት ርዝማኔ 24 ሰዓታት ወይም 1440 ደቂቃ ነው፡፡ ይኽን ዓለም የተስማማበት የአንድ ዕለት ደቂቃ በሄኖክ አቈጣጥር ብንቀይረው በአንድ ሰዓት (ክፍለ ዕለት) 80 ደቂቃ ነበር ማለት ነው፡፡

## ለ. ዐውደ ወርኅ

ጨረቃ በግዕዙ ወርኅ ሲኾን በአማርኛው አጠራር አጥሮ ወር እንደተባለ ጌታቸው ኃይሌ ያስረዳሉ ዐውደ ወርኅ በርዝማኔው ከዕለት ቀጥሎ ሲመላለስ በትክክል የሚታይ የተፈጥሮ ክስተት የጨረቃ ዑደት ነው፡ ጨረቃ በ29 ወይም በ30 ቀናት ውስጥ ወደነበረችበት ትመለሳለች፡፡ ስለዚኽ ዐውደ ወርኅ በየ30 ዕለታት የሚመላለስ ዑደት ነው ማለት ነው፡፡

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 22 አገላለጽ ጨረቃ የ29 እና የ30 ዕለት ርዝማኔ እያፈራረቀች እንደምትታይ እንዲኹም ሙሉ ብርሃን የምትሰጠው በወሩ አጋማሽ ማለትም 14/15ኛው ቀን እንደኾነ ያስገነዝባል፡፡

## ሐ. ዐውደ ዓመት

የቀንና የሌሊቱ ርዝማኔ፣ የዝናብና የፀሐይ ወቅቶች መፈራረቅ፣ በአጠቃላይ በየወራቱ የሚለያዩ ነገሮች ተመልሰው እንደገና የሚመጡበት ዑደት ዐውደ ዓመት ተብሎ ይጠራል፡፡ በመኾኑም የአንድ ዐውደ ዓመት ርዝመት በፀሐይ 365 ዕለት በጨረቃ ደግሞ 354 ዕለት እንደየአቈጣጠሩም የፀሐይ ዓመት ወይም የጨረቃ ዓመት እየተባለ ይጠራል፡፡

## መ. ዐውደ ጳጉሜን (ወንጌላዊ)

የአንድ ዐውደ ጳጉሜን ርዝማኔ አራት ዓመታት ነው፡፡ ይኽም በግዕዙ ሠግር (leap year) ይባላል፡፡ በተጨማሪም በፀሐይ አቈጣጠር በእየዓመቱ የሚተርፉ(የማይቆጠሩ) ስድስት ካልዒቶች በ600 ዓመት ተሰብስበው ጳጉሜን ሰባት ቀናት ትኾናለች፡፡[144]

143 መጽሐፈ ሄኖክ ፤ ምዕራፍ 21

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 28 አገላለጽ ጳጉሜን ለብቻ መቈጥር እንዳለባት ማስጠንቀቂያ አዘል መልእክት "ጳጉሜን ከዋክብት የለም ብለው ይበድላሉ" ይላል። በእዚኽ ምዕራፍ የጳጉሜን ዕለት ብዛት አራት ነው ይላል ምክንያቱን በምዕራፍ 21 ላይ የዓመት ዕለታት ብዛት 364 ስላለ እንደኾነ መረዳት ያስፈልጋል። የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ሽርፍራፊ ጊዜያትን በመሰብሰብ የጳጉሜን ወር ስድስት እንዲኹም በዘመናት ኺደት ሰባት የሚያደርጉበትን ስሌት በተገቢው ኹኔታ መረዳት ያስፈልጋል።

## ሠ. ዐውደ አበቅቴ

አበቅቴ የግሪክ ቃል ሲኾን በእንግሊዝኛው ኤፓክት (epact) እየተባለ ይጠራል።[145] ዐውደ አበቅቴ በየ19 ዓመታት የሚደጋገም ዑደት ነው። አበቅቴ መስከረም አንድ ቀን ዐውደ ዓመት ሲጀመር የጨረቃ ዓመታዊ ዕድሜ ማለት ነው።[146] ይኽ በየ19 ዓመቱ አንድ ጊዜ የሚደረገው የፀሐይና የጨረቃ ‹‹ተራክቦ›› /መገናኛ ፣አብረው ጉዞአቸውን የሚጀምሩበት/ ዐውደ አበቅቴ ይባላል። ይኽ ዐውድ በአንድ ዓመት መቍጠሪያ በኾኑት በፀሐይና በጨረቃ የዓመት ጉዞ ልዩነት መሠረት የተዘጋጀ ነው። ይኽም ማለት ሄኖክ አንድ ዓመት 364 ቀን (ሊቃውንቱ ከላይ እንዳየነው አንዷን ዕለት ጨምረው 365 ቀን  እና በጨረቃ 354 ቀን መካከል የሚፈጠር የ11 ዕለት ልዩነት የሚፈጠር ዐውድ ነው። በዚኽ መሠረት በ19 ዓመታቸው ፀሐይና በጨረቃ በአንድ ላይ ጉዞ የሚጀምሩበት ማለት ነው።

## ረ. ዐውደ ማኀተም

የዐውደ ማኀተም ርዝማኔ 76 ዓመታት ነው። የ19 እና የ4 ትንሹ የጋራ ብዜታቸው (4 x 19) 76 ስለኾነ ዐውደ አበቅቴና ዐውደ ጳጉሜን ዑደታቸውን በአንድ ቀን እኩል የሚጀምሩት በየ76 ዓመቱ ነው። የመጨረሻው ወንጌላዊ (ዮሐንስ) እና 18 አበቅቴ ይገናኙበታል።[147] ይኽ ዐውድ በ19 ዓመታት የሚፈጠሩ የፀሐይና የጨረቃ ልዩነቶች እና በአራት ዓመት አንድ ጊዜ የሚመጡ ክስተቶች የሚገናኙበት ነው።

---

144 ዝኒ ከማሁ

145 ዝኒ ከማሁ

146 ዝኒ ከማሁ

147 *አለቃ ያሬድ ፈንታ*፤ 2004 ዓ.ም.

## ሰ. ዐውደ ፀሐይ

የዐውደ ፀሐይ ርዝማኔ 28 ዓመታት ነው። የዐውደ ዕለት እና ዐውደ ጳጉሜን ዑደቶች የሚገናኙበት ዐውድ ነው። የ7 እና የ4 ትንሹ የጋራ ብዜታቸው (4 x 7) 28 ስለኾነ የዐውደ ፀሐይ ርዝማኔ 28ኛ ዓመታት ነው። ለዚኽ ዐውድ መነሻ ፀሐይና ጨረቃ የተፈጠሩት ረቡዕ ስለኾነ፤ ይኽ ዕለት (ዕለተ ረቡዕ) ጥንተ ዮን (ኦን) ይባላል። ይኽ ዐውድ ኹለቱን መሠረታዊ አዕዋዳት ማለትም ዐውደ ዕለትና ዐውደ ጳጉሜን የሚያገናኝ ነው።

## ሸ. ዐውደ ቀመር

ይኽ ዐውድ በሊቃውንቱ ዐቢይ ቀመር እየተባለ የሚጠራ ሲኾን በ532 ዓመት አንድ ጊዜ የሚፈጸም ዐውድ ነው።[148] ዐውደ ዕለት (በየ7 ዕለቱ የሚመላለስ)፣ ዐውደ ጳጉሜን (በየ4 ዓመታቱ የሚመላለስ) እና ዐውደ አበቅቴ (በየ19 ዓመታቱ የሚመላለስ) ዞረው የሚገናኙበት በየ532 ዓመታት አንድ ጊዜ ነው። ይኽ ዑደት ዐውደ ቀመር ይባላል። በዚኽ ዐውድ በሄኖክ የተጠቀሱት አዕዋዳት ኹሉ የሚፈጸሙበት ነው።

ከዚኽ በተጨማሪ ቀመረ ዐረብ የሚባልና ርዝመቱም 228 ዓመታት የኾነ ዑደት አለ። ይኽም የጨረቃ ዓመተ ዓለም የሚታወቅበት ስሌት ነው።[149]

# ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያ የነበረው አገልግሎት

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት በሀገራችን በተለይ ለሦስት ዐበይት ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሲውል እንደነበር እንገነዘባለን። ይኸውም ለመንፈሳዊ አገልግሎት፤ የተለያዩ ጉዳዮችን ክስተት ለመተንበይ እና የታሪክ መዛግብትን ለማረጋገጥ ነው።

### *ሀ. ለመንፈሳዊ አገልግሎት*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ መስከረም አንድ ቀን የዓመቱ ተንቀሳቃሽ በዓላት እንደ ትንሣኤ፣ ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ስቅለት፣ ዕርገትና ጰራቅሊጦስ የመሳሰሉት ቀናት፣ እንዲኹም የመነሻ ቀናቸው ተወስኖ የማይታወቁ አጽዋማት እንደ ዐቢይ ጾም፣ ጾመ ሐዋርያትና ጾመ ድኅነት የመሳሰሉት

[148] ዝኒ ከማሁ
[149] አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም

ቀላል በኾነ መንገድ በማውጣት እና በዚኹ አያይዛ የማይንቀሳቀሱ ወይም ዓመቱ ቢቀያየርም ቋሚ የኾኑትን በዓላትና አጽዋማት ለይታ ለምእመኗ ታሳውቃለች፡፡

የሚዘዋወሩ በዓላትና አጽዋማት የሚገኙት (በዓላቱ የሚውሉበትን ፤ አጽዋማቱ የሚገቡበት ቀን የሚታወቀው) አራት ነገሮች በመደመር ነው፡፡ እነርሱም (1) መጥቅዕ ፣ (2) መጥቅዕ የሚውልበት ዕለት ተውሳክ ፣ (3) የበዓላትና የአጽዋማት ተውሳክ እና (4) የነነዌ መባጃ ሐመር (የነነዌ ጾም የሚገባበት ወርኃዊ ቀን) ናቸው፡፡ [150] በየቀኑ የአሥርቆቱን ሥርዓት ታደርሳለች፡፡ አሥርቆት ማለት የሌሊት መባቻ በጨረቃ ፤ የመዓልቱን መባቻ በፀሐይ ቆጥሮ መናገር ነው፡፡[151] ሌሊቱን ለማውጣት አበቅቴና ዕለቱን (በፀሐይ) ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በመኾኑም የሚከተለው ቀመር የእያንዳንዱን ዕለት ሌሊት ለማግኘት ያገለግላል፡፡

ሌሊት = አበቅቴ + ዕለት + የወሩ ሕፀፅ

ለምሳሌ፦ የ2012 ዓ.ም. የመስከረም 1 (አንድ) ቀንን የአሥርቆት ሥርዓት እንመልከት፡፡

ዓመቱ፡ በፀሐይ 2012 ዓመት፤ በጨረቃ 2070 ዓመት ከ11 ወር፤ ከ 16 ቀን ነው፡፡

- የሌሊት መባቻ በ 24 ፣ የጨረቃ መባቻ በ 28 ፣ እንዲኹም የመዓልቱ መባቻ በ 1 እንደሚኾን በማስላት እና ቀኖቹን እንዲኽ ለይቶ በማውጣት ለእየራሱ ጸሎት ይደርሳል፡፡

## ለ. ለትንበያ አገልግሎት

የዘመን መለዋወጥ የፀሐይ፣ የጨረቃ፣ የከዋክብትን ዑደት እና የነፋሳትን ኹኔታ ተከትለው የሚመጡ የወቅቶች መለዋወጥ እንዲኹም እነዚኽን ምክንያት በማድረግ የሚመጡ የተለያዩ ክስተቶችን በማየት የሰዎች የኑሮ ኹኔታ ላይ ወደፊት ሊኾኑ የሚችሉ ነገሮችን ለመተንበይ የባሕረ ሐሳብን ዘዴዎች ይጠቀሙበት ነበር፡፡ እንዲኹም አንዳንድ ሊቃውንት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም የሚመጣበት ቀን መቼ ሊኾን እንደሚችል የነቢያትን ትንቢት መነሻ በማድረግ ይተነብያሉ፡፡ በዚኽ ትንቢት መሠረት ጌታችን 8000 ዓመት ሳይሞላ ወይም ትንሽ ሲያጎድል

[150] መርሐ ዕውር

[151] አለቃ ያሬድ ፈንታ ፤ 2004 ዓ.ም

እንደሚመጣ የሚናገሩ አሉ፡፡[152] በዚኽም የተነሣ ይመስላል ብዙ የባሕረ ሐሳብ መምህራን 7980 ዓመት ላይ ሲደርሱ ዘመኑን መቍጠር ያቆማሉ፡፡

### *ሐ. የታሪክ ክስተቶችን፣ መዛግብትን ትክክለኛነት ለማወቅ እና ለማረጋገጥ*

የኢትዮጵያ ሊቃውንት በባሕረ ሐሳብ ትምህርትና የአቈጣጠር ስሌታቸው በመታገዝ የታሪክ ድርሳናትን ማረጋገጥ እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡

ለምሳሌ፦ ክርስቶስ የተወለደው ታኅሣሥ 29 ቀን ፣ ማክሰኞ ዕለት መኾኑን እንዲኽ ያረጋግጣሉ ፡ ይኽንን ለማስላት ፀሐይና ጨረቃ ዑደታቸውን በእኩል ጊዜ ከጀመሩ ምን ያኽል ዓመት እንደኾናቸው መቍጠሪያ የኾነውን አበቅቴ የሚባለውን ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚኽም የፀሐይን አበቅቴ ለማወቅ ሲፈልጉ ዘመኑን በዓመተ ዓለም (5500 + ከክርስቶስ ልደት ወዲኽ ያለውን ዓመት) ይወስዱና ያለንበት ዘመን ገና ስላላለቀ አንድ ቍጥር ያነሡለታል (አንድ ለዘመን ተው የሚለውን ዐዋጅ በማስታዉስ)[153]፡፡ [154]የተረፈውን ከአራት ቦታ ከፍለው አንዱን ክፍል (ሩቡን) በዋናው ላይ ይደምሩበታል፡፡ ሩቡን ለማውጣት ከአራት ቦታ ሲከፈል የአራቱ ግማሽ ኹለት ወይም አራት ሩብ ከተረፈ አብረው ይደምሩታል፤ ያለዚያ ደግሞ ይጥሉታል፡፡ ጠቅላላውን ድምር በሰባት ገድፈው (ለሰባት አካፍለው)፤ የሚተርፈውን የዚያ ዓመት የፀሐይ አበቅቴ እንደሚኾን ደንግገው አስቀምጠዋል፡፡ የፀሐይ አበቅቴ የሳምንቱን ዕለት ማወቂያ ነው፡፡ ስለዚኽ ይኽን አሠራር ተከትለው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ማክሰኞ ዕለት እንደዋለ አረጋግጠዋል፡፡

## የዘመን አቆጣጠር

የተለያዩ ዐውዶችን በመጠቀም አጽዋማትና በዓላትን ለማውጣት፣ ዘመኑ በፀሐይና በጨረቃ ለየብቻ ስንት እንደኾነ አስልቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የቍጥር ስሌቱን ለማስተማር ብዙ ዓመታትን በዐውድ ማካፈል ስለሚያስፈልግ መጀመሪያ ከመጀመሪያው ዐውድ ይነሡና ዐውዱ በጨመረ ቍጥር ከእያንዳንዱ ዐውድ

[152] መጽሐፈ ዞሲማስ፣ ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም.፣መርጌታ ዘነበ ሐየሎም፤
[153] ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም.
[154] ለዘመን አንድ ተው የሚልበት ምክንያት ስለተጀመረ ይቈጠራል ስላልተፈጸመ ይቀነሳል፤ በዚኽ ምሳሌ ለማስረዳት የ5500 ዓመትን ታህሣሥ 29 ለማወቅ አንድ ይቀነሳል፤ ምክያቱም ለመደመር ገና ወደፊት ያሉ 8 ወራቶች አሉ የማታወቁ፤ እንዲኹም ለመቀነስ አራት ወሮች አልፈዋል ስለዚኽ ለመቍጠርም ለመተውም ስለሚያስቸግር መቀነሱ የተሻለ ነው፡፡ በሒሳብ(mathematics) ትምህርት ሙሉ ቍጥር የሚጀምርው ከዜሮ ነው፡፡ በባሕረ ሐሳብ መምህራንም ዘንድ ሙሉ ቍጥር ለመጀምር ይመስላል አንድ በመቀነስ ይጥራሉ፡፡

የሚተርፈውን ቍጥር ልዩነቱን በመያዝ ቀሪውን ብቻ በመቍጠር ምን ያኽል እንደኾነ በቃላቸው ያሰላሉ። ዘዴው[155] አንድ የተሰጠ ቍጥርን በቀሪ ማካፈል (modular arithmetic and algebra) ሲኾን ቀሪ (remainder) ለባሕረ ሐሳብ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሄኖክ በዋናነት ተካፋይ ቍጥሮችን የሚጠቀም ሲኾን በቀሪ የሚካፈሉትን የመጽሐፈ ሄኖክ የተረጎሙ ሊቃውንት አካተውታል። ለምሳሌ አንድ ዓመት 364 ቀን ነው የሚለው ሲያብራሩ 5ኛይቱን ቀን ከሱባኤ አትገባም ብሎ ተዋት ይላል።[156]

ዘመንን ለመቍጠር በሄኖክ አገላለጽ የሰማይ ምሥጢር ብሎ በምዕራፍ 21 እስከ 28 የገለጻቸውን በዋናነት የፀሐይንና የጨረቃን ዑደት ማወቅ ያስፈልጋል። ይኽም የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጥር መነሻው የሮም ከተማ መቆርቆርን መሠረት ካደረገው ከጎርጎርዮሳውያን አቈጣጠር ልዩ እንዲኾን ያደርገዋል።[157] ኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ከምዕራባያውን እንዲለይ የሚያደርገው መነሻው የሥነ መለኮት ትምህርት መኾኑ እና ማገናዘቢያውም (ማመሳከሪያውም) ሥነ ፍጥረት መኾኑ ነው።[158]

## ዑደተ ፀሐይ

የአንድ ዓመት ርዝመት በፀሐይ 365 ዕለት ከ15 ኬክሮስ ከ6 ካልዒት ነው። የብርሃን መጠኗ ከጨረቃና ከከዋክብት ይበልጣል። የባሕረ ሐሳብ መምህራን ፀሐይ የተፈጠረችው እሑድ ከተፈጠረው ብርሃን ነው ይላሉ።[159]

የፀሐይ የጉዞ መስመር ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ሲኾን በምሥራቅ ስድስት መስኮቶች (መውጫ) ፤ በምዕራብም እንዲኹ ስድስት መስኮቶች (መግቢያ) አሏት። ፀሐይ በምዕራብ ከገባች በኋላ በበነጋው በሰሜን በኩል ዞራ በምሥራቅ ትወጣለች። ስለዚኽ ዑደቷ የሰዓት ተቃራኒ (counter clockwise) ነው ማለት ነው።

ይኽም ማለት ፀሐይ ከሰሜን ወደ ደቡብ ወይም ከስድስተኛው ደጃፍ ወደ አንደኛው ደጃፍ ስትመለስ ቀኑ ያጥራል። ምክንያቱም ፀሐይ ወደ ሰሜን ስትዞር ከምድር ዋልታ በአጭር ርቀት ስለምትገኝ የወሩ ርዝማኔ በሽርፍራፊ ሰዓት ያንሳል። የእየወሩ

155 ባሕረ ሐሳብ ትምህርት የሚሰጥበት የተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ በቃል ወይም በንባብ የሚሰጥ ሲኾን በዚኽ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች እየጻፉ ሳይኾን በመስማት ብቻ የሚከናወን ነው።

156 የመጽሐፈ ሄኖክ አድምታ፤ ምዕራፍ 21 ፤ በዚኽ አገላለጽ ሱባኤ ማለት ሰባት ለማለት ወይም በሰባት ስለማይካፈል።

157 ኅሩይ ሰሜ፡ ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፡ 2000 ዓ.ም. ገጽ 77

158 ዝኒ ከማሁ

159 መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘረቡዕ፣

የዕለት ሰዓትም በፀሐይ አቀማመጥ ምክንያት አንዱ ዕለት ከሌላው ዕለት እንዲበላለጥ ያደርገዋል።[160] እንዲኹም ፀሐይ ከደቡብ ወደ ሰሜን ወይም ከአንደኛው ደጃፍ ወደ ስድስተኛው ደጃፍ ስትሄድ ቀኑ ይረዝማል።

በሄኖክ የአንድ ዕለት ርዝማኔ 18 ክፍል እንደኾነ ከላይ ተገልጿል። ስለዚኽ የመዓልትና የሌሊት ሰዓት ወይም ክፍል በየወሩ ከሚወጡ ከዋክብት አንጻር ያላቸውን ንፅፅር በሚቀጥለው ሠንጠረዥ መመልከት እንችላለን።

ሠንጠረዥ 1፡ በየወሩ ከሚወጡ ከዋክብት አንጻር ያላቸውን ግንኙነት ከመዓልት አንጻር

| ተ.ቁ. | ወር | አንድ ዕለት 24 ሰዓት በማድረግና አሁን በዓለም አቀፍ አገልግሎት ላይ ያለው | | በሄኖክ አገላለጽ መሠረት አንድ ዕለት 18 ክፍል በማድረግ | | የወሩ ኮከብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመዓልቱ ሰዓት | የሌሊቱ ሰዓት | የመዓልቱ ክፍል | የሌሊቱ ክፍል | |
| 1 | *መስከረም* | *12* | *12* | *9* | *9* | *ሰንቡላ* |
| 2 | ጥቅምት | 11 | 13 | 8 | 10 | ሚዛን |
| 3 | ኅዳር | 10 | 14 | 7 | 11 | አቅራብ |
| 4 | *ታኅሣሥ* | 9 | 15 | 6 | 12 | ቀውስ |
| 5 | ጥር | 10 | 14 | 7 | 11 | ጀደይ |
| 6 | የካቲት | 11 | 13 | 8 | 10 | ደለው |
| 7 | *መጋቢት* | *12* | *12* | *9* | *9* | *ሑት* |
| 8 | **ሚያዚያ** | **13** | **11** | **10** | **8** | **ሐመል** |
| 9 | ግንቦት | 14 | 10 | 11 | 7 | ተውር |
| 10 | ሠኔ | 15 | 9 | 12 | 6 | ጀውዛ |
| 11 | ሐምሌ | 14 | 10 | 11 | 7 | ሸርጣን |
| 12 | ነሐሴ | 13 | 11 | 10 | 8 | አሰድ |

በዚኽ ሠንጠዥ መሠረት የመዓልት(የቀኑ ወይም ብርሃኑ ክፍል) እና የሌሊቱ ክፍል ከወር ወር ይለያያል። የልዩነቱ መሠረት በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 21 እንደተገለጸ የፀሐይ መውጫ በእየወሩ መቀያየር ተከትሎ የተፈጠረ ነው። በዚኽም መሠረት

[160] ዝኒ ከማሁ

ፀሐይ ምድርን እኩል በእኩል የምትከፍላት በዓመት ኹለት ጊዜ ማለትም መዓልቱና ሌሊቱ እኩል በሚኾኑበት በመስከረም እና በመጋቢት ወራት ነው። በትክክል እኩል (Equinox) የሚኾነው መስከረም 25 እና መጋቢት 25 ላይ ነው።[161] ከመስከረምና ከመጋቢት በስተቀር ሌሎች ወሮች የመዓልትና የሌሊት የሰዓት ርዝማኔ እኩል አይደለም።

ሌላው በዚኽ ሠንጠረዥ ለመግለጽ የተሞከረው አሁን የምንገለገልበት አንድ ቀን በ24 ሰዓት ከፍለን ቢኾን የሌሊቱና የመዓልቱ ከወር ወር መለያየት በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ በተቀመጠው መሠረት መኾኑን መረዳት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በእየወሩ የሚወጡ ከዋክብት በሄኖክ የተገለጸውን መተርጉማን (ተርጓሚዎች) በዚክ መልኩ በስፋት አስቀምጠውታል።
የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር የዓመት መጀመሪያ ወር መስከረም የኾነበት አንዱ ምክንያት የመዓልትና የሌሊት እኩል መኾኑ ነው።

## የእየዕለቱን ሰዓት መበላለጥ ሊቃውንቱ በምን ሰፍረው ዐወቁት ?

በሄኖክ የአንድ ቀን ርዝማኔ 18 ክፍል እንደኾነ የተገለጸ ቢኖንም የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ከ18 ክፍል ይልቅ በ24 ሰዓት ከፍለው ለመሥራታቸው ምክንያቱን ማረጋገጥ በዚኽ ጥናት አልተቻለም። የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት  በአንድ ቀን ውስጥ ያሉትን ሰዓቶች ያወቁበትን መንገድ እንዲኽ ብለው መዝግበውታል ‹‹አንተ በትክክል የራስህ ጥላ በደረሰበት ላይ ምልክት ታደርጋለህ፤ ሰዓቱን ለማወቅ እግርህን በማፈራረቅ እየሰፈርህ ትቈጥራለህ። ከመዠመሪያው ሰዓተ መዓልት እስከ ሠርክ ዐሠራ ኹለት ሰዓት፤ ከታኅሣሥ ወር እስከ ሠኔ ወር 1 1/2 ጫማ በየወሩ ትቀንሳለህ፣ ዳግመኛም ከሠኔ ወር እሰከ ታኅሣሥ ወር 1 ½ ጫማ በየወሩ ትጨምራለህ።››[162] በማለት በሄኖክ ከወር ወር የሰዓት ልዩነት ለመረዳት ችለዋል።

የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 28 መሠረት በማደረግ የፀሐይን ዑደት በመጠቀም ዓመትን በአራት መድበው በእየሦስት ወሩ የሚወጡ ክዋከብትን ይገልጻሉ። በእያንንዱ በአማካይ ዘጠና አንድ (91) ዕለት፣ ከዐሥራ ስምንት (18) ኬክሮስ፣ ከአርባ አምስት (45) ካልዒት የያዙ ወቅቶች ይገኛሉ[163]። እነርሱም

[161] ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም
[162] አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም
[163] ዝኒ ከማሁ

1. **ጸደይ** (ከመጋቢት 26 እስከ ሠኔ 25 ቀን) ፡ በዚኽ ወቅት የሚገኙ ወሮችና ኮከቦች ሚያዝያ /ሐመል/ ፣ ግንቦት /ተውር/ እና ሠኔ /ጀውዛ/ ናቸው። በጸደይ የሚቆመው የሦስት ከዋክብት አለቃ ምልክኤል ይባላል። ወቅቱ የመሬት ጊዜ ነው።
2. **ክረምት** (ከሠኔ 26 እስከ ምስከረም 25 ቀን) ፡ በዚኽ ወቅት የሚመደቡ ወሮችና ኮከቦቻቸው ሐምሌ/ሸርጣን/ ፣ ነሐሴ/ አሰድ/ እና መስከረም /ሰንቡላ/ ናቸው። በክረምት የሚቆመው የሦስት ከዋክብት አለቃ ሕልመልሜሌክ ይባላል። በመኾኑም ወቅቱ የውኃ ጊዜ ነው።
3. **መፀው** (መስከረም 26 እስከ ታኅሣሥ 25 ቀን) ፡ በዚኽ ወቅት የሚመደቡ ወሮችና ኮከቦቻቸው ጥቅምት /ሚዛን/ ፣ ኅዳር/አቅራብ/ እና ታኅሣሥ/ቀውስ/ ናቸው። በመፀው የሚቆመው የሦስት ከዋክብት አለቃ ምልኤል(ሚላኤል) ይባላል።ወቅቱ የነፋስ ጊዜ ነው።
4. **በጋ** (ከታኅሣሥ 26 እስከ መጋቢት 25 ቀን) ፡ በዚኽ ወቅት የሚመደቡ ወሮችና ኮከቦቻቸው ጥር/ጀደይ/ ፣ የካቲት /ደለው/ እና መጋቢት/ሑት/ ናቸው። በበጋ የሚቆውመ የሦስት ከዋክብት አለቃ ናርኤል ይባላል። ወቅቱ የእሳት ጊዜ ነው።

## ኬክሮስና ክንትሮስ

ኬክሮስ፡- ትርጉሙ የመሬት ትልቅ ክፍል (መሬት ላይ በሐሳብ የተሰመረ ረጅም መስመር) ማለት ሲኾን ከደቡብ እስከ ሰሜን የተዘረጋ ፤ ሌሊቱና መዓልቱ ተለይቶ የሚታወቅበት መክፈያ ነው። ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያለው የኬክሮስ ብዛት ስድሳ ነው።[164]

ክንትሮስ ፡- ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የተዘረጋና ምድርን በሐሳብ የሚከፍል መስመር ነው። ክንትሮስ ከኬክሮስ ጋር እንደ ጥብጣብ አልጋ የተሠራ የረጋ ነፋስ ስለኾነ እንደ ምድር ኾኖ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ይጓዙበታል።[165] ይኸም ማለት የፀሐይን እና የጨረቃን የጉዞ መስመር ለይቶ ለማወቅ የሚያገለግል መለኪያ ይኾናል ማለት ነው።

[164] ጌታቸው ኃይሌ ፤ 1993 ዓ.ም.
[165] አለቃ ያሬድ ፈንታ ፤ 2004 ዓ.ም.

የኬክሮስ መጠን 16 ዓመት ከ8 ወር ያኽል የሚፈጅ ሲኾን ይኽም እንደሚከተለው ሊከፋፈል ይችላል።[166] 1 ኬክሮስ ፡ 6 ክንትሮስ ፤1 ሰዓት፤ 5 ኬክሮስ (30 ክንትሮስ) ነው። ስለዚኽ 1 ዕለት፡ 60 ኬክሮስ ፤1 ኬክሮስ፡ 60 ካልዒት[167]፤1 ካልዒት፡ 60 ሣልሲት[48] ፤1 ሣልሲት ፡ 60 ራብዒት[49]፤ 1 ራብዒት፡ 60 ኃምሲት[50] 1 ኃምሲት፡ 60 ሳድሲት[51] ይኾናል ማለት ነው።

## ዑደተ ጨረቃ (ወርኅ)

ጨረቃ በዋናነት ሊሊቱን ለመቍጠር የምታገለግል ናት።[168] በእየዕለቱም የራሷን ቅርፅ ስለምትለውጥ፤ እያንዳንዱ የጨረቃ ቅርፅ ራሱን የሚደግመው በየኻያ ዘጠኝ ወይም በየሠላሳ ቀን ነውና። ጨረቃ ሙሉ (full moon) በኾነች ጊዜ የብርሃን መጠኗ የፀሐይን አንድ ሰባተኛ (1/7) ያኽል ነው።[169] ጨረቃ የምትወጣው በምሥራቅ ሲኾን የምትገባውም እንደ ፀሐይ በምዕራብ ነው። ጥንተ ዮን (ጨረቃ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየችው) ለጨረቃ ሐሙስ ነው።

ጨረቃ በምትወለድበት/በምትወጣበት ጊዜ ወደ ክቡ የሚገባው ቅርፃ (የማጭድነቱ ቅርፅ) ወደ ምሥራቅ ኾኖ ፀሐይ ስትጠልቅ በአራት ኬክሮስ ርቀት ትወጣለች። አንድን ሌሊት ሙሉ 60ውን ኬክሮስ የምታበራው መታየት ከጀመረች በ14/15 ኛው ቀን ነው። ስለዚኽ አማካይ የዕለት መንገዷ 59 ኬክሮስ 3 ካልዒት 40 ሣልሲት 16 ራብዒት 18 ኃምሲት ከ48 ሳድሲት ሲኾን በዚኽ ጉዞዋ ከምዕራብ ሳትደርስ ወይም 56 ካልዒት 19 ሣልሲት 43 ራብዒት 41 ሐምሲት ከ12 ሳድሲት ሲቀራት ፀሐይ 60ውን ኬክሮስ ፈጽማ በምሥራቅ ትታያለች። እንዲኹም ኻያ ቀን ሲኾናት (በኻያኛው ቀን) በቀን (በመዓልት) እና በማታም (በሌሊትም) ትታያለች። ሄኖክ እንደሚለው በሃያ ቀኗ በሌሊት ሰው መስሎ በቀን ሰማይ መስሎ ይታያል ይላታል።[170]

የዓመቱን አጠቃላይ በዓላት፣ አጽዋማት፣ አሥርቆት ወዘተ ለማውጣት አበቅቴና መጥቅዕ ማወቅ ያስፈልጋል።

---

166 ዝኒ ከማሁ
167 ካልዒት ማለት ሁለተኛ ማለት ሲሆን ከኬክሮስ ቀጥሎ የሚሰላበት የጊዜ መለኪያ
168 ኦሪት ዘፍጥረት 1፡16
169 መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘኤጲፋኖስ
170 መጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 22

## ሀ. አበቅቴ

ጥንተ አበቅቴ[171] የሚባለው በእየዓመቱ በፀሐይና በጨረቃ መካከል የሚፈጠሩ ልዩነቶች ናቸው፡፡ በየዓመቱ አበቅቴው ስለሚለያይ በተያዘው ዓመት አበቅቴ ላይ 11 ቢደመር የሚመጣው ዓመት አበቅቴ ፣ 19 ቢደመር ደግሞ ያለፈው ዓመት አበቅቴ ይገኛል፡፡

## ለ. መጥቅዕ

መጥቅዕ ማለት ጨረቃ በዓመቱ የመጀመሪያው ወር (30 ቀን) የሚሞላበት የዕለት ቍጥር ነው፡፡ መጥቅዕ የቃሉ ትርጉም ደወል ማለት ሲኾን አጽዋማት እና በዓላትን ለማውጣት ይጠቅማል፡፡ የመጥቅዕና የአበቅቴ ድምር ኹልጊዜ ሠላሳ ነው፡፡

እያንዳንዱ ዓመት ላይ በፀሐይም ኾነ በጨረቃ ቈጥሮ በስሌት ለማግኘት በመጀመሪያ ከጌታችን ልደት በፊት ያለውን ጊዜ ዓመተ ፍዳ እና ከጌታችን ልደት ወዲኽ ያለውን ዓመተ ምሕረት (በፀሐይ) በመደመር፤ በቀመረ ዐረብና በንዑስ ቀመር በመቀመር በጨረቃ የዓመቱ ቍጥር ምን ያኽል እንደ ኾነ ማወቅ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፡- የ2012 ዓመት ማለትም ከልደተ ክርስቶስ ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለውን 2012 ዓመተ ፀሐይ በጨረቃ ስንት ዓመት እንደኾነ ለማስላት በመጀመሪያ ዓመተ ፀሐይን በቀመረ ዐረብ ፣ በንዑስ ቀመር መቀመር ያስፈልጋል፡፡ ይኽም ማለት፡-

2012 ÷ 228 = 8 ቀመረ ዐረብ ኾኖ፤ 188 ዓመት ይተርፋል፡፡ ትርፉን (ቀሪውን) በንዑስ ቀመር እንቀምረዋለን (እናካፍለዋለን)፡፡

188 ÷ 19 = 13 ንዑስ ቀመር ኾኖ፤ 13 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል፡፡ ከዚኽ በኋላ ከቀመረ ዐረብ የሚገኘውን በ7 ዓመት፤ ከንዑስ ቀመር የሚገኘውን በ7 ወር፤ ለንዑስ ቀመር ስናካፍል ያገኘነውን ዓመተ አበቅቴ ደግሞ በ 11 ዕለት (በጥንተ አበቅቴ) እናባዛለን፡፡

መጨረሻ ካገኘነው ዓመተ አበቅቴ አንድ ዓመት መቀነሱን ልንዘነጋ አይገባም፡፡[172] ይኽም የያዝነው ዓመት ገና ስላልተጠናቀቀ ነው፡፡ እንዲኹም ለጨረቃ ዘመን መሠረት የኾነውን 4 ወር ከ 10 ቀን ፣ ከትራፋተ ዐውድ የተገኘውን 24 ዕለት

[171] ጥንተ አበቅቴ ማለት የመጀመሪያው በፀሐይና በጨረቃ መካከል የተፈጠረው የ11 ዕለታት ልዩነት ማለት ነው፡፡

[172] አዋጅ ነው፡፡

መደመርም ያስፈልጋል።[173] እነዚኽ ዕለታት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በየዓመቱ ከሚተርፉት ተሰብስበው የተገኙ ናቸው።

ስለዚኽ 8 ቀመረ ዐረብ × 7 ዓመት = 56 ዓመት

13 ንዑስ ቀመር × 7 ወር = 91 ወር (91 ወር ማለት 7 ዓመት ከ 7 ወር ማለት ነው።)

12(13 - 1) ዓመተ አበቅቴ × 11 ዕለት = 132 ዕለት (132 ዕለት ማለት ደግሞ 4 ወር ከ 12 ቀን ማለት ነው።)

ይኽ ኹሉ በአንድ ላይ ሲደመር 63 ዓመት (56+7) ከ11 ወር (7+4) ከ 12 ዕለት ይኾናል። ይኽንን የአገኘነውን ዓመት ከዓመተ ፀሐይ አንድ ዓመት ከአነሣንለት በኋላ ቀሪው ላይ እንደምረዋለን። በመኾኑም

2011(2012 - 1) + 63 ዓመት 11 ወር 12 ዕለት = 2070 ዓመት ከ11 ወር 12 ዕለት ይኾናል።

ይኽም ማለት ክርስቶስ ከተወለደ ጀምሮ (በፀሐይ) መስከረም 1 ቀን 2012 ዓ.ም በዓመተ ጨረቃ ሲሰላ 2070 ዓመት ከ11 ወር ከ12 ዕለት ኾኖታል ማለት ነው።

በአጠቃላይ ዘመንን ለመቁጠር መነሻውን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። በሐሳበ ዲሜጥሮስ የቀመር መነሻው ዕለት (ጥንተ ቀመር) ማክሰኞ ሲኾን፣ የሐሳበ ቢዘን ጥንተ ቀመር እሑድ እንዲኹም የሐሳበ ጉንዳጉንዲ ዓርብ ናቸው። ሦስቱም ሐሳቦች መነሻቸውን ለመወሰን እና ልዩነቱን ለመግለጽ የየራሳቸው አመክንዮ ያቀርባሉ።[174]

በአጠቃላይ ባሕረ ሐሳብ በኹለቱ አዕዋዳት ማለትም የፀሐይና ጨረቃ ዑደት በመጠቀም በኹለቱም እንደ አስፈላጊነታቸው የሚቆጥር ልዩ የኾነ የዘመን መቍጠሪያ ኾኖ የሚያገለግል ነው። ዘመንን ለመቍጠር በዋናነት የዓለምን ዘመን መክፍያ የኾነውን የጌታችንን ልደት ሊቃውንት የክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ ብለው ተርተውታል።[175] ይኽም የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጥር ከሌሎች በተሻለ ነገረ መለኮታዊ ይዘት ያለው እና፤

173 አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም. ገጽ 154
174 ዝኒ ከማሁ
175 ኅሩይ ሰሜ፡ ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፡ 2000 ዓ.ም. ገጽ 75

# ሥነ ከዋክብት

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 24 በስፋት እደተጠቀሰው ከዋክብት በስም እየጠራ የሚቆዩበትን የጊዜ ርዝማኔ ይገልጻል፡፡ ከዋክብት ጨረቃ ጋር በሌሊት ያበሩ ዘንድ የተፈጠሩ ናቸው፡፡[176] የብርሃን መጠናቸው ከጨረቃ ያነሰ ነው፡፡ ቅርፃቸውም እንደ ፀሐይና ጨረቃ ክበብ ሳይኾን የተለያየ ቅርጽ አላቸው፡፡ ለምሳሌ የአይሁድ ኮከብ የሚባለው ባለስድት ጫፍ አለው፡፡

የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የከዋክብት ብዛት እንደማይታወቅ እና የብርሃን መጠናቸው አንዱ ኮከብ ከሌላው እንደሚበላለጡ እንዲኹም ብርሃን የሌላቸው ከዋክብት መኖራቸውን ይናገራሉ፡፡ "መጽሐፍ አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይበልጣል"[177] ኹሉም ክዋክብት እኩልና ተመሳሳይ አይደሉም፡፡ በእየዕለቱና በእየወሩ የማይወጡ ከዋክብት ማለትም በኾኑ ዘመናት ልዩነት አንድ ጊዜ የሚታዩ ከዋክብት አሉ፡፡[178]

የከዋክብት ትምህርት በባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ዘንድ የሚሰጥበት ምክንያት ከዋክብት እንደ ፀሐይና ጨረቃ ኹሉ ለዘመን መቊጠሪያነት የሚያገለግሉ ስለኾኑ እና የዘመን መለዋወጥን ተከትለው የሚከሰቱ ክስተቶች ከከዋክብት ጋር ግንኙነት ስላላቸውም ጭምር ነው፡፡ ስለዚኽ የከዋብትን ትምህርት በኹለት ከፍለን እንመልከት፡፡

# የከዋክብት ዓይነታቸውና ጠቀሜታቸው

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ዘመንን እንደ ፀሐይና ጨረቃ ኹሉ በከዋክብት ይቈጥራሉ፡፡ በከዋክብት አንድ ዓመት ሦስት መቶ ስድሳ አራት ቀን (364) ነው፡፡

የከዋክብትን ከወጡበት ጊዜ አንጻር ለኹለት ከፍለን ማየት እንችላለን ፤ አንዱ ሄኖክ በመጽሐፉ በእየሦስት ወሩ (ስማቸው ዝቅ ብሎ ተጽፏል) ፣ በእየወሩ ፣ በእየዓሥራ ሦስት ቀንና በእየዕለቱ የሚወጡ ከዋክብት በማለት የለያቸው ሲኾኑ እነዚኽንም ከዋክብት ከላይ በሠንጠረዥ 1 እንደተገለጸው በስማቸው ተጠርተዋል፡፡[179] ኹለተኛው የከዋክብት ዓይነቶች ቋሚ መውጫ ዕለት የሌላቸው በተወሰነ የጊዜ ልዩነት የሚወጡ

176 ኦሪት ዘፍጥረት 1፥16
177 1ኛ ቆሮ 15፥ 41
